

‹‹የሃይማኖት ተቋማት ራሳቸውን በመፈተሽ ራሳቸውንም አገሪቱንም ከጥፋት መታደግ ይጠበቅባቸዋል››

- መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ፣ በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮትና የስነልቦና መምህር

ገጽ 6

ጥንቃቄ ለአመጋገብ!

ገጽ 8


# አዲስ ዘመን

81ኛ ዓመት ቁጥር 225 ሚያዝያ 15 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## ‹‹በዓሉ የአስተሳሰብ ትንሳኤ የምናመጣበት ሊሆን ይገባል››

- መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ
በቅድስት ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮትና የስነልቦና መምህር



ፎቶ - እዩብ ተፈሪ

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ አበባ፡- መላው የክርስትና እምነት ተከታዮች የዘንድሮውን የትንሳኤ በዓል ሲያከብር ከመብልና መጠጥ ባለፈ የአስተሳሰብ ትንሳኤ ለማምጣት ቁርጠኛ የሚሆንበት ሊሆን እንደሚገባ በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮትና የስነልቦና መምህር መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ አሳሰቡ፡፡

አባ ጌዴዎን ብርሃነ ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ ትንሳኤ ሰዎች እንዲኖሩ ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ መስዋዕት አድርጎ ያቀረበበት የመጨረሻው የሰላም ምዕራፍ ነው፡፡ በመሆኑም መላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሚከበርበትን መሰረታዊ ዓላማን ከግምት ውስጥ

“በዓሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ሕግን በሚተላለፉ ላይ እርምጃ እንዲወሰድ የብሔራዊ ደኅንነት ምክር ቤት ወሰነ

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- ለሰላምና ለሀገር ደኅንነት ሚናቸውን መወጣት ሲገባቸው፤ በተቃራኒው በተሰለፉ፣ ሕግን በሚተላለፉ ቡድኖችና ግለሰቦች ላይ ተገቢው ርምጃ እንዲወሰድ የብሄራዊ ደኅንነት ምክር ቤት ወሰነ፡፡

የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት በወቅታዊ ሀገራዊ የደህንነትና የፀጥታ ጉዳዮች ላይ መክሮ ትናንት ባወጣው መግለጫ፤ ሕግን በሚተላለፉ ቡድኖችና ግለሰቦች ላይ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ምክር ቤቱ በመግለጫው ለሰላምና ለሀገር ደኅንነት ሚናቸውን መወጣት ሲገባቸው፤ በተቃራኒው የተሰለፉ ግለሰቦች፣ አካላት እና ቡድን ላይ ሕግና ጸጥታ የማስከበር ሥራ እንደሚሰራ አመልክቷል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ባህልን ለመገንባት ስንነሣ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያስከብሩ ጥብቅ ርምጃዎች በነጻነትና መብት ስም እንዳይላሉ፤ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት ለማስከበር የምንወስዳቸው ጥብቅ ርምጃዎችም

ሕግን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ - ገበየሁ ገብሬ

## ‹‹ጥላቻ፣ ኢ-ፍትሐዊነትና አመጸኝነት ለትውልድ የሚተላለፉ ክፉ ዘሮች በመሆናቸው መገታት ይገባቸዋል››

- ፓስተር ጻድቁ አብዶ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ቂም በቀል፣ ጥላቻ፣ ኢ-ፍትሃዊነት፣ አመጸኝነት እና አድመኛነት ለትውልድ የሚተላለፉ ክፉ ዘሮች በመሆናቸው መጸየፍ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሕብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻድቁ አብዶ ገለጹ፡፡

“ጥላቻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የላልይበላ ገዳም ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው የሚያስችል እንቅስቃሴ ተጀመረ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- የላልይበላ ገዳም ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖረው ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩ ተገለጸ፡፡

የድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ አስተባባሪ ዲያቆን አንተነህ እሸቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ የላልይበላ ገዳም በነበረበት ለመመለስ በዘላቂነት መፍትሔ የሚሆነው በተቻለ ፍጥነት የሀገርን ሰላም እና የቱሪዝም ፍሰቱን ወደነበረበት መመለስ ነው።

ግሸን በዓመት እስከ አንድ ሚሊየን ዜጎች እንደሚጎበኙት የጠቆሙት አስተባባሪው፤ በላልይበላም የሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴውን ለማነቃቃት እንዲሁም ደብሩ መሰል ችግር ሲገጥመው መቋቋም የሚችልበት ቋሚ የገቢ ምንጮችን በሂደት ለመመስረት መታሰቡን አመላክተዋል።

አስራ አንድ አብያተ-ክርስቲያናትን አቅፎ የያዘው ላልይበላ በውስጡ ከአንድ ሺህ በላይ አገልጋይ ካህናት፣ ከ100 በላይ የቅርስ ጠባቂዎች እንዲሁም በላልይበላ ከተማ ልመና እንዲቀር ለማድረግ ያደራጃቸውና ከደብሩ በቀጥታ የሚደጎሙ አረጋውያን ተጧሪዎች፣ ሕጻናት ከነወላጆቻቸው በድምሩ ከ10 ሺህ በላይ በቀጥታ በገዳሙ የሚደጎሙ ዜጎች መኖራቸውን አንስተዋል፡፡

ገዳሙ ቀደም ሲል ለካህናትና ቅርስ ጠባቂዎች ደመወዝ፣ ለሚያስተዳድራቸው አረጋውያን እና ሕጻናት ድጋፍ የሚያስፈልገውን አራት ሚሊየን ብር ወርሃዊ ወጪውን ሸፍኖ በዙሪያው ላሉ የገጠር አብያተ-ክርስቲያናትና ለአካባቢው ማህበረሰብ ሲደግፍ እንደነበር አስታውሰዋል።

ሰሞኑን በተደረገው የድጋፍ ማሰባሰብ ፕሮግራም ስምንት ሚሊየን የሚሆን ብር ቃል መገባቱን አስታውሰዋል። ነገር ግን ከሁለት ወር የዘለለ የደመወዝ ወጪ መሸፈን የማይችል በመሆኑ ዘላቂ ድጋፍ መመስረት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰላምታ መጽሔት ላይ የላልይበላ ፎቶ ሳይወጣ የቀረበት ጊዜ የለም ያሉት ላልይበላ ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ቅርስ ጭምር በመሆኑ ሊረሳ አይገባም ብለዋል።

የላልይበላ ዓለም ዓቀፍ ቅርስ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ የሆቴሎች፣ የባንኮችና የተለያዩ ተቋማት የገቢ ምንጭ በመሆኑ ገዳሙን ባለበት ለማቆየት የመጀመሪያውን እሳት በማጥፋት በኩል ሁሉም ሊረባረቡ ይገባል ብለዋል።

ባንኮችም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ላልይበላ ላይ ያገኛሉ ያሉት አስተባባሪው፤ ገዳሙ ችግር ላይ ሲወድቅ ድጋፍ ሊደረግለት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የሮሃ ቅዱስ ላልይበላ ገዳም የገቢ ማሰባሰቢያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አቢሲንያ ባንክ፣ ዳሽን ባንክ እና ሕብረት ባንኮች በተመሳሳይ ባለ አራት ዲጂት የባንክ ሂሳብ ቁጥር 0712 ድጋፍ እንዲደረግ የተመቻቸ መሆኑን ጠቁመዋል።



ዲያቆን አንተነህ እሸቱ

# ኅብረተሰቡ መጪዎቹን በዓላት ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ እንዲያከብር የምጣኔ ሀብት ምሁራን መከሩ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ መጪዎቹን በዓላት ሲያከብር ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ መሆን እንደሚገባው አስተያየታቸውን የሰጡ የምጣኔ ሀብት ምሁራን መከሩ::


የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሃብት መምህሩ ፍሬዘር ጥላሁን እንደሚሉት፤ በዓላትን አስመልክቶ የምግብና ምግብ ነክ ሸቀጦች የዋጋ ጭማሪ ይኖራል፤ስለሆነም ኅብረተሰቡ በዓላቱን ሲያከብር አቅምን ባገናዘበና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሊሆን ይገባል::

በኢትዮጵያ የአቅርቦትና ፍላጎት አለመጣጣም በመፈጠሩ የኑሮ ውድነት ተከስቷል:: ይህንን ለመቋቋምም የመጪዎቹንና ቀጣዮቹን በዓላት አቅምን ባገናዘበና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ማሳለፍ ለችግሩ መፍትሄ እንደሆነ ገልጸዋል::

በኢትዮጵያ በሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በዓል የሚያከብረው በብዙ ወጪና ለብዙ ቀናት በሚደረግ የድግስ ዝግጅት ነው:: አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር በዓሉን አቅምን ባገናዘበ መንገድ ማሳለፍ ይገባል:: ይህን በማድረጋችን ያዘመመብንን የኑሮ ውድነትና የሸቀጦች ዋጋ መናር ማስታገስ እንችላለን ብለዋል አቶ ፍሬዘር:: አሁን ላይ በአገር ደረጃ ምግብና የምግብ ነክ ሸቀጦች ዋጋቸው እየጨመሩ ነው:: የዋጋ መናር ላይ በዓሉ ተጨምሮ አቅምን ባገናዘበ ማሳለፍ ካልቻልን በአገር ምጣኔ ሀብት ላይ ጫና ይፈጠራል::

በዓሉን ተከትሎ ስግብግብ ነጋዴዎች ትርፍን ለማሳደግ የመንቀሳቀስ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ:: መንግሥት ቁጥጥሩን ሊያጠናክር ይገባል ሲሉም አቶ ፍሬዘር መክረዋል:: በማህበረሰቡ በኩል ከኑሮ ውድነት አጉል ከበርቴ ነጋዴዎች መጠንቀቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል::

ለበዓል ልዩ ገቢና ቁጠባ በሌለባት አገር እየተስተዋለ ባለው የሸቀጦች ዋጋ መናር በዓልን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ከባድ ነው ያሉት አቶ ፍሬዘር፤ በዓሉን በደማቅ ሁኔታ ለማክበር ከፈለግን ደግሞ ልዩ የሆነ ለበዓል ፍጆታ



**አቶ ፍሬዘር ጥላሁን**

የሚውል የቁጠባ ባህልን ልናዳብር ይገባል ይላሉ::

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ዶክተር ይንገስ ዓለሙ በበኩላቸው፣ ማህበረሰቡ የወቅቱን የኑሮ ውድነት ባገናዘበ መልኩ ማክበርና በቀጣይ ከበዓል በኋላ ሊያጋጥም የሚችለውን የኑሮ ጫና ታሳቢ ማድረግ ይኖርብናል ብለዋል::

ባህልን በአንድ ጀንበር መቀየር ይከብዳል ያሉት ዶክተር ይንገስ፤ ያለንንና በድጎማ የሚቀርቡትን ፍጆታዎች በተገቢው መንገድ መጠቀም ያስፈልገናል ብለዋል::

መጪዎቹን የፋሲካና የኢድ ዓል-ፈጥር በዓላት ስናከበር ጎረቤትን ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባ የመከሩት ዶክተር ይንገስ፤ መንግሥትም ለበዓላቱ የሚያስፈልጉ የፍጆታ ምርቶቸን ማህበረሰቡን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ ማቅረብ ይገባዋል ሲሉ ገልጸዋል::

እንደ ዶክተር ይንገስ ገለጻ፤ ዜጎችና መንግሥት በቀጣይ ሊያጋጥሙን የሚችሉትን ክስተቶች እንዴት ማለፍ ይገባል:: በመጪዎቹ የክረምት ወራት በመስኖና በመደበኛ እርሻ እንዴት በማምረት አቅርቦትን ማሻሻል እንደሚገባም ማሰብ አለብን ብለዋል::

# በጋምቤላ ክልል ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት ተደርጓል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አባባ ፡- ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ እንደሚገኝ የጋምቤላ ክልል አስታወቀ:: ዘንድሮ በክልሉ በ64 ተፋሰሶች ላይ አካባቢን የማልማት ሥራ ተሠርቷል::

የክልሉ ግብርና ተፈጥሮ ሃብት ቢሮ ኃላፊ አቶ አጃክ ኡቻላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ክልሉ ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ በተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ ትኩረት አድርጓል:: አየር ንብረት ለውጥና የአፈር መሸርሸርን በመከላከል በግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር በክልሉ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ተፋሰስ ልማት ጉልህ ሚና አለው ብለዋል:: ይህንን ለማሳካት በርእሰ መስተዳድሩ የሚመራ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እስከታችኛው የኅብረተሰብ ክፍል ድረስ ንቅናቄ ውስጥ መግባቱን ገልጸዋል:: እስከአሁን ድረስ በተሰራው ስራ በ64 ተፋሰስ አካባቢዎች ልማት ማካሄድ ተችሏል::

እንደ ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ በተፋሰስ ልማቱ የተሰሩ እርከኖችና እስትራክቸሮች እንዳይበላሹ በአረንጓዴ ልማት ሥራዎች በመታገዝ ባለፈው ዓመት ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል:: ዘንድሮ ደግሞ አምስት ሺህ 325 ተፋሰስ አካባቢዎች ላይ የሚተከሉ ዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ችግኞች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰው፤ የተዘጋጁ ችግኞች 75 በመቶው ለምግብነት የሚውሉ መሆናቸውን አመልክተዋል::

በክልሉ በዘንድሮ የመኸር እርሻ በዘር የሚሸፈን የእርሻ መሬት በመጨመር ምርትን ለመጨመር በእቅድ እየተሠራ ነው:: ባለፈው የመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ከ147 ሺህ 701 ሄክታር ወደ 148ሺህ 786 ሄክታር ከፍ ለማድረግ በእቅድ መያዙንም ኃላፊው ገልጸዋል:: እቅዱም ተግባራዊ ሲደረግ ምርቱ ከአራት ሚሊዮን 345 ሺህ 325 ኩንታል ወደ አራት ሚሊዮን 562 ሺህ 290 ኩንታል ጭማሪ እንደሚያሳይ ጠቁመዋል::



አቶ አጃክ ኡቻላ

በክልሉ የግብርና ሥራዎችን በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ ለማድረግ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ያነሱት ቢሮ ኃላፊው፤ በዘንድሮው ዓመት በተለያየ ምክንያት በክልሉ የበጋ ስንዴን በሙሉ አቅም ማከናወን አለመቻሉን ገልጸዋል:: በዚህም ምክንያት የበጋ መስኖ ምርት ቀንሷል::

በሁሉም የግብርና ሥራዎች እንደ ክልል ያለው የአቅም ውስንነት በግብርና ምርትና ምርታማነት መጨመር ላይ ሌላኛው ተግዳሮት መሆኑን ገልጸዋል:: የምርጥ ዘር ማባዣ በክልሉ አለመኖርና ምርጥ ዘር ጊዜውን ጠብቆ ለአርሶ አደሩ አለመድረስ ሌላኛው በዘርፍ እድገት ላይ ጫና ያሳደሩ ጉዳዮች መሆናቸውን ገልጸዋል::

የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የገጠሙንን ተግዳሮቶችን ለመፍታት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጠይቀዋል::



አቶ ከበደ ዴሲሳ

# አዲስ የወጣው መመሪያ እርስ በእርሱ የሚጣረስ መረጃ እንዳይፈጠር እንደሚረዳ አገልግሎቱ ገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዲስ ያወጣው መመሪያ እርስ በእርሱ የሚጣረስ መረጃ እንዳይፈጠር እንደሚረዳ ገለጸ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ከበደ ዴሲሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለይ የፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች መረጃዎች በተገቢው መንገድ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ አገልግሎቱ መመሪያ አውጥቷል።

በመመሪያው መሰረት በፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የሚገኙ የኮሙኒኬሽን ክፍሎች አስፈላጊውን መረጃ ለሕዝቡ በቅንጅት እንዲያደርሱና ድጋፍም እንዲደረግላቸው ይረዳል።

እንደ አቶ ከበደ ማብራሪያ፤ በወጣው መመሪያ መሰረት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚኒስቴር መስሪያ ቤት የኮሙኒኬሽን ኃላፊዎችን የመምራት፣ የማቀናጀት፣ የመደገፍና የመመደብ ስልጣን አለው። የኮሙኒኬሽን ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን ለማብቃትም እገዛ ያደርጋል ብለዋል። ተገቢውን መረጃ በተናበበ መልኩ በቀላሉ በህብረተሰብ ዘንድ እንዲያደርሱም መስሪያ ቤቱ ድጋፍና ክትትል እንደሚያደርግ ጠቅሰዋል።

መረጃ በተናበበ መልኩ በቋሚነት ለሕዝቡ የሚደርስበት ሁኔታ ላይ ከሚዲያ አመራሮች ጋር ቋሚ የግንኙነት ጊዜ መኖሩን የጠቆሙት ሚኒስትር ደኤታው፤ በተመሳሳይ መልኩ መስሪያ ቤቱ በወቅታዊ ጉዳይ ላይ በየሳምንቱ መግለጫ እየሰጠ ይገኛል ብለዋል።

ስህተቶች ከተፈጠሩ ወይም እንዳይፈጠሩ ከሚዲያዎች ጋር ባላቸው ቋሚ ግንኙነት ጊዜ ግምገማ እንደሚደረግም አቶ ከበደ ተናግረዋል።

አገልግሎቱ ትክክለኛ መረጃ ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን ከፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ከሚዲያ ተቋማት ጋር በቅንጅት እየሠራ ይገኛል። መንግሥትንና ሕዝብን ለማቀራረብ የተናበበ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ታማኝ ድልድይ ሆኖ ለማገልገል ጥረት እያደረገም ነው። እርስ በእርሱ የሚጣረስና ጥርጣሬ የሚፈጥር መረጃ ለማቃናት ያላሰለሰ ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑም ሚኒስትር ዴኤታው ገልጸዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የሚወጡትን መረጃዎች በማዕከላዊነት የሚመራ አካል ባለመኖሩ በአንድ ጉዳይ ላይ እርስ በእርሱ የሚጣረስና የተለያየ መረጃ የማቅረብ ችግር በስፋት ይታይ እንደነበር የጠቆሙት አቶ ከበደ፤ መንግሥት ክፍተቱን በመረዳት ወጥና ተዓማኒ መረጃ ለህብረተሰቡ ተዳራሽ ለማድረግ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መዋቀሩን አንስተዋል።

በመመሪያው መሰረት ተቋማት መረጃን በአግባቡ ለሚዲያ እንዲሰጡ አገልግሎቱ ድጋፍ እንደሚያደርግ መጠቀሱንም ጠቁመዋል። መረጃ የመስጠት ግዴታና መረጃን የማግኘት መብት በህገ መንግሥቱ የተደነገገ ነው። ስለሆነም ይህ እንዲሳካ አስፈላጊውን ክትትል አገልግሎቱ ያደርጋል ብለዋል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት በቀጣይ ሚዲያዎች ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙና ለሕዝብ ተደራሽ እንዲያደርጉ ይደግፋል። በተለይ ደግሞ የሀሰት መረጃን ለማጋለጥ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

# በአማራ ክልል በቀጣዩ የምርት ዘመን 143 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዷል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዩ ዓመት የምርት ዘመን በጦርነቱ ሳቢያ የቀነሰውን ምርት ታሳቢ በማድረግ 143 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በክልሉ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው 243 ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር እስካሁን 112 ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር መሰብሰቡ ተገለጸ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የሰብል ልማት ክትትልና ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ አለባቸው አሊጋዝ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014/2015 የምርት ዘመን አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር በዘር በመሸፈን 143 ሚሊዮን ምርት ለማምረት እየተሰራ ነው።

እንደ አቶ አለባቸው ገለጻ፤ በ2014 ዓ.ም በአሸባሪው ሕወሓት ወረራ ምክንያት ቀንሶ የነበረውን ምርት ታሳቢ በማድረግ የተሻለ ምርት ለማምረት የግብርና ቢሮው ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። ለዚህም የሙያተኞችን አቅም ማጎልበት ሲሆን በየደረጃው ያሉ የግብርና ባለሙያዎች የአሰራር ክለሳ በማድረግ እስከ ቀበሌ ድረስ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል።



አቶ አለባቸው አሊጋዝ

በተጨማሪም በስልጠናው አርሶ አደሮች እንዲሳተፉ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

የምርት እድገትን ለማምጣት ከአርሶ አደሩ እስከ አመራሩና የግብርና ባለሙያው ከፍተኛ ቁርጠኝነትና የነቃ ስራ የሚጠይቅ መሆኑን የገለጹት የሰብል ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተሩ፤ ለታቀደው ምርት ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች መካከል የምርጥ ዘር አቅርቦት አንዱ ነው። ይህም በክልሉ በተለያዩ ድርጅቶች የተባዛ ወደ 243 ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር ይሰበሰባል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን እስካሁን 112 ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር ተበጥሮ ተሰብስቧል።

ምርጥ ዘሩ በቶሎ የሚዘሩ አካባቢዎችን ታሳቢ በማድረግ እየተሰራጨ መሆኑን የገለጹት አቶ አለባቸው፤ ክልሉ ከሚፈልገው ስምንት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እስካሁን ወደ ክልሉ የገባው 50 በመቶ የሚሆነው ብቻ ነው ብለዋል።

በዚህ ዓመት የሰው ሰራሽ የአፈር ማዳበሪያ የዋጋ መናርና የአቅርቦት እጥረት አለ። የዋጋው መናር እንደ አገር ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ በመሆኑ ችግሩን አርሶ አደሩ እንዲገነዘበው የማድረግ ስራ ተሰርቷል ብለዋል።

በተጨማሪም በህገ ወጥ መንገድ እንዳይሸጥ ቁጥጥር በማድረግ የቀረበውን ማዳበሪያ በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ምርታማ ለሆኑ አካባቢዎችና ውጤት በሚያመጡ አካባቢዎችም እንዲሰራጭ የማድረግ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።



# "ከኢድ እስከ ኢድ ወደ ሀገር ቤት ጥሪ"ን ተከትሎ ከተለያዩ የዓለም አገራት እንግዶች እየገቡ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- "ከኢድ እስከ ኢድ ወደ ሀገር ቤት ጥሪ"ን ተከትሎ ከተለያዩ የዓለም አገራት እንግዶች ወደ አገር ቤት እየገቡ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ ቀደም ሲል ኢድን በአገር ቤት እናክብር በማለት "ታላቁ የኢድ ሰላት በኢትዮጵያ" በሚል መሪ ቃል ለኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ለኢትዮጵያ ወዳጆች ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል።

በዚህም መሰረት ከተለያዩ የዓለም አገራት ኢድን በአገር ቤት ለማክበር እንግዶች አዲስ አበባ በመግባት ላይ ይገኛሉ።

በቀረበው ጥሪ መሰረት ኢድን በጋራ እያከበርን፣ የተቸገሩ ወገኖችን በመጠየቅና በማገዝ ጥሩ ቆይታ ልናደርግ መጥተናል ሲሉ ኢዜአ ያነጋገራቸው እንግዶች ገልጸዋል።

በተለይ በጦርነት ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ተዘዋውሮ በመጎብኘት አቅማቸው የቻለውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

በመንግሥት የተደረገው ጥሪ ወገኖችን ከማገዝ በተጨማሪ ቤተሰብን አግኝቶ ኢድን በጋራ ለማሳለፍም ልዩ አጋጣሚ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢድን በጋራ ለማክበር የተገኙት ወገኖቻችን በቆይታቸው የተቸገሩ ወገኖችን በማገዝ ወደ መጡበት ሲመለሱ ደግሞ የአገራቸው አምባሳደር በመሆን የኢትዮጵያን እውነታ የሚያስረዱ መሆኑን ከኢድ እስከ ኢድ ብሔራዊ ኮሚቴ ጣምራ ሰብሳቢ ዑስታዝ አቡበከር አህመድ ገልጸዋል።

ለኢድ የሚመጡት በዓሉን አክብረው በአገራቸውም ኢንቨስት የማድረግ እድል እንዲያገኙ እየተመቻቸላቸው መሆኑን ተናግረዋል።

ከኢድ እስከ ኢድ የጎረቤት አገራት የእምነቱ ተከታዮች እና የሃይማኖት መሪዎች ጥሪ የተደረገላቸው መሆኑንም ኡስታዝ አቡበከር አስታውሰዋል።

ኢትዮጵያ በእስልምና ታሪክ ትልቅ ድርሻ ያላትና ታሪካዊ ሀገር በመሆኗ ዓለም በቅጡ እንዲያውቃት የሁላችንም ጥረት ሊታከልበት ይገባል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የዘንድሮው 1 ሺህ 443ኛው የኢድ-አልፈጥር በዓል በመላው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ከሳምንት በኋላ የሚከበር ይሆናል።

# አሜሪካ ለኢትዮጵያ 313 ሚሊዮን ዶላር የሰብዓዊ ድጋፍ አደረገች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሜሪካ ለኢትዮጵያ ተጨማሪ 313 ሚሊዮን ዶላር የሰብአዊ ድጋፍ ማድረጓን የአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ገለጸ፡፡

በኢትዮጵያ በሰሜኑ ክፍል በተከሰተው ጦርነት ጉዳት ለደረሰባቸው የአፋር፣የአማራ እና የትግራይ ክልሎች ወገኖች የሚውል ድጋፍ መሆኑ ተገልጿል።

በዚህም በክልሎቹ የሚገኙ 7 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች የምግብና የመጠጥ አቅርቦት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ድርጅቱ አስታውቋል፡፡

አሜሪካ ለኢትዮጵያ ህዝብ እያደረገች ያለውን ድጋፍ አጠናክራ እንደምትቀጥል ቁርጠኝነቷን እያሳየች ነው ያለው ድርጅቱ፤ ከጥር ወር ጀምሮ በአማራና በአፋር ክልሎች ብቻ ከ4 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የምግብ ድጋፍ ማድረጓን አስታውሷል፡፡

የፌዴራል መንግሥትና የአካባቢው ባለሥልጣናት የሰብአዊ እርዳታ በየብስ ትራንስፖርት ወደ ትግራይ እንዲገባ ባደረጉት ውሳኔ ድርጅቱ ከ100 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የምግብና ለህጻናት የሚሆኑ የአልሚ ምግቦች እንዲደርስ ማድረጉን ገልጿል፡፡

# ‹‹በዓሉ የአስተሳሰብ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በማስገባት የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ሊተጉ ይገባል።

«ትንሳኤ ማዕከሉ አዲስ ህይወት ነው። ያ አዲስ ህይወት ደግሞ በመብል ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በአስተሳሰብ ትንሳኤ ላይ የተመሰረተ ነው። ትንሳኤ ዶሮ መብላት አይደለም፤ ዶሮና ሌሎቹ ግርግሮች ለስጋችን ደስታ ማድመቂያ እንጂ የነፍስ ደስታ ማዕከል አይደለም›› ብለዋል። የእምነቱ ተከታዮች የደስታው ምንጭና ማዕከል ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ሊዘነጉ እንደማይገባም አስገንዝበዋል።

«ይህ በዓል የኢትዮጵያን ትንሳኤ የምናይበት ቀን እንዲሆን ሁላችንም በበኩላችን መረባረብ አለብን›› ያሉት አባ ጌዲዎን፤ ለሀገሪቱ እድገት እና ለሰላም ማነቆ የሆኑ ችግሮቻችንን በመተጋገዝ ማስወገድ እንደሚገባ ተናግረዋል።

«ኢትዮጵያ ለሁላችንም በማንም የማትተካ ወርቃችን፣ ጌጣችን፤ ክብራችን፤ ማንነታችን ናት። ስለዚህ እርስበርስ መለያየትና መጋጨታችንን በመተው በአንድ ልብ ለሀገራችን መስራት መቻል አለብን›› ሲሉም አባ ጌዲዎን አሳስበዋል።

በዋናነትም ህዝብን እርስ በርስ የሚያጋጩ አስተሳሰቦችን በማራገፍ ኢትዮጵያ በሰላምም ሆነ በልማቷ ትንሳኤ እንዲሆንላት ሁሉም የቤት ስራውን መስራት እንዳለበት ጠቁመዋል። «ቆሻሻ የሆነውን አመለካከት ከቤታችን ጀምሮ ጠርገን በማውጣት ውስጣችንን ማፅዳት አለብን›› ብለዋል።

«በአዕምሮ የተፈናቀለ ሰው የተፈናቀለ ሰውን አይረዳም። አሁን ሀገራችንን እያተራመሱ ያሉት ከሰውነት አስተሳሰብ የተፈናቀሉ ሰዎች ናቸው›› ያሉት አባ ጌዲዎን፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከበጎ አስተሳሰብ የተፈናቀሉ ሰዎችን በትምህርት፤ በፀሎት የመመለስ ኃላፊነት እንዳለበት ተናግረዋል።

ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉና የተቸገሩትን ወገኖች ህብረተሰቡ ያለውን በማካፈል ኢትዮጵያ ከችግር የምትላቀቅበትን ትንሳኤ ማፍጠን እንደሚገባው አስገንዝበዋል።

«እውነተኛ ትንሳኤ የሚከበረው እቤታችን በምናደርገው የድግስ ልክ ሳይሆን በአስተሳሰብ በመለወጥና ወገኖችን በማገዝና በመደገፍ ነው። ክርስቶስ ስለእኛ ዋጋ እንደከፈለ ሁሉ እኛም በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን ከችግር ለመታደግ ዋጋ መክፈል ይገባናል›› ሲሉም አሳስበዋል።

# ‹‹ጥላቻ፤ ኢ-ፍትሐዊነትና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ፓስተር ጻድቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገጹት፤ ቂም በቀል፣ጥላቻ፣ ኢፍትሃዊነት፣ አመጻኝነትና አድመኝነት፣ ለትውልድ የሚተላለፍ ክፉ ዘሮች ናቸው። በመሆኑም ድርጊቶቹ አንድ ቦታ ላይ መገታት ይገባቸዋል።

ይህንን መርገም ለማስወገድ ትክክለኛው መንገድ የሰላም፣ የእርቅ፣ የይቅርታና የምህረት መንገድ ነው። ከጥላቻ በመላቀቅ፣ ከቂም በቀል ፍላጎት በመጽዳት በአገር ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን በውስጣችን ካለው ክፉ ሃሳብ መላቀቅ ይገባናል ብለዋል።

በአገር ሰላም እንዲሰፍን መጸለይ ይገባናል። በተለያየ እምነት ያለን ኢትዮጵያውያን ሃይማኖተኛ ናቸው የሚባለውን ዛሬ በተግባር መግለጽ ይገባናል። በክርስትና፣ በእስልምናና ሌሎች እምነቶች ሁሉም መጽሐፍት ጥላቻን አያስተምሩም፣ ቂም በቀልን ለእግዚአብሄር ተው እንደሚል እንደቃሉ መታዘዝ ያስፈልጋል።

መዘዙ ለልጅ ልጆችና ለትውልድ ስለሚተርፍ ከዚህ መንገድ መመለስ ያስፈልጋል። የሌላው ህመም ሕመማችን ሆኖ ሊሰማን ይገባል። እምነታችን ሊገዛን ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

የሌሎች ሰዎች ቁስል እንደራሳችን ቁስል፣ የሌሎች ሕመም እንደራሳችን ሕመም ሊሰማን ይገባል ያሉት ፓስተር ጻድቁ፤ እንደ ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአገር አቀፍ ደረጃ ሰላም እንዲሰፍን እየጸለይንና እያሳሰብን ቆይተናል ነው ያሉት።

አሁንም በዚህ እንቀጥላለን። ክፉን በመልካም በማሸነፍ በጎ ሰዎች ዝምታቸውን መስበር አለባቸው። ሰላምና ፍቅርን ከጥላቻ በላይ መስበክ ይኖርብናል ብለዋል።

ሰላም እና እርጋታ የማይጠቅማቸው ሰዎች መኖራቸውን ማመን ያስፈልጋል። በፖለቲካ፣ በብሄር ወይም በሃይማኖት ሰበብ ከሁከቱ እንጠቀማለን፣ እናተርፋለን ብለው በማሰብ ሰላምን ለማደፍረስ የሚንቀሳቀሱ አካላት አንዳንዴ ሃይማኖት ከብሄር ጋር በማጣመር የሚንቀሳቀሱ አሉ። ይህ ነገር ለአድራጊውም አይጠቅምም። ከጉዳት ውጪ የሚያመጣው ጥቅም የለም።

ብሄርም ሃይማኖትም አሁን አልተፈጠረም። ለዘመናት አብረን ኖረን ዛሬ አዲስ አገር እንደመሰረትን ሰዎች ማዕበል እንደሚያናውጠው ባህር መሆን የለብንም። ትርፍ የሚገኘው ከሰላም መሆኑን መቀበል ይገባል።

በሰላም፣ በስምምነት፣ በፍቅርና በመግባባት ሲሆን እንጂ፤ በጉልበት የሚነጠቅ አይቆይም፣ ዘላቂም አይደለም። አንድን ነገር በጉልበት ፈልጎ የሚያገኝ ቢኖር በእጁ ላይ አይቆይም። የሚነጥቀው ጉልበተኛ ይታዘዛል።

ሰው የሚዘራውን ያንኑ ያጭዳልና መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ለሁላችንም የሚበጀን እግዚአብሄር ወደ ልቦናችን እንዲመልሰን፣ የእግዚአብሄር ጣልቃ ገብነት እንዲኖር መጸለይ ያስፈልጋል።

የአእምሮ ቀውስ ያለባቸውና ሰላም የማይጠቅማቸው ሰዎች በቀላሉ የሰውን ስሜት በመኮርኮር ሌሎች ላይ ችግር እንዲደርስ የሚያደርጉ ድርጊታቸው ተገቢ ባለመሆኑ ሊታቀቡ ይገባል። የሌላው ቁስል እንደራስ ቁስል ሊሰማቸው ይገባል።

# ሕግን በሚተሳሰፉ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ዴሞክራሲያዊ ባህልን እንዳያቀጭጩ በሚዛን መንቀሳቀስ ይገባል ብሏል ምክር ቤቱ በመግለጫው።

ሁለቱን በሚዛን ለማከናወን ደግሞ የእያንዳንዱ ዜጋ፣ ተቋም፣ ፓርቲ፣ ቡድን፣ ወገን፣ የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት። የሕግና የጸጥታ ተቋማትም ሕገ መንግሥታዊና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው ብሏል።

እንደ ምክር ቤቱ መግለጫ፤ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ ቡድኖችና ግለሰቦች፣ ሐሰተኛ መረጃዎችን በማሠራጨት ሕዝብና ሀገርን ሰላም የሚነሡ አካላት፣ በሕገ ወጥ መንገድ ታጥቀው የሕዝብን ሰላም የሚነሡና ለታሪካዊ ጠላቶች በተላላኪነት የሚያገለግሉ ቡድኖች ላይ ሕጋዊና ተገቢ ርምጃ ይወሰዳል፡፡

በመሬት ወረራና በተለያዩ የሥርቆትና የማታለል ተግባራት የተሠማሩ፣ የትራንስፖርትና የሕዝብ እንቅስቃሴዎችን የሚያውኩና የልማትና የኢንቨስትመንት ተግባራትን የሚያደናቅፉትን በጥናትና በመረጃ በመለየት ተገቢ ርምጃ እንዲወሰድም ነው የደኅንነት ምክር ቤቱ የወሰነው።

የምግብና ልዩ ልዩ ሸቀጦች ዋጋ እንዲንር በሕገ ወጥ መንገድ ምርት የሚያከማቹ፣ በኮንትሮባንድ መልክ ነዳጅና ሌሎች ምርቶችን ወደ ጎረቤት ሀገራት የሚያሾልኩ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድም አስታውቋል መግለጫው።

ወላጆች ልጆቻቸውን፣ ሸማግሌዎች ወጣቶችን፣ የሃይማኖት አባቶች ምእመኖቻቸውን፣ የፓርቲ መሪዎች አባሎቻቸውንና የጎሳ መሪዎች ወገኖቻቸውን በመምከር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከግጭትና ከሽብር ራሱን በማራቅ ለሰላምና ለሀገር ደኅንነት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣም ጥሪ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በተቃራኒው ተሰልፎ የሚገኝ ማንኛውም ሰው፣ አካልና ቡድን ላይ ሕጉ የሚፈቅደውን ተገቢውን ሕግና ጸጥታ የማስከበር ሥራ እንደሚሰራ ነው ያስታወቀው፡፡

ለሕዝበ ክርስቲያኑም ሆነ ለሕዝበ ሙስሊሙ የበዓላት ሰሞን እንደመሆኑ፤ አማኞች በትብብርና በመግባባት የጠላቶችን ፍላጎት በማክሸፍና የጋራ ደህንነታቸውን በማረጋገጥ እንደ ሀገር የተሳካ ጊዜያት እንዲያሳልፉም የደህንነት ምክር ቤቱ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡

ትዕግስትም ልክ እና መጠን አለው ያለው መግለጫው፤ አሁን የጸጥታና ደኅንነት ተቋማት አስፈላጊ በሆነ ሰዓት ሁሉ ተመጣጣኝ ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ ከደህንነትና ጸጥታ ጋር የተያያዙ ችግሮች በዘላቂነት እንዲቀረፉ የብዙ አካላት ርብርብና ተናብቦ መሥራትን እንደሚጠይቅም ነው ምክር ቤቱ በመግለጫው የጠቆመው፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ዜጋ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሚዲያና ሌሎች የሕዝብ ዐይን፣ ጆሮና ክንድ ሆነው የሚሰሩ አካላት ከጸጥታ ተቋማት ጋር በቅንጅትና በመግባባት በመሥራት የጸረ ሰላም ሃይሎችን ሴራ ለማክሸፍ ቁርጠኞች መሆን እንዳለባቸውም በመግለጫው ጥሪ ቀርቧል፡፡

የቅዳሜ መጽሄት

# አገልግል



‹‹የሃይማኖት ተቋማት ራሳቸውን በመፈተሽ ራሳቸውንም አገሪቱንም ከጥፋት መታደግ ይጠበቅባቸዋል››

- መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ፣ በቅድስት ስላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮትና የስነልቦና መምህር

ገጽ 6



ከመቀጠር ብዙዎችን ወደመቅጠር

ገጽ 13



ለራስ ምንም ለአገር ደጀን

ገጽ 16

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## ቢሮው ባለፉት ስምንት ወራት ያከናወናቸው አንኳር ሥራዎች

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ ብቃት ያለውና አገልጋይነትን የተላበሰ የሰው ኃይል በመገንባት፣ ፍትሐዊና ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ዕውን አድርጎ ተደራሽ አገልግሎት በመስጠትና ግብርን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ለከተማዋ ዕድገትና ብልጽግና የሚያስፈልጋትን ገቢ በብቃት መሰብሰብ የሚያስችል ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ ይገኛል። ከዚህ አኳያ ቢሮው ተልኮውን ለማሳካት ባለፉት ስምንት ወራት ያከናወናቸውን አንኳር ሥራዎችን በሚመለከት እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።

*** የገቢ አፈጻጸም**

ቢሮው በ2014 በጀት ዓመት በአጠቃላይ 48 ነጥብ 542 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ በእቅድ ይዞ ወደ ሥራ የገባ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ባለፉት ስምንት ወራት ለመሰብሰብ በእቅድ ከተያዘው 34 ነጥብ 63 ቢሊዮን ብር 39 ነጥብ 551 ቢሊዮን ወይም የእቅዱን 116 ነጥብ 11 በመቶ መሰብሰብ ተችሏል።

ይህ አፈጻጸም ከባለፈው በጀት ዓመት በተመሳሳይ ወቅት ከተሰበሰበው 29 ነጥብ 407 ቢሊዮን ብር ጋር ሲነጻጸር የ34 ነጥብ 49 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ ከመቻሉም ባሻገር በ2014 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ በእቅድ ከተያዘው ውስጥ 81 ነጥብ 48 በመቶውን በስምንት ወሩ ማሳካት ተችሏል።

*** ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንፃር የተሠሩ ሥራዎች**

ቢሮው ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ በቁጥር 79 ለሚሆኑ ሠራተኞች፣ ወላጆቻቸውን በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ያጡ ህፃናትና ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች በስምንት ወር ውስጥ 517 ሺህ 600 ብር ከሠራተኞች ደመወዝ በየወሩ እየተቆረጠ የሚዋጣ ገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል። እንዲሁም ቢሮው ለማሳደግ ለተረከባቸው 14 ህጻናት 109 ሺህ 333 ብር ከሠራተኛው ደመወዝ እንዲዋጣ በማድረግ ድጋፍ ተደርጓል።

ከዚህ ባሻገር 24 ለሚሆኑ የዘጠነኛ እና አሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ ወጪያቸውን በመሸፈን ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ ተችሏል። በተጨማሪ ዲፕሎማ 12፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 29፣ ሁለተኛ ዲግሪ 203 በድምሩ 244 ሠራተኞች ደግሞ ከ20 እስከ 50 በመቶ የትምህርት ወጪ ቅናሽ ተደርጎላቸው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ተደርጓል።

በሌላ በኩል የቢሮው ሠራተኞች ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ቃል በገቡት መሠረት አሥር ሚሊዮን 557 ሺ 578 ብር ለግድቡ ግንባታ አስተዋጽኦ ተበርክቷል። እንዲሁም በቢሮ ደረጃ ለአገር መከላከያ ሰራዊት 39 ሚሊዮን 661 ሺ 422 ብር ድጋፍ ለማድረግ ቃል ተገብቶ ድጋፉ እየተደረገ ይገኛል። ከዚህ ባለፈ የቢሮው አመራሮች እና ሠራተኞች በአማራ እና አፋር ክልሎች በጦርነቱ ለተጎዱ ወገኖች ከ13 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የምግብ፣ የአልባሳት እና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ድጋፍ አድርገዋል።

*** ተቋማዊ ቅንጅትን ለማጠናከር የተሠሩ ሥራዎች**

ከመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) ጋር በቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመናዊ አሠራር ለመተግበር እና ተቋሙ እየተጠቀመባቸው የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ደህንነት ለማረጋገጥ በቅንጅት እየተሠራ ይገኛል። በሌላ በኩል በትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርትና ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ማዕከል ጋር በመተባበር ተማሪ ተኮር የአስተምህሮ ሥራ ለመሥራት የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ወደ ተግባር መግባት ተችሏል።

ከዚህ ባሻገር በገቢ አሰባሰቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካላቸው የከተማ አስተዳደሩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች፣ ከፍትሕ አካላት (ጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ የፌዴራል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን)፣ ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ጋር በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ በቢሮው ኤፍ ኤም ሬዲዮ 94.7/"94.7 FM" ጣቢያ በግብር (ታክስ) ዙሪያ ቋሚ መርሃ ግብር እንዲዘጋጅ ስምምነት ላይ በመድረስ በታክስ ጉዳይ ላይ አዲሱን ትውልድ የመገንባት ሥራዎች ለመሥራት የሚያስችል የሁለትዮሽ ስምምነት በመፈራረም ወደ ሥራ ተገብቷል። ሌላው ከቴክኒክ ሙያ ሥልጠና እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የዘመናዊ የቢሮ አስተዳደር ሥርዓት (Smart office management system) ተጠቃሚ ለመሆን ስምምነት ላይ ተደርሶ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል እድል መፍጠር ተችሏል።

*** ተቋማዊ የተግባቦት (Communication)**

ተቋማዊ የተግባቦት (Communication) በመደበኛ የመገናኛ ዘዴዎች በተለይ ከዋልታ ቋሚ የአየር ጊዜ በመግዛት፣ በልዩ ልዩ የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎች (Face-book, you tube, Twitter, Telegram)፣ በቢሮው ድረ ገጽ (Webpage) እንዲሁም ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የተቋሙን ሁነቶች እና በግብር (ታክስ) የሕግ ማዕቀፎች ዙሪያ አያሌ መልእክቶችንና ትምህርታዊ ጽሑፎችን በተደራጀ ሁኔታ ማስተላለፍ ተችሏል። እየተላለፈም ይገኛል።

*** የበጎ ሥነ-ምግባር መገንቢያ ንቅናቄ**

በቢሮው የሚስተዋሉ የሌብነት አመለካከትና ተግባራትን ከመከላከል አንጻር የበጎ ሥነ-ምግባር መገንቢያ የንቅናቄ ሰነድ በማዘጋጀት ዋና መስሪያ ቤቱን ጨምሮ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የሚገኙ አመራሮች፣ ሠራተኞች እና ከአጠቃላይ ግብር ከፋዩ አሥር በመቶ (ከ41 ሺ) በላይ የሚሆኑ ግብር ከፋዮችን የሚያሳትፉ መድረኮች በማከናወን ችግሩን ለማቃለል የሚያስችሉ ተጨባጭ ግብዓት ማግኘት ተችሏል።

*** አገልግሎት አሰጣጥ ከማሻሻል አንጻር**

ግብር ከፋዩ የሚያገኘውን የአገልግሎት ዓይነት እና የአገልግሎት ስታንዳርዶችን የያዘ የተገልጋይ ቻርተር ለሦስተኛ ጊዜ በማሻሻል አሳትሞ ለግብር ከፋዩ እንዲደርስ በማድረግ ላይ ይገኛል። እንዲሁም ቢሮው የግብር ከፋዩን ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ጉልበትና ወጪን ሊቀንሱ የሚችሉ አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶችን ሥራ ላይ በማዋል ላይ ሲሆን፤ በ2013 በጀት ዓመት የግብር ማስታወቂያ ወቅት አዲስ በማልማት ሥራ ላይ እያዋለ በሚገኘው "ET-tax" የቴክኖሎጂ ውጤት 213 ሺ 523 የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች በአጭር የጽሑፍ መልዕክት ግብራቸውን በማስታወቅ እንዲከፍሉ ማድረግ ተችሏል። በቀጣይ ደግሞ የደረጃ "ሀ" እና "ለ" ግብር ከፋዮችም በሚለማው የቴክኖሎጂ ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል።

በሌላ በኩል ግብር ከፋዩን በሕግ ተገዥነቱ በመለየት ቤት ለቤት በመጎብኘት እውቅና የመስጠት እና የማበረታታት ሥራ በመሥራት በቢሮው እና በግብር ከፋዩ መካከል ጤናማ ግንኙነት ለማጠናከር የሚያስችል ተግባር እየተከናወነም ይገኛል።


**አድራሻ፦**

ስልክ የቢሮ ኃላፊ 0115575790
የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741
የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608
የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O. Box 27400 code 1000


**የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!**

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የሃይማኖት ተቋማት ራሳቸውን በመፈተሽ ራሳቸውንም አገሪቱንም ከጥፋት መታደግ ይጠበቅባቸዋል››

*- መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ፣*
*በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ መለኮትና የስነልቦና መምህር*

ማህሌት አብዱል

**የተወለዱትና ያደጉት በቀድሞው አጠራር አሩሲ ክፍለ አገር ዴራ አማኑኤል ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሲሆን፤ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ዴራ አማኑኤል እንዲሁም አሰላ መለስተኛ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል፡፡ በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በነገረ-መለኮት (ቲዮሎጂ) የሰሩ ሲሆን፤ በአልፋ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርነት ዲፕሎማ አግኝተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፊሎሎጂ፤ ካውንስሊንግ ሳይኮሎጂ፤ በትምህርት አመራርና አስተዳደር የትምህርት መስኮች ሶስት ማስተርሶችን መስራት ችለዋል፡፡ እንዲሁም ከቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በድህረ- መረቃ ዲፕሎማ ሀገረ በቀል ነገረ-መለኮት እና ሲስተማቲክ ነገረ-መለኮት ተጨማሪ ማስተርስ ማግኘት ችለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአገር ውስጥ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡**

**በደብረሊባኖስ ገዳም ለአስር ዓመት ያህል በትምህርትም በአገልግሎትም የቆዩት የዛሬው የዘመን እንግዳችን፤ ወደ አዲስ አበባ ከተመለሱ በኋላም በ1999 ዓ.ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት አዘጋጅነት ለአንድ ዓመት ያህል ቀርቦ በነበረው የሚሊንየም አውደ ርዕይ ላይ ለዘጠኝ ወራት አገልግለዋል፡፡ በኋላም በስብከተ ወንጌል አያት ኪዳነ ምህረት፣ ቀበና ኪዳነ ምህረት፣ ቁስቋም ማርያም፣ እየሱስ፣ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን አገልግለዋል፡፡ ሰወስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ የንፅፅር ነገረ መለኮት በመምህርና በአሰልጣኝነት ሰርተዋል፡፡ በተጨማሪም ሀዋሳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በአስተዳዳሪነት አገልግለዋል፡፡**

**በአሁኑ ወቅት በቅድስት ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የነገረ-መለኮትና የስነልቦና መምህር እንዲሁም፤ ደብረአሜን መርካቶ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን በስብከተ-ወንጌል እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ እኚህ አባት መላከምህረት ቆሞስ አባ ጌዴዎን ብርሃነ ይባላሉ፡፡ አዲስ ዘመንም የትንሳኤ በዓልን ምክንያት በማድረግ እንግዳ አድርጎ ያቀረባቸው ሲሆን፤ ከእንግዳችን ጋር ያደረግነውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡**



ፎቶ፡- አዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ከመንፈሳዊ ትምህርቱ ጎን ለጎን በቀለም ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ እንዴት ሊደርሱ እንደቻሉ ያስረዱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አባ ጌዴዎን፡-** ለእኔ እዚህ መድረስ ዋነኛ ምክንያት ናት ብዬ የማስበው እናቴን ነው፡፡ እናቴ አባቴን ያገባችው የተማረ ሰው ስለሆነ የመማር ፍላጎቷን ያሳካልኛል፤ ያስተምረኛል በሚል ሃሳብ ነው፡፡ በዚያ ጊዜ እንዲያውም ‹‹የኛ ሙሽራ አገባች አስተማሪ›› ሲባል እየሰማች ስላደገችና ህብረተሰቡም ለመምህርነት ትልቅ እሳቤ ስለነበረው አባቴ ህልሟን እንደሚያሳካላት ፅኑ እምነት ነበራት፡፡ ግን እንዳሰበችው ሳይሆን ቀረ፡፡ አባታችን በተለያየ ምክንያት ከተለየ በኋላ ነው ከመጀመሪያ ልጇ ጋር ትምህርት ቤት አብራ የገባችው፡፡ እስከ አራተኛ ክፍል ከተማረች በኋላ ግን እንዳልኩሽ አባታችን ስላልነበር ሶስት ልጆችን ይዛ ሕይወት በቀላሉ የሚገፋ አልሆን አላት፡፡ በመሆኑም ትምህርቱን ጥላ ወደ ንግድ ዓለም ገባች፡፡ እናም ገና እንጭጭ በሆነው ማንነታችን ውስጥ የእናታችን ፍላጎትና ጉጉት ሳናስበው ውስጣችን ተቀርጾ ነበር፡፡ በተለይ እኔ የእሷን ህልም ማሳካት አለብኝ ብዬ ነው የተነሳሁት፡፡ አሁንም ላይ ሆኜ ሳስበው የእሷ ህልም ወደ እኔ የተጋባ ነው የሚመስለኝ፡፡

ከዚሁ በተጓዳኝ ከልጅነቴ ጀምሮ እግዚአብሔርን የማገልገል ፍላጎት ነበረኝ፡፡ እናቴ ‹‹ውለድ፤ ክበድ›› ብላ ስትመርቀኝ አይ እኔ መነኩሴ ነው የምሆነው እላት ነበር፡፡ ከህፃንነቴ ጀምሮ በመንፈሳዊ ነገር የመስፋት ፍላጎቴ እያየለ መጣ፡፡ እና እነዚህ ሁለቱ ህልሞቼ እንደሰው መነሻ ምክንያቶቼ ናቸው ብዬ ባምንም፤ ከዚያ በላይ አገልጋይ የሆንኩት በእግዚአብሔርም ጥሪ ይመስለኛል፡፡ ይህንን ስልሽ ግን በእዛ እድሜዬ ሁሉንም ነገር አገናዝቤ፤ ጉዳት ጥቅሙን ለይቼ አይደለም፤ ግን ለአምላኬ መገዛትና የማገልግል ፅኑ መሻት ነበረኝ፡፡ ነፍስ ካወቁኝ በኋላ ደግሞ ይህ መሻቴ እየጎለበተ ሄደ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሀዋሳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በአስተዳዳሪነት በሰሩበት ወቅት አንድ ፈታኝ ችግር አጋጥሞት እንደነበር ሰምተናል፡፡ እስቲ ስለነበረው ሁኔታ ያብራሩልን?**

**አባ ጌዴዎን፡-**ሀዋሳ ቅዱስ ገብርኤል በአስተዳዳሪነት በተመደብኩበት ጊዜ እንደምታስታውሱት በሲዳማና ወላይታ ማህበረሰቦች መካከል ግጭት ተፈጥሮ ነበር፡፡ ያንን ግጭት ለማርገብ የአገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት አባቶች የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ስናደርግ ነበር፡፡ በእርግጥም የሽማግሌዎቹ ሚና የማይተካ ነበር፡፡ ግጭቱ በከፍተኛ ደረጃ በተፋፋመበትና በርካቶች እየሞቱ በነበረበት ቦታ ሁሉ በድፍረት እየገባን ሰዎችን እያረጋጋን ነው የነበረው፡፡ የነበረው ሁኔታ በጣም የሚያስፈራና ጭካኔ የተሞላበት፤ እኔ በተለይ የጭካኔንም ልክ ሳልፈልግ በሕይወቴ ያየሁት ያኔ ነው፡፡ ለሚዲያ የማይመጥኑ በጣም አሳዛኝ ነገሮች ነው ያየነው፡፡ ወደየት እየሄድን እንደሆነ የሚያስደነግጥ ሁኔታ ነው የተፈጠረው፡፡ እነሱ መንገድ እየዘጉና ሰው እያቃጠሉ ባለበት ጊዜ እኛ ብንሞትም እንሙት ብለን ነው ወደ እሳቱ ስንገባ የነበረው፡፡

በተለይ እኔ መስቀል ይዤ ስቆም ‹‹የእግዚአብሔር ሰው ይለፉ›› ይሉኝ ነበር፡፡ ይህም የሚያሳይሽ የእግዚአብሔርን ድንቅ ስራ ነው፡፡ ምክንያቱም በእምነት አንመሳሰልም፤ ግን አክበረውኝ እንድገባ ይፈቅዱልኝ ነበር፡፡ እሳት ብቻ ሳይሆን ነገር እንደ እሳት የሚነድበት ሁኔታ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ክብርና ሞገስ ሆኖን የተጋጩትን ወገኖች እስከማስታረቅ ደርሰናል፡፡ በዚህም የክልሉ መንግስት ከፍተኛ ድጋፍ አድርጎልናል፡፡ የሰላም ሚኒስቴሯና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድረስ ላበረከትነው አስተዋፅኦ እውቅና ተሰጥቶናል፡፡ በዚያ ላበረክትነው አስተዋፅኦ ‹‹የማይተካ ሚና የሚል ሰርተፍኬት›› ከመንግስት አግኝተናል፡፡

ስለዚህ ሀዋሳ ተፈጥሮ በነበረው ግጭት በአጠቃላይ ሕዝባችን ወዴት እየሄደ እንደሆነ እንድንጠይቅና ሁኔታው ምን ያህል ወደ ጭካኔ እየተለወጠ እንደሆነ እንድናይ አድርጎናል፡፡ በተለይ እኔ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ምን አይነት ትውልድ ነው እያፈሩ ያሉት? የሚል ጥያቄ ፈጥሮብኛል፡፡ የደቡብ አፍሪካ አንድ ዩኒቨርሲቲ ላይ ‹‹አንድን አገር ለማፍረስ ከፈለግህ ረጅም ተወርዋሪ ሚሳኤል አታምርት፤ ትልልቅ ቦንቦችንም አትስራ፤ ይልቁን ስርዓተ ትምህርቱን አበላሽ›› ይላል፡፡ ምክንያቱም ከዚያ የሚወጡ ዳኞች ፍትህን ያዛባሉ፤ ከዚያ ተመርቀው የሚወጡ ዶክተሮች በእጃቸው ህሙማን ይሞታሉ፤ በአካውንታንቶች ገንዘብ ይመዘበራሉ፤ በእምነት መሪዎች ወገንተኝነት ይሰበካል፡፡ ቶሎ አገርን ለማጥፋት ከቦንብና ከሚሳዔል ይልቅ ስርዓተ ትምህርትን ማበላሸት ከፍተኛ ውድቀት እንደሚመጣ ነው በዚህ ፅሁፍ ለመግለፅ የተሞከረው፡፡ ልክ እንደዚያ ሁሉ በእኛም አገር አሁን ለተከሰተው ችግር ዋነኛ መንስኤ ነው ብዬ ነው የማምነው፡፡

በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ተማሪዎች እንዴት? እና ለምን? ጠበቡ የሚለው ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን ሃይማኖተኞች ሆነን ሰላን ከእምነታችን አስተምሮ ውጭ ዘረኝነትን ጎጠኝነት ልንስፋፋ ባልተገባ ነበር፡፡ በዩኒቨርሲቲም ደረጃ ልዩነቶቻችን ላይ እንድናተኩር ተደርገን ነው የተቀረጽነው፡፡ 85 ቋንቋ መናገራችን ለመግባቢያ እንጂ እርስበርስ መለያያና የግጭት ምክንያት ሊሆነን ባልተገባ ነበር፡፡ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያሉ ምሁራን ይህንን እንዴት መገንዘብ እንዳቃታቸው አይገባኝም፡፡ የምንማረው እኮ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት ነው፡፡ ትምህርት የመዳረሻ ግቡ የጠራ አመለካከት ማምጣት ነው፡፡ ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎቻችን እያመረቱ ስላለው ትውልድ ትኩረት ሊሰጠውና መፈተሽ አለበት የሚል እምነት ነው ያለኝ፡፡

ሁለተኛው፣ ሕዝባችን ይህንን ያህል ለምን ተጨካከነ? የሚለው ነገር ያሳስበኛል፡፡ የእለት ምግባቸውን እንኳን በልተው በማያድሩ ምስኪኖች ላይ ጦር የመስመበቁ ዓላማም እስካሁን ድረስ ግልፅ አልሆነልኝም፡፡ ከዚያ የሚገኘው ትርፍም አልገባኝም፡፡ ሌላው ዋነኛው ነገር ግን ሁላችንም ከበረታን ሥራ መስራት እንደምንችል እረዳለሁ፡፡ ለምሳሌ፣ ሀዋሳ በነበርኩበት ጊዜ በትህትና ተቀብሎኝ ሲያስተናግደኝ የነበረው በእምነት ከእኔ ጋር የማይመስለው ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ክብር ሰጥተውኛል፤ ስቸገር በችግሬ ሁሉ ገብተው ስራዬን በብቃት እንድወጣ ከአጠገቤ አልተለዩኝም፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ አገሪቱ ከገባችበት ችግር ለመታደግ የምንችልበት እድል አለ ብዬ እንዳስብ አድርጎኛል፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለይ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ራሳቸውን መፈተሽ አለባቸው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ህብረተሰቡ በዚህ ደረጃ ሊጨካከን የቻለበትን ምክንያት መመርመር ይገባናል፡፡ እንዳልኩሽ ግን ከተሰራ ለውጥ ማምጣት የማንችልበት ሁኔታ የለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የወገንተኝነትና ጎጠኝነት ችግር በቤተ እምነቶች ውስጥም ጎልቶ እየታየ ነው ያለው፡፡ ለመሆኑ የዚህ ምክንያት ምንድነው ያለው?**

**አባ ጌዴዎን፡-** እውነት ነው፤ ግን እንደሚታወቀው ክርስቶስ ምድር ላይ ሳለ 12 ሐዋሪያቶች ነበሩ፡፡ ግን ከእነሱ አንዱ የሆነው ይሁዳ ከክርስቶስ ሃሳብ ጋር አልነበረም፡፡ ይሁዳ ከገንዘብ ፍላጎቱ የተነሳ የማይገዛውን አምላክ በብር እስከመሸጥ፤ የማይለወጠውን ፈጣሪ በገንዘብ ሲለውጥ ታያለሽ፡፡ ክርስቶስ ራሱ ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም ብሎ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ከ12 ሐዋሪያት አንዱ ይሁዳ ነው፡፡ በተለይ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ቁጥር 70 ላይ ‹‹እኔ መረጥኳችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፤ ከመረጥኩት አንዱ ግን ፍፁም ዲያቢሎስ ነው›› ይላል፡፡ ከዚያ የምንማረው በክርስቶስ ከተመረጡትና ከተማሩት ከሁሉም ሐዋሪያት መካከል አንዱ ዲያቢሎስ ከሆነ አሁን ያለነው የመንፈሳዊ አባቶችም ፍፁም ልንሆን እንደማንችል ነው፡፡

በሌላ በኩል ይሁዳም ሆነ ሁሉም ሐዋሪያት ንፁህ ቢሆኑ ኖሮ ሰው ሁሉ በዳኝነት ጣልቃ እየገባ ከአሁኑ የባሰ ችግር ውስጥ በገባን ነበር፡፡ እንደእኔ አላሰብሽም ማለት አንቺ መጥፎ ነሽ ማለት አይደለም፡፡ አንቺ የምታይበት አቅጣጫ ሌላ ነው፤ እኔም የማይበት የተለየ ነው፡፡ ክርስቶስ ይሁዳን ቢያስወግደው ኖሮ አሁን ላይም እንደእኔ አላሰብክም ብለን የምናስወግደው አካል ይበዛ ነበር፡፡ ሁሉንም ነገር በእኛ ሚዛን የምንመዝን የሃይማኖት መስፈርቱ ከእነአካቴው ይበላሽ ነበር፡፡ ስለዚህ ልክ እንደይሁዳ አይነት ሰዎች በመካከላችን ሊኖሩ ይችላሉ፤ ልክ እንደእሱ በአቋራጭ ሊከብሩ የሚፈልጉም አይጠፉም፡፡ እንግዲህ ከቅዱሱ መምህር ስር የተማረው ይህ ሃዋርያ እንዲህ ከሆነ አሁን ካለነው መምህራን ውስጥም ሁላችንም እንደክርስቶስ ቅዱሳን ልንሆን አንችልም፡፡ ምክንያቱም የሰው ንፁህ የለውም፡፡

በዚህ እሳቤ መሰረት ብዙ ነገሮች ዓላማቸውን እየሳቱ እየመጡ እናያለን፡፡ አሁን ያለው ውጤት መነሻው መሰረቱ እሱ ነው፡፡ የሰው ልጅ ከአዳም ጀምሮ ነፃ ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ አዳም የተከለከውን ፍሬ የበላው ነፃ ፈቃድ ስለተሰጠው ነው፤ ይሁዳም ክርስቶስን የሸጠው ነፃ ፈቃዱን ተጠቅሞ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች አሁንም ክፉ ማድረግም፤ ነፃነትም ለእነሱ የተተወ ነው፡፡ የሃይማኖት አባት ሆነሽ ሃይማኖቱ የሚያዝሽን ብቻ መስራት የአንቺ መብት ነው፤ ሃይማኖትሽን ሽፋን አድርገሽ ክፉ ነገር መስራትም የአንቺ መብት ነው፡፡ ለሁሉም የመጨረሻ የዳኝነት ፍርድ አለ፡፡ እስከዚያ የፍርድ እለት በሁሉ ነገር ጣልቃ አይገባም፤ ምክንያቱም የነፃነት አምላክ ነው፡፡

አሁን ላይ የሚያጠያይቀው ነገር ለምን እንከን ኖረ አይደለም፤ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ ከእንከን የተለየችበት ጊዜ የለም፡፡ ግን ደግሞ እንከኑ ለምንድን ነው ጎልቶ የወጣው? የሚለው ነገር በእውነት ያነጋግራል፡፡ መጠየቅ ያለብንም ይህንኑ ነው፡፡ አሁን ላይ በተለይ የአውሮፓውያኑ እሳቤ በስርተ-ትምህርት በኩል በቀጥታ ለዘመናት የቆየውን አገራዊ እሴት አስወግዶ የራሱን መሰረት ጥሏል፡፡ አይደለም ለሺ ዓመታት የቆየው እሴት ለጥቂት ዓመታት የነበረውን ስርዓተ ትምህርት በአንድ ጊዜ ተነቅሎ ሌላ ሲተካ የሚፈጠረውን የትውልድ ክፍተት ምን ያህል ችግር እንደፈጠረ አይተናል፡፡ አሁንም የነበረው መንግስት ሲቀየር እየተከፈለ ያለውን ዋጋ እያየን ነው፡፡ የነበረን በአንድ ጊዜ ማስወገድ በሕዝቦች መካከል መተማመን ላይፈጥር ይችላል፤ መረጋጋት ይጠፋል፤ በሚታየው ነገር አለማመን ሊመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ ከብዙ ነገር አንፃር በመሃል የሚፈጠረው ክፍተት ቀላል አይደለም፡፡ ነባሩ ስርዓተ ትምህርታችን ምዕራብውያንን ማዕከል ወደ አደረገው ስርዓት በመቀየሩ አንደኛ የኢትዮጵውያን የሕይወት ፍልስፍናቸው እንዲጠፋ ሆኗል፤ ከሁሉ የባሰው ደግሞ ራስን ማጣታችን ብቻ ሳይሆን እነሱንም በቅጡ መምሰል አለመቻላችን ነው፡፡ ይሄም በመሃል የሚወላውሉ ሰዎች እንዲፈጠሩ አድርጓል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ በእምነት ተቋማቱ ላይ የሚታየው ያልተገባ አሰራር የሚመነጨው**

**ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች**

# የዘመን እንግዳ

**በምዕራብውያኑ ተፅዕኖ ነው እያሉ ነው?**

**አባ ጌዴዎን፡-** በትክክል፤ የሚገርምሽ የእነሱ ተፅዕኖ ትምህርት ስርዓቱንና ባህላችንን ከመቀየር ባለፈ ሌላው አውሮፓውያኑ የራሳቸውን ሃሳብ ለማስረፅ ያደረጉት ነገር እምነትን መበረዝ ነው። የሕዝቡን መንፈሳዊ ልዕልና የመምታት አጀንዳ ይዘው ነበር ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት። ይህንን የምልሽ ዝም ብዬ አይደለም፤ በመረጃ ላይ ተደግፌ እንጂ!። በራሳችን የምንተማመንባቸውን ነገሮች ሁሉ ስንጥል እነሱ እንደፈለጉት ለዘላለም የእነሱ ባሪያ እንድንሆን ያደርጉናል። እነሱ እኛ እንድናድግ ፈፅሞ አይፈልጉም፤ በእነሱ እሳቤ ነፃ የሚባል ነገር የለም፤ የሚሰጡን ብድርና እርዳታም ከበስተጀርባው ሌላ ድብቅ ሴራ ያለው ነው። እኛ ለጊዜው ያለብንን ችግር መወጣታችን እንጂ ከስጦታው በኋላ ሊመጣብን የሚችለውን ነገር አናየውም። ነፃ የትምህርት እንኳን የሚሰጡን የእነሱን አስተሳሰብ በእኛው ሰዎች ልቡና ለመጫን ነው። ምዕራብውያን በጣም በጥንቃቄ ነው አላማቸውን የሚያሳኩት። የሃይማኖት አባቶችን ሳይቀር በዚህ እሳቤ ውስጥ እንዲጠለፉ አድርገዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በመንግስታዊውም ሆነ በሃይማኖት ተቋማት የአገልጋይነት መንፈስ እየቀነሰ መምጣት፤ በምትኩ ሙሰኝነትና ኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ እየጎለበተ የመጣበት ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ? በተለይ የእምነት ተቋማት ለሌሎች አብነት መሆን ሲገባቸው የዚሁ ችግር አካል እንዴት ሊሆኑ ቻሉ?**

**አባ ጌዴዎን፡-** ይህ የዘመናችን አስደንጋጩ ችግር ነው!። ለምን አስደንጋጭ ሆነ? ካልሽኝ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ በሃይማኖት ስር ያሉ አካላትን ገንዘብን ማዕከል አድርገው መስራት በመጀመራቸው ነው። አንቺም ብትሆኚ በተለይ ስለሃይማኖት ተቋማቱ ችግር ያነሳሽልኝ የተጨበጠ መረጃ ስላገኘሽ ይመስለኛል። ያነሳሽው ችግር በተግባርም ይኖራል። በመሰረቱ ዘረኝነት ራሱ ሙስና ነው። ሃይማኖቱ የማይፈቅደውን ሥራ መስራትና በተቃራኒ አስተምህሮ መቆሙም ሙስና ነው። ሰዓት አለማክበር ሊሆን ይችላል፤ የማይገባሽን ቃል ሳይቀር መናገር ሙስና ነው። እንደአጠቃላይ የእከሌ ሃይማኖት ሳልል ሁሉም ላይ የምታዘበውን ነገር ነው የምነግርሽ። በዚህ ረገድ አገራችን አስደንጋጭ ሁኔታ ላይ የቆመችበት ጊዜ ላይ ነን። አንዳንዱ በረቀቀ መልክ ያደርገዋል፤ አንዳንዱ ደግሞ በግልጽ ያደርገዋል። ልዩነቱ የድርጊቱ ግልፅ መሆንና አለመሆን ካልሆነ በስተቀር ይህ ጉዳይ አሳሳቢ ከሆኑ ችግሮች መካከል ዋነኛው ነው። ይህም የሆነው አለማዊነት (secularism) በመስፋቱ ነው።

በተለይ ከ1739 ዓ.ም በኋላ ድህረ-ዘመናዊነትና ዘመናዊነት የሚል አስተሳሰብ መጥቷል። ይህ አስተሳሰብ ትልቁ ዓላማው ግላዊነትን ማሳደግ ነው። ለሰዎች ዋጋ ከመክፈል ይልቅ ለራስ መቆምንና ለራስ ብቻ መኖርን ነው የሚያበረታታው። ይህ አይነቱ ፍልስፍና የመጀመሪያ ዓላማው ደግሞ የሃይማኖትን እሳቤ መምታት ወይም መበረዝ ነው። ከዚያ ጊዜ ወዲህ የመጣው ትውልድ የዚያ ችግር ሰላባ ነው የሆነው። በአጠቃላይ የምዕራብውያኑ አስተሳሰብ ነው በእምነት ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ገብቶ እንደሚገባን ሕዝብን እንዳናገለግል ያረገን።

**አዲስ ዘመን፡- ግን ለሁሉም ችግራችን ምዕራብውያንና የምዕራብውያንን ፍልስፍና ማድረጉ ምን ያህል አሳማኝ ነው? በተለይ አሁን ላይ ለተስፋፋው ሌብነት እነሱን ተጠያቂ ማድረግ ይቻላል?**

**አባ ጌዴዎን፡-** እንዳልሽው ሁሉንም ጥፋት በምዕራብውያኑ ላይ አላክን ራሳችንን ነፃ ለማድረግ ይመስላል። ግን እስኪ ራሳችንን ከማየታችን በፊት በገጠር ያለውን ማህበረሰብ እና በከተማ ያለውን ከፋፍለን እንይ። ከዚህ አንፃር የምዕራብውያን እሳቤ ለማን የበለጠ ተደራሽ እንደሆነ ለማወቅ ብዙ ርቀት መሄድ አያስፈልግም። በአንድም በሌላም የከተማው ማህበረሰብ የበለጠ የምዕራብ አስተሳሳብ ተፅዕኖ ያደረበት ነው። ገጠር ላይ የምታየውን ኢትዮጵያዊ ጨዋነት አዲስ አበባ ላይ አታገኚውም። ሙስናውን ብታይ ጎልቶ የሚታየው ከተማ ላይ ነው። ገጠር ያለ አንድ ቄስ በየቀኑ ከስድስት ሰዓት በላይ ሲያገለግል ቆይቶ መቅደስ ገብቶ ካህን ሆኖ ሲያገለግል ያመሻል። ገጠር ያለው ካህን በነፃ ጉልበቱን ይሰጣል። ሌላው ደግሞ ለሚሰጠው አገልግሎት እየተከፈለውም በዚያም አረካ ብሎ ያልተፈቀደለትን ነገር የሚወስድ ከሆነ፤ ይህ የአስተሳሰብ ክፍተት ሊመጣ የቻለው ከምንም ሊሆን ይችላል?፤ አስተሳሰቡ በመበረዙ ነው። በዘመናዊነት ሰበብ ሰዎች የራሳቸውን ጨዋ ልዕልና የልብ ንፅህና አጥተውታል።

ሉዓላዊነት በአስተሳሰብ ዓለምን በኢኮኖሚ አንድ



የማድረግ ዓላማ እንዳለው ቢነግሩም ዋናው እሳቤ ግን ሌላ ነው። እነሱ በአስተሳሳብ በመቅደማቸው ተፅዕኖ አሳድሮብናል። ግን ዋናው ጉዳይ በእነሱ ተፅዕኖ ስር መሆናችን ሳይሆን ከተፅዕኗቸው ስር ፈንቅለን መውጣት ያለመቻላችን ነው። ይህ ለእኔም የዘመናት ያልተመለሰ ጥያቄ ነው። በአብዛኛው ጊዜ አርዓያ የምናደርጋቸው ሰዎች በእነሱ እሳቤ የተቃኙ ሰዎችን ነው። ስለዚህ ከእነሱ ጫና ፈንቅሎ ለመውጣት እንቸገራለን። አሁን ላይ ብዙ አገራት እያሉ የአሜሪካ፤ የራሺያና የቻይና ትኩረት እኛ ላይ የሆነው ኢትዮጵያ ላይ ያዩት ነገር ስላለ ነው። እነሱ በያሉበት ሆነው በሳተላይት እኛን መቆጣጠር የሚያስችል አቅም ኖሯቸው ሳለ የእኛ ድህነት ናፍቋቸው ወይም ውበታችን ከሌላው በተለየ አምሯቸው አይደለም፤ ይልቁንም አንድም የጂኦፖለቲካ ጉዳይ ነው፤ ሁለተኛው የአፍሪካ ቀንድ ስትራቴጂክ አገር በመሆንዋ ነው። ያላት የተፈጥሮ ሃብትም የእነሱን ትኩረት ከሚስቡ ነገሮች መካከል ናቸው።

እንደ እኔ እምነት ከዚህ ሁሉ በላይ በመንፈሳዊ ዓለም የሚታይ ምስጢር ስላለ ነው። እኛ ፈጣሪ ራሱ ዓላማ ያለባት አገር ናት ያለችን። ለምሳሌ የአሜሪካ ከተሞች በተደጋጋሚ በአውሎ ንፋስ የሚጠቁት ከራስ ዳሸን በሚመጣ ንፋስ ነው። ትራምፕ ይህንን ተራራ በቦንብ መምታት አለብን ሲል እንደነበር የቅርብ ትዝታችን ነው። ይህ በመንፈሳዊ ዓለም ብዙ ሚስጢር አለው። ግን አሁን ላይ በመረጃ ላይ ብቻ በሚያምን ትውልድ ውስጥ በመንፈሳዊ ያለን መረዳት ሁሉ ለማሳመን ጊዜ መፍጀት ነው የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ እየጎላ የመጣው በተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት አለመግባባት እንዲሁም ውስጣዊ ችግር መንስኤና መፍትሔያቸው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አባ ጌዴዎን፡-** የመጀመሪያው ችግር የሃይማኖት ተቋማት እንደተቋም ያላቸውን ራዕይ ለማሳካት ቁርጠኝነት ያለመኖሩ ነው። ምክንያቱም ራዕያቸው የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ ነው። አሁን ላይ በብዛት የምናስተውለው ተልዕኮ እና ዓላማ ላይ ያለማተኮር ችግር ነው። ይህ ደግሞ ፅኑ የሆነ ማንነት ካለመኖር የሚመነጭ ነው። በተጨማሪም ለእምነቱ ያለመስጠት እና መንፈሳዊነት እጦት ውጤት ነው። የቱንም ያህል እውቀትና ጥበብ ቢኖርሽ መንፈሳዊነት ከሌለሽ ከንቱ ነሽ። በእውነትና በጥበብ ብቻ የእግዚአብሔርን መንግስት ሳይሆን ዓለምን አናተርፍ። አሁን ላይ በሃይማኖት ሰዎች ላይ የሚታየው ችግር ከመንፈሳዊነት የራቁ እንቅስቃሴዎች ነው። የሃይማኖት ተቋማት የተመሰረቱበት ዋነኛ ዓላማ ይዘው መዝለቅ ያልቻሉት መንፈሳዊነታቸውን በመተዋቸው ነው። እግዚአብሔርን ማዕከል ያላደረገ ሕይወት ከስጋ ትርፍ አያልፍም።

ስለዚህ የሃይማኖት አባቶች የተሰጣቸውን ሰማያዊ ሃላፊነት ማለትም ብልሃትን፣ እውቀትን፣ ጥበብን፣ ክህሎትን እና መንፈሳዊነት ይዘው ነው ማገልገል የሚገባቸው። እያንዳንዱ አገልጋይ እነዚህን ነገሮች አሟልቶ ካልያዘ ውጤታማ አይሆንም። አመራርነት ደግሞ ቁርጠኝነትና ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል። ራስሽን እንደሻማ አቅልጠሽ ለሌላው ብርሃን የምትሆኚበት እንጂ የምትከበሪበት አይደለም። በተለይ የሃይማኖት መሪዎች እነሱ ሞተው ሕዝቡን ደህና የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው። መሪያችን ክርስቶስ እሱ ሞቶ ለእኛ ሰላምና ደነትን ከሰጠን እኛ የሃይማኖት መሪዎችም የክርስቶስን አርዓያ መከተል ነው የሚጠበቅብን። አሁን ላይ ግን እነሱ ሞተው ሰላምን ከመስጠት ይልቅ ለእነሱ ሲሉ የሌላው መሞት እምብዛም ግድ የማይሰጣቸው ነው።

ይህም የሆነው ከመንፈሳዊነት ጉድለት ነው። መንፈሳዊነት መጽሐፍ ቅዱስ ስለያዝን ወይም ብዙ ስላነበብን አይደለም። መንፈሳዊነት ስለእግዚአብሔር ማወቅን አይጠይቅም፤ ይልቁንም ራሱን እግዚአብሔርን ማወቅን ነው የሚፈልገው። መንፈሳዊነት የሚጠይቀው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርን ነው። ይህ ግን በአሁኑ ወቅት ባሉ የሃይማኖት ሰዎች ዘንድ እምብዛም የማይታይ መሆኑ ነው በእምነት ተቋማት መካከልም ሆነ ውስጥ አለመግባባት እንዲፈጠር ያደረገው። በአንድ ሃይማኖት ውስጥ ሆነው በጎሳና በቋንቋ እርስ በእርስ የሚጣሉ በርካቶች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ከሰማያዊው እግዚአብሔር ይልቅ ጎሳንና ቋንቋን ያስቀድማሉ። ይህም መንፈሳዊነት ያለመኖር ውጤት ነው። ግጭት መፍጠር በሃይማኖት ካባ ውስጥ ሆነው በራሳቸው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ባህሪም ነው።

መፍትሔ ብዬ የምለው የሃይማኖት ተቋማት የቆሙበትን ዓላማ ብቻ ይዘው ራሳቸውን መፈተሽ አለባቸው። ከዚህም በተጨማሪ መንግስት የሃይማኖት ተቋማት ለሰላምና ለአገር እድገት ሚናቸውን እንዲወጡ ሊያግዛቸው ይገባል። ለምሳሌ፣ የሩሲያ መንግስት የአገሪቱ ሃይማኖት ለሚያበረክተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ድጋፍ ያደርግላቸዋል። በተለይ ዜጎችን በትክክለኛ መንገድ ለመቅረፅ ለሚያበረክቱት አስተዋፅኦ በዓመት 128 ቢሊዮን ዶላር ይደጉማቸዋል። እኛ አገር ስንመጣ ግን ይህ አይነቱ ልምድ የለም። በመጀመሪያ ደረጃ የሃይማኖት ተቋማቱ ራሳቸውን ችለው በበጎነት ግባቸው ላይ አተኩረው እንዲሰሩ ነው የሚጠበቀው። በሁለተኛ ደረጃ መንግስት ለትውልድ ቀረፃ አስተዋፅኦ ማበርከት በሚችል መልኩ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል። ድጋፍ ሲያደርግ ግን ተጨባጭ በሆነ፤ አገሪቱን ማዕከል ባደረገ እሳቤ ላይ መሆን አለበት። ምክንያቱም የአገር ጉዳይ በመሆኑ ነው። ስለዚህ የሃይማኖት ተቋማት ራሳቸውን ፈትሸው ራሳቸውንም አገሪቱንም ከጥፋት መታደግ ይጠበቅባቸዋል። ይህ የሚሆነው ደግሞ የተመሰረቱበትን ዋነኛ ተልዕኮ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። በዚህ መርሆ ውስጣቸው የገባውን አለመግባባትና ቅራኔ ሊያስወግዱ ይገባል ባይ ነኝ።

በተለይም ያሏቸውን አገልጋዮች መፈተሽ አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። ይህም ማለት ተልዕኳቸውን መሰረት በማድረግ የሚሄደውና የማይሄደውን መለየት አለባቸው። ይህንን መለየት ካልቻሉ አገርንም ራሳቸውንም ይዘው ነው ገደል የሚገቡት። ስልጠና ለሚያስፈልገው ስልጠና፤ የሙያ ማሻሻያ ለሚያስፈልገው የሙያ ማሻሻያ፤ ድጋፍ ለሚያሻው ድጋፍ በመስጠት፣ መባረር ያለበትንም ማባረር ይገባቸዋል። ይህም ማለት አስተዳደራዊ መፍትሔ ወይም እርምጃ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል ማለት ነው። ለዚህ ደግሞ መንግስት ድጋፍ ማድረግ አለበት። ድጋፍ የሚደርገው ለሃይማኖቱ አይደለም፤ ሃይማኖቱ ለአገር ለሚያበረክተው አስተዋፅኦ ነው። ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ከተፈለገ ዜጎችን በበጎ መንገድ የሚቀርፁ የእምነት ተቋማትን ማገዝ ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የትንሳኤ በዓልን በማስመልከት ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎት?**

**አባ ጌዴዎን፡-** ትንሳኤ ማዕከሉ አዲስ ሕይወት ነው። ያ አዲስ ሕይወት ደግሞ በሙብል ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በአስተሳሰብ ትንሳኤ ላይ የተመሰረተ ነው። ትንሳኤ ተስፋ ያጣ የሰው ልጅ ተስፋ ያገኘበት ቀን ነው። ትንሳኤ ሰዎች እንዲኖሩ ክርስቶስ ራሱን በመስቀል ላይ መስዋት አድርጎ ያቀረበበት እሱም በድል የተጠናቀቀበት የመጨረሻው የሰላም ምዕራፍ ነው። ትንሳኤን ስናስብ መሰረታዊ ዓላማው የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ትንሳኤ እንዲኖረን ልንጓጓ ይገባል። ትንሳኤ ዶሮ መብላት አይደለም፤ ዶሮና ሌሎቹ ግርግሮች ለስጋችን ደስታ ማድመቂያ የነፍሳችን ደስታ ማዕከል አይደለም። ሁሉም የበዓል ዝግጅቶች የእውነተኛው ደስታችን ማድመቂያ ብቻ ናቸው። የደስታው ምንጭና ማዕከል ክርስቶስ ነው። በእኛ አዕምሮ ውስጥ ደግሞ ሞተ አበቃ ያልነው ነገር እንደ አዲስ የተነሳበትና ተስፋ ያገኘንበት ትልቅ ቀን ነው። ስለዚህ ትንሳኤ ተስፋ ያገኘንበት ብቻ ሳይሆን የግፈኞች ሴራ የከሸፈበትና እውነት ጎልቶ የወጣበት ነው። እውነትን ለመቅበር ብዙ ተረባርበዋል፤ እውነት የሆነው ክርስቶስ ግን ሞትና መቃብሩን ፈንቅሎ ነው የተነሳውና ድል ያደረጋቸው። ከዚህ ደግሞ የምንማረው ከግፈኞች ጋር መተባበር ውድቀትን፤ ከእውነት ጋር መቆም ግን እውነተኛ ትንሳኤን እንደሚያስገኝልን ነው። የክርስቶስ መነሳት የሱ ብቻ አልነበረም፤ ክርስቶስን ለሚከተሉት ሁሉ ትንሳኤያቸው ነው።

ይህ በዓል የኢትዮጵያን ትንሳኤ የምናይበት ቀን እንዲሆን ሁላችንም የበኩላችን መረባረብ አለብን። ለእድገቷ እና ለሰላሟ ማነቆ የሆኑ ችግሮቻችንን ተጋግዘን ማስወገድ ይገባናል። ኢትዮጵያ ለሁላችንም በማንም የማትተካ ወርቃችን ጌጣችን፤ ክብራችን፤ ማንነታችን ናት። ስለዚህ እርስበርስ መለያየትና መጋጨታችንን ትተን በአንድ ልብ ለአገራችን መስራት መቻል አለብን። እርስ በርስ እንድንጋጭ የሚያደርጉ ቆሻሻ አስተሳሰቦች አራግፈን ዳግም አገራችን በሰላምም ሆነ በልማቷ ትንሳኤ እንዲሆንላት ሁላችንም የቤት ስራችንን መስራት አለብን። በተለይ ቆሻሻ የሆነውን አመለካከት ከቤታችን ጀምሮ ጠርገን ማውጣት ውስጣችንን ማፅዳት አለብን። በአእምሮ የተፈናቀለ ሰው የተፈናቀለ ሰውን አይረዳም። አሁን ላይ አገራችንን እያተራመሱ ያሉት ከሰውነት አስተሳሳብ የተፈናቀሉ ሰዎች ናቸው። ከበጎ አስተሳሰብ የተፈናቀሉ ሰዎችን በትምህርት፤ በፀሎት የምናግዝበት፤ ከቦታቸው የተፈናቀሉትን፣ የተቸገሩትን ደግሞ ያለንን በማካፈል አገራችንን ከችግር የምትላቀቅበትን ትንሳኤ ማፍጠን ይገባናል። እውነተኛ ትንሳኤ የሚከበረው እቤታችን በምናደርገው የድግስ ልክ ሳይሆን በአስተሳሳብ በመለወጥና ወገኖችን በማገዝና በመደገፍ ነው። ክርስቶስ ስለእኛ ዋጋ እንደከፈለው ሁሉ እኛም በችግር ውስጥ ያሉ ወገኖችን ከችግር ለመታደግ ዋጋ መክፈል ይገባናል። ያለንን በማካፋል የክርስቶስን ፍቅር መግለፅ እንችላለን።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አባ ጌዴዎን፡-** እኔም ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በዓሉ የሰላም፤ የፍቅር እንዲሁም ተካፍለን የምንበላበት ይሁንልን እያልኩኝ፤ እናንተም ለሰጣችሁኝ እድል ከልቤ ላመሰግን እወዳለሁ።

# ማህደረ ጤና

## ጥንቃቄ ለአመጋገብ!

**አስናቀ ፀጋዬ**



ሕዝበ ክርስቲያኑ ለሃምሳ አምስት ቀናት በፆም በፀሎት ቆይቶ እነሆ ነገ ፆመ ልጓሙን ይፈታል። የፋሲካ በዓልም በነገው እለት በመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች በታላቅ ድምቀት ይከበራል። በዓሉ በተለይ ደግሞ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች በኩል በተለየ ሁኔታ ይከበራል።

በዓሉ ከሚከበርባቸው መንገዶች አንዱ ሕዝበ ክርስትያኑ ዶሮ፣ በግ፣ ፍየልና በሬ በማረድ የእነዚህን እንስሳት ስጋ በተለያየ መልኩ በማብሰልና በመመገብ ሲሆን የነዚህ እንስሳት ገበያም በዚህ በዓል ወቅት በተለየ ሁኔታ ይደራል። ምእመኑ ለረጅም ጊዜያት በፆም የቆየና ከቅባታማ ምግቦች የራቀ እንደመሆኑ መጠን ታዲያ እነዚህን የእንስሳት ተዋፅኦዎች ሲመገብ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ በስነ ምግብ ባለሙያዎች ይመከራል።

አቶ ቢራራ መለሰ በጤና ሚኒስቴር የስርአተ ምግብ ባለሙያ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት የፋሲካ በዓል ሲታሰብ በርካታ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከእንስሳት ተዋፅኦና ከቅባታማ ምግቦች ለረጅም ጊዜያት ታቅበው ቆይተው እነዚህን ምግቦች የሚመገቡበት ነው። ሰዎች አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የጥራጥሬ ምግቦችን ሲመገቡ ቆይተው የእንስሳት ተዋፅኦዎችንና ቅባታማ ምግቦችን ወደ መመገብ ሲዞሩ በሰውነት ውስጥ የምግብ መፈጨት ለውጥ ስለሚኖር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህን ምግቦች በብዛት ከመውሰድ ይልቅ በመጠኑ እንዲወስዱም ይመከራል። ቀደም ሲል ሲመገቡ የነበሩትን ምግቦች ከስጋና ከቅባት እህሎች ጋር በመቀላቀል ቢመገቡም ይመረጣል።

እንደ አቶ ቢራራ ገለፃ እንዲህ አይነቱ የአመጋገብ ስርአት ወቅታዊ ወይም ፆምን ታክኮ የሚደረግ ብቻ መሆን የለበትም። ለአብነትም በፆም ወቅት ሰዎች በየአይነት ሲመገቡ ከእንስሳት የማያገኟቸውና ከእህል ዘሮች የሚያገኟቸው ሰውነት ገምቢ ምግቦች አሉ። በሽታን የሚከላከሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ምግቦችም አሉ። በተመሳሳይ ኃይል ሰጪ በርካታ የምግብ አይነቶችም በስፋት ይገኛሉ።

ከዚህ አኳያ ሰዎች በፆም ወቅት የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርአት ሲከተሉ ቆይተዋል ማለት ነው። በፋሲካ በዓል ወቅትም ሰዎች በተመሳሳይ መልኩ የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርአትን ሊከተሉ ይገባል። አትክልትና ፍራፍሬዎችም በስርአተ ምግባቸው ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከእንስሳት ተዋፅኦዎችም በተመጣጠነ መልኩ በስርአተ ምግብ ውስጥ መጨመር አለባቸው።

ስጋን ብቻ መመገብ የራሱ ጠቃሚ የምግብ ንጥረ ነገር ያለው ቢሆንም በፆም ፍቺ ወቅት ከአትክልትና ፍራፍሬዎች ጋር በማመጣጠን መመገብ ቢቻል የተሻለ ይሆናል። በተቻለ መጠን ተፈጥሮ ባስቀመጠቸው መሰረት ሰዎች የእንስሳት ተዋፅኦዎችን ሲመገቡ የእህል ዘሮችን፣ የአትክልትና ፍራፍሬዎችን ሳይተውና በማመጣጠን መሆን ይኖርበታል። ሁሉም ነገር ከመጠን በላይ ሲሆን ትርፍ ነውና ለሰውነት ተስማሚ አይሆንም። ውፍረት ያስከትላል። ውፍረት ሲመጣ ደግሞ ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣል።

አቶ ቢራራ እንደሚናገሩት ሰዎች ለረጅም ጊዜ በፆም ምክንያት የእህልና የአትክልት ምግቦችን ሲመገቡ ቆይተው ወደ ስጋና ቅባታማ ምግቦችን ወደ መመገብ ሲሸጋገሩ ጊዜያዊ ጉዳት ሊያጋጥማቸው ይችላል። በተለይ ደግሞ ሰውነት የለመደውና ለምግብ መፈጨት ጠቃሚ የሆኑና ቅባት የሚፈጩ ኢንዛይሞች በፆም ወቅት ስራቸው ስለሚቀንስ ሰዎች በቀጥታ ወደ ቅባታማና የስጋ ምግቦች ወደ መመገብ ሲዞሩ ድንገተኛ የጤና ችግር ሊያጋጥማቸው ይችላል። ጠቃሚ ንጥረ ምግቦች ወደ ሰውነት ሴሎች ላይገቡም ይችላሉ። ይህ ከመሆኑ በፊት ታዲያ ሰዎች የስጋና የቅባት ምግቦችን በትንሽ መጠን ቀስ በቀስ እያስለመዱ መመገብ ይኖርባቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች እነዚህን የስጋ ተዋፅኦዎችንና ቅባታማ ምግቦችን ብሎም አልኮልን ከበቂ በላይ ሲወስዱ በሰውነታቸው ውስጥ ከበቂ በላይ ሊከማች ይችላል። ይህ ክምችት ታዲያ የደም ቧንቧዎችን ሊያጠብ ይችላል። አላስፈላጊ የሸንት ክምችትም ያስከትላል። ይህም ለደም ግፊት፣ ስኳር፣ ኩላሊት፣ ካንሰርና ሌሎችም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣል።

የፋሲካ በዓል ቢሆንም፣ ዶሮው፣ በጉ፣ ቅርጫው ሁሉ የተትረፈረ ቢሆንም ይህን ሁሉ የስጋ ተዋፅኦ ከሌሎች የአትክልትና ፍራፍሬ፤ እንዲሁም የእህል ዘር ምግቦች ጋር አመጣጥኖ መመገብ ያስፈልጋል። ይህ ካልሆነ ግን ቅባት በበዛባቸው ምግቦች ምክንያት የተዛባ አመጋገብ ሊከሰት ይችላል። ስለዚህ በበዓል ወቅት ትልቅ የአመጋገብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

# ለጤንነትዎ

## ለጤናማ እንቅልፍዎ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ለሰው ልጅ ከምግብና መጠጥ ባለተናነሰ መልኩ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ አንዱ እንቅልፍ ነው። እንቅልፍ ሰዎች ጥሩ የአእምሮና የአካል ጤንነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ቀን በስራ የደከመ ሰውነትና አእምሮ እንዲያገግም በማድረግ ረገድም የእንቅልፍ ሚና ከፍተኛ ነው።

ከዚህ ባለፈ እንቅልፍ የጤና እክል እንዳይኖር፣ ጤናማ ክብደት እንዲኖር፣ የስኳርና የልብ ህመምን የመሳሰሉ የከፉ የጤና ችግሮች እንዳያጋጥሙ፣ ጭንቀት እንዲቀንስና የሰውነት ስሜት እንዲሻሻል፣ በትምህርት ቤትም ሆነ በስራ አካባቢ ውጤታማ ለመሆንና ከሰዎች ጋርም መልካም ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል።

እንቅልፍ የዚህን ያህል የጤና ጥቅም ካለው ታዲያ ሰዎች በቂ እንቅልፍ የማያገኙ ከሆነ በተቃራኒው ጤናቸው ይቃወሳል። በቂ እንቅልፍ የማያገኙና የከፉ የእንቅልፍ ችግር የሚታይባቸው ሰዎች ለከፍተኛ የደም ግፊት፣ ለስኳር፣ ለልብ በሽታና ልብ በድንገት ስራዋን ማቆም እንዲሁም ለስትሮክ ሊጋለጡ ይችላሉ።

በተጨማሪም በቂ እንቅልፍ የሌላቸው ሰዎች ለውፍረት፣ ለድብርት፣ የሰውነት በሽታን የመከላከል አቅም ማነስና ሌሎችም ተያያዥ የጤና ችግሮች



ሊያጋጥማቸው ይችላል። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እንቅልፍ እምቢ ሲላቸው የእንቅልፍ መድሃኒቶችን አብዝተው በሚወስዱ ጊዜ ለጎንዮሽ የጤና ጉዳቶች ይጋለጣሉ። በአብዛኛው በእንቅልፍ ኪኒኖች ላይ ጥገኛ ሆነውም ይታያሉ።

እርስዎስ እንቅልፍ በበቂ ሁኔታ ይወስድዎታል? እንቅልፍዎስ ጤናማ ነው? አዎ! እርስዎም የእንቅልፍ ችግር ሊኖርብዎ ይችላል። ወይም ደግሞ ጤናማ እንቅልፍ እንዳይኖርዎ የሚረብሹ ነገሮች ይኖራሉ። ጤናማ እና በቂ እንቅልፍ እንዲኖርዎ ታዲያ ከታች የተዘረዘሩትን እንዲያደርጉ በጤና ባለሙያዎች ይመከራሉ።

1ኛ፡- የሚተኙበትንና የሚነሱበትን ሰዓት ያስተካክሉ፤

2ኛ፡- ከእንቅፍ በፊት ሁሌም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ያድርጉ፤

3ኛ፡- ከእንቅልፍ በፊት ቡና አይጠጡ፤ ከባድ ምግቦችንም አይመገቡ

4ኛ፡- አዕምሮዎን ከሚያጨናንቁ ነገሮች ያፅዱ፤

5ኛ፡- የሚተኙበትን መኝታ ምቾት ያረጋግጡ፤ አመቺ ካልሆነ ያስተካክሉ፤

6ኛ፡- እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና መሰል የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን በእንቅልፍ ሰዓትዎ አይጠቀሙ፤

7ኛ፡- የመኝታ ክፍልዎ ለእንቅልፍ አመቺ መሆኑንና አስፈላጊ ነገሮችን ማሟላቱን ያረጋግጡ፤

8ኛ፡- በቀን የሚወስዱትን ናፕ ይቀንሱ።

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "የአስቆሮቱ ይሁዳ ልጆች፤ የበርባን ጠበቆች"

**ዝክረ ሰሙነ ሕማማት፤**

ይህ ሳምንት በክርስትና አማኒያን ዘንድ "ሰሙነ ሕማማት" [የሕማማት ሳምንት] በመባል ይታወቃል። ሳምንቱ ከሆሳዕና እስከ ትንሣኤ ያሉትን ቀናት የሚሸፍን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን ለመያዝ የአይሁድ አለቆችና ካህናት የመከሩበት፤ እርሱን ካልያዙ እህል አንኳን ላለመቅመስ ክፉ መሃላ የተማማሉበት፣ በአስቆሮቱ ይሁዳ ከህደት ጌታን እንደ ወንጀለኛ አስረው ወንጀለኛው በርባንን እንደ ጻድቅ ነጻ ያወጡበት ሳምንትም ነው። ፍጻሜው የተጠናቀቀው የደምና የሕይወት መስዋዕትነት በተከፈለበት የክርስቶስ የመስቀል ሥራ ሆኖ ማሳረጊያውም ትንሣኤ ነው።

ክርስቶስ የተቀበለው ስቃይና መከራ ሲተረክም ጎን ለጎን ተደጋግሞ ስማቸው ከሚነሳው መካከል የአስቆሮቱ ይሁዳ፣ የካህናት አለቆችና ፈሪሳዊያን፣ ገዢው ጲላጦስና በርባን የሚሉት ተዘውትረው ይታወሳሉ። በተለይም እስከ ሞት ድረስ አሳልፎ የሰጠው የራሱ ወዳጅና ደቀመዝሙር ይሁዳና ወንጀሉ እንደ ክብር ተቆጥሮለት ሞቱ በክርስቶስ ሞት የተለወጠለት የበርባን ታሪክም ለምድራዊው የፍትህ ርሃብና ለሰዎች ልጆች የልብ ድንዳኔ ጥሩ ማሳያ ነው።

ከላይ ተመጥኖ የታወሰውን የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክና የክርስትና እምነት እንደ ዋና ዓምድ የቆመበትን አስተምህሮ የሚገልጹትን ዋና ዋና አናቅጽ ከአራቱ ወንጌላት (ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ) እየመዘዝን ካስታወስን በኋላ ወደ ዋናው አገራዊ ዐውዳችን ተመልሰን በራሳችን ጉዳዮች ላይ ጫን ብለን እንወያያለን።

"ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ የነበረው አስቆሮቱ ይሁዳ ወደ ካህናት አለቆች ዘንድ ሄዶ ክርስቶስን አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ልትሰጡኝ ትችላላችሁ? አላቸው። እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት። ከዚያች ሰዓት ጀምሮም አሰልፎ ሊሰጠው ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር።... ከእርሱም ጋር ብዙ ሕዝብ ሰይፍና ጎመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሎች ዘንድ መጡ። አሳልፎ የሚሰጠውም የምስመው እርሱ ነው፤ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቷቸው ነበር። ይሁዳም ወደ ኢየሱስ ቀረበና "መምህር ሆይ ሰላም ላንተ ይሁን!" ብሎ ሳመው። ኢየሱስም መልሶ "ይሁዳ ሆይ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን?" አለው።"

"ሲነጋም የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሎች ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ። አስረውም ወሰዱት። ለገዢውም ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። ... ጲላጦስም አላቸው ይህንን ሰው በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድስ እንኳን በደል አላገኘሁበትም። እነሆ ለሞት የሚያደርሰው ምንም በደል አልፈጸመም" አላቸው።

"...በዚያ በዓል ሕዝቡ የወደዱትን አንድ እስረኛ ሊፈታላቸው ለገዢው ልማድ ነበረው። በዚያም ወቅት በርባን የሚባል በጣም የታወቀ እስረኛ ነበራቸው። ሁላቸውም ኢየሱስን አስወግድ! በርባንንም ፍታልን! እያሉ ጮኹ። እርሱም ሁከትን በከተማ አስነስቶ ሰውን ስለ ገደለ በወህኒ ታስሮ ነበር። ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታ ወዶ ዳግመኛ ጠየቃቸው። ነገር ግን እነርሱ ስቀለው! ስቀለው! እያሉ ጮኹ።"

"ለሦስተኛም ጊዜ ኢየሱስ ያደረገው ክፋት ምንድን ነው? ለሞት የሚያደርስ በደል አላገኘሁበትም ስለዚህ እፈታዋለሁ አላቸው። እነርሱ ግን በርባን እንዲፈታ ኢየሱስ ግን እንዲጠፋ ሕዝቡን አባባሉ። እንዲሰቀልም በታላቅ ድምጽ አጽንተው ለመኑት። ጩኸታቸውና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ። ጲላጦስም ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው አላቸው? ሁሉም በአንድ ድምጽ ‹ይሰቀል!› እያሉ ጮኹ። ያንን የለመኑትን ስለ ሁከት፣ ሰውን ስለመግደል በወህኒ ታስሮ የነበረውን በርባንን ፈታላቸው።"

"ጲላጦስም እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ። ሕዝቡም ሁሉ መልሰው ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። በዚያን ጊዜም በርባንን ፈታላቸው። ኢየሱስ ግን ተገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።"

**የእኛዎቹ የአስቆሮቱ ይሁዳዎችና የበርባን ጠበቆች፤**

"ግፍ የተሠራብን በእኛ፤ ካሱ ይሉናል በዳኛ" እንዲል ብሂላችን፤ ኢትዮጵያ እያለፈችበት ያለው መከራ በነበር የሚታወስ ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ አንገት እያስደፋ ሲዘከር የሚኖር ታሪክ ጭምር ነው። የመከራ እቶን እያጋጋሉ፣ መከረኛው ሕዝብም በረመጡ እየተንገበገበ እንዲሰቃይ አሳር ያሸከሙን አሳረኞች መልካቸውም ሆነ ብዛታቸው የትዬለሌ ነው።

የአስቆሮቱ ይሁዳን መሰል ከሃዲዎች እንደ ፍግ ላይ የጅብ ጥላ በየቦታው ፈልተው "ኢትዮጵያን ለማሰቀል" ያልሞከሩት ሙከራ፣ ያላሴሩት ሴራ አልነበረም። አንዳንዶች ይሁዳዎች በአገሪቱ የሥልጣንና የኢኮኖሚ ወጭቶች ውስጥ በቀዳሚ ተጠቃሚነት እጃቸውን ከተው እፍታውን እየፈተፈቱ ሲጎርሱ ኖረው ምሬት ባንገፈገፈው የሕዝቡ ቁጣ የ"ወጭቱ" ጥቅም ከፊታቸው ዞር ሲል ያደረሱትና እያደረሱ ያለው የግፍ ዓይነትና አበዛዝ በብዙ ማሳያዎች ሊረጋገጥ የሚችል ነው።

"ይሁዳ ክርስቶስን በመሳም አሳልፎ እንደሰጠ" ሁሉ እነዚህን መሰል የእኛ ጉዶችም ኢትዮጵያ ለክፉዎች ተላልፋ እንድትሰጥ ከአደባባይ እስከ ጓዳ፣ ከታላላቅ ጉባዔዎች እስከ የድብቅ ሸንጎዎች ያልዘረጉት መረብ፣ ያላጠመዱት አሽክላ የለም ማለት ይቻላል። ለክፉ ቀን ባህር አሻገረው "ድምጽ" እንዲሆኗው በአዘጋጁቸው የፖለቲካ ጀሌዎቻቸውና የርኩስ ሃሳብ ካህናት ልጆቻቸው አማካይነትም የኢትዮጵያን ስም ለማጠልሸት በሉዓላዊነታችን ላይ ያልለቀለቁት ጥላሸት አልነበረም። ለአይዟችሁ ባይ የዓለም ኃያላን "ፈሪሳዊያን" አሸርጋጆችም ራሳቸውንና ክብራቸውን እያነጠፉላቸው በስመ ሰብዓዊ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ላይ ማዕቀብ እንዲጣል ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።

ይሁዳ ከሩቅ አይመጣም። አብሮ ኖሮ እስከ ሞት ላለመለያየት በመሃል ጭምር ኪዳን ቢገባም እንኳን፤ "ጥቅም" ከተመዘነለት ግን ከራሱ ውጭ ማንንም ቢሆን አሳልፎ ለመስጠት ሙት ኅሊናው አይወቅሰውም፤ አይገስጸውም። አስቆሮታዊ ይሁዲነት መልኩ ብዙ፣ ቀለማቱም አያሌ ናቸው። ከሀዲስ አንዴ በክህደቱ ጸንቶ ያሻውን ለመፈጸም ሊታወር ይችላል። አስቸጋሪዎች አስቆሮታዊያን በጋራ ማዕድ ላይ እንደ ብርቱ ወዳጅ እየተጎራረሱ "በሞቴ" "በሞቴ"ን እያስቀደሙ ሞትን ደጋሾች ናቸው። ኢትዮጵያም በእነዚህ ጭምር በጽኑ እየተፈተነች ነው። ሁለት ባላ ተክለው አንዱ ሲነቀል በአንዱ ለመንጠልጠል ዝግጁ የሆኑ በርካቶች በመንግሥታዊ ሥርዓት ውስጥ ተሰግስገው የጭቃ ውስጥ እሾኽት ሚናቸውን እየተወጡ እንዳሉ ከራሳቸው ከቁንጮ መሪዎች አንደበት ደጋግመን አድምጠናል።

የአንዳንዶች ጩኸትና የዘመቻ ሩጫ ወንጀለኛውን በርባንን ለማጽደቅ እንደሆነም እያስተዋልን ነው። በወንጀላቸው፣ በግፋቸውና በክህደታቸው ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ቅጣት እንኳን የሚያንሳቸው የዘመናችን ከሃዲያን እንደ "ጻድቃንና ሰማዕታት" እየተቆጠሩ በሽብሽባ እንዲወደሱ፣ በአድናቆት እንዲሞካሹ የሚደረገው ሩጫና "የሆሳዕና" አድናቆትም በእኛም ዘመን የተለመደ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ኢትዮጵያ በአስቆሮቱ ይሁዳ አማካይነት "ለሞት ተላልፋ እንድትሰጥ"፣ የወንጀለኞቹ የእነበርባን ጠበቆችም መላው የዓለም ሕዝብ በአንገታቸው ላይ ኒሻን እንዲያጠልቅ፣ በደረታቸው ላይም ሜዳሊያ እንዲያንጠለጥል" ቀን ከሌት እንቅልፍ አጥተው እየተቅበዘበዙ እንደሆነ እያስተዋልንና እየሰማን ነው።

ከመንፈሳዊ አንድምታ ጋር እያቆራኘን የቆዘመንበትን እውነታ በግልጽ ቋንቋና በተራ የመግባቢያ ወጋችን ትንሽ እናፍታታው። ያለ ምንም የግነት ገለጻ ያለፉት ጥቂት ዓመታት ለኢትዮጵያ ሰሙነ ሕማማት እንደነበሩ ማንም ሊክደው የማይችለው ሐቅ ነው። የሕመሟ ጥዝጣዜም ቀላል የሚባል አልነበረም። በተለይም ከሥልጣን ተገፍትሮ ወደ ተፈጠረበት በረሃ ዳግም የሸፈተው ቡድን የፈጸማቸው የክህደት ተግባራት በቀላሉ ተዘርዝረው የሚያበቁ አይደሉም።

መከላከያን የሚያህል የአገር ኩራት ተክዶ የተወጋውና በታሪክ ይቅር የማይባል በደል የደረሰበት በውስጡ በነበሩት በከሃዲያኑ የአስቆሮቱ ይሁዳ ወላጆች ነበር። በውስጥም የአገሪቱ የፖለቲካ መልካ/ጅረት እንዲናጋ፣ የኢኮኖሚው መሠረት እንዲርድ፣ የማሕበራዊ ትስስሩ ገመድ እንዲላላ፣ የኅብረተሰቡ በጎ እሴቶች እንዲናዱ፣ የሃይማኖት ውቅሩ ስንጥቅ እንዲገጥመው የተቀናበረውና እንዲተገበር የተደረገው እነዚሁ የጥፋት መልእክተኞች "በተጠበቡበት" ሴራ እንደሆነ መካድ አይቻልም።

በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የመሸጉና የተሸሸጉ "የፖለቲካው ካባ ለባሾም" እንዲሁ በሥልጣናቸው ሼል ውስጥ ተደብቀው ሕዝብ እያማረሩ ይሁዳዊ ድርጊታቸውን እየተወጡ እንዳለ በምናያቸው ብዙ ድርጊቶች እያረጋገጥን ብቻም ሳይሆን እውነት መሆኑንም መሪዎቻችን በይፋ እየገለጡልን ነው።

ኢትዮጵያ "የመስዋት በግ" (Scapegoat) ሆና የአገር ከዳተኞችና ወንጀለኞች ጀግና ሆነው እንዲከበሩና የዓለምን ቀልብ እንዲገዙ የሚደረገው ርብርብም በቀላሉ የሚታይ አይደለም። "ታላቅነታቸውን" በታናናሽ ድርጊታቸው እየገለጹ ያሉ መንግሥታትም በነጋ በጠባ ጉባዔያቸው ላይ እየተሰየሙ መንጫጫታቸውና በማዕቀብ ዱላ ማስፈራራታቸው መዘግየት ካልሆነ በስተቀር ቆሟል ብሎ ለመናገር አይቻልም።

"የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪነታቸውን" መታወቂያ እያውለበለቡ በፍርደ ገምድልነት ኢትዮጵያን ለማሳጣትና የግፈኞቹ ድርጊት እንደ "ጽድቅ" እንዲቆጠር የበርባን ጠበቃ የመሆናቸው ድርጊትም ከበስተጀርባው በማን እንደሚዘወርና እንደሚነዱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠፋዋል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

የሁለት ሺህ ዓመቱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ድርጊት ዛሬም "ፍሬሽ" ነው። ለበርባን ጥብቅና ካልቆምን ባይ የጪሂዎች ኡኡታም የአጪጪሁ ስልት ካልሆነ በስተቀር ድምጸቱ ልዩነት የሌለው አንድ ዓይነት ነው። ጲላጦሶችም በየአገራቱ የሥልጣን ወንበሮች ላይ ዛሬም እንደተሰየሙ አሉ። ሕማማት የአንድ ሣምንት ጉዳይ ነው። ትንሣኤ ግን ዘላቂና ቀጣይ ነው።

የኢትዮጵያ ሕማማት የሚጠናቀቀው በትንሣኤ ብርሃን ፈክቶ ስለመሆኑ ይሁዳዎቹም ሆኑ የበርባን ጠበቆች በሚገባ አሜን ብለው እውነታውን በመቀበል ወደ ቀልባቸው እንዲመለሱ በሕዝብ ድምጽ እንመክራቸዋለን። እያስተዳደሩን ካሉት መካከልም "ይሁዳዎች" ፍጻሜያቸው ስለማያምር በንስሃ ቢመለሱ ይበጃቸዋል። ከሕዝብ ጉሮሮና ሀብት ላይ እየቆነጠሩ የሚሰበስቡትና የሚዘርፉት ሀብት "ሳይበሉት" እንደሚያልፉ ቢረዱት አይከፋም። ይሁዳ ክርስቶስን በሸጠበት ሠላሳ ዲናር የተገዛው የደም መሬት ነው። በመንግሥት ሥልጣን የተሸሸጉ ኅሊና ቢሶችም ከአገር መቀነት የሚፈቱት "ሀብት" ቤታቸውን የደም ቤት እንዳያደርግ ራሳቸውን ቢያጸዱ ይበጃቸዋል።

ይሁዳ ሆይ ከህደትህ አያዋጣም። በአካላዊ አንደበት በርባን እንዲፈታ መጮኽ ቢቻልም ከውስጥ ኅሊና ኡኡታ ግን ማምለጥ እንደማይቻል የሚመለከታቸው ሁሉ ይወቁት። የሕማማት ሣምንቱ የሚያበቃው ነገ ነው። ነገ ትንሣኤ ይበሰራል። የኢትዮጵያ ሕማማትም እንዲሁ ማለቂያው ቅርብ ነው። አገራዊ ትንሣኤያችንም ሩቅ አይደለም። ሰላም ይሁን! መልካም በዓል።

> ይሁዳ ከሩቅ አይመጣም። አብሮ ኖሮ እስከ ሞት ሳለመለያየት በመሃል ጭምር ኪዳን ቢገባም እንኳን፤ "ጥቅም" ከተመዘነለት ግን ከራሱ ውጭ ማንንም ቢሆን አሳልፎ ለመስጠት ሙት ኅሊናው አይወቅሰውም፤ አይገስጸውም። አስቆሮታዊ ይሁዲነት መልኩ ብዙ፣ ቀለማቱም አያሌ ናቸው። ከሀዲስ አንዴ በክህደቱ ጸንቶ ያሻውን ለመፈጸም ሊታወር ይችላል። አስቸጋሪዎች አስቆሮታዊያን በጋራ ማዕድ ላይ እንደ ብርቱ ወዳጅ እየተጎራረሱ "በሞቴ" "በሞቴ"ን እያስቀደሙ ሞትን ደጋሾች ናቸው

**ፖለቲካና ወቅታዊ**

# ተናጋሪው ዶሴ

# የልብ ወዳጅ እጆች

**መልካምሥራ አፈወርቅ**



ትንሹ ልጅ ያደረበት መኻታ አልተመቸውም። ደጋግሞ ይገላባጣል። ማምሻውን ሲሰማው የቆየው ጉዳይ አሁንም ከስጋት እንደጣለው ነው። ሰዎቹ በየደቂቃው የአባቱን ስም እያነሱ ያወጋሉ። የሚጠሩት የገንዘብ መጠን ደግሞ ከዚህ በፊት ሰምቶት አያውቅም። ልጁ ውስጡ እየተረበሸ፣ ሆዱ እየተላወሰ ነው። ጥቂት ቆይቶ ምን እንደሚገጥመው አያውቅም። ክፉኛ ተጨንቋል።

ትንሹ ልጅ ሰዎቹ ምሽቱን ከቤት እንደሚያሳድሩት ገምቶ ነበር። እንዳሰበው አልነሆም። ዛሬም ከቤቱ ውጭ ካለ የጭድ ክምር ውስጥ እንዲያድር ፈርደውበታል። ከቀናት በፊት በወላጆቹ ቤት በፍቅር የሚያዩት ብዙ ዓይኖች ነበሩ። ያሻውን ቢጠይቅ ይደረግለታል፣ ያማረውን ቢበላ ከልካይ የለውም። ዛሬ ግን ይህ ሁሉ ታሪክ ሆኗል። የልጅ አንጀቱ ተላወሰ። ዓይኖቹ በትኩስ ዕንባ ተሞሉ።

ትንሹ ልጅ አጠገቡ ያሉት ሰዎች ከአንድ ሰው ጋር በስልክ ሲያወሩ ሰምቷል። ደጋግመው የሚጠሩትን ግለሰብ በደንብ ያውቀዋል። ሰውዬው ከነዚህ ሰዎች ጋር በምን እንደተዛመደ አልገባውም። ስሙ ሲነሳ ሁሉ አብሮት የሚጠራው የገንዘብ መጠን አሁንም እያስደነገጠው ነው። ልጁ መሽቶ በነጋ ቁጥር ዓይኖቹ መንከራተት ያዙ፣ ቤተሰቦቹ በውስጡ ውለው ቢያድሩ ክፉኛ ናፈቁት። የሚወረወርለት ቁራሽ እንጀራ የእናቱን እጅ ቢያስታውሰው መላልሶ ሆድ ባሰው።

ልጁ ዕንባ እየተናነቀው ጆሮዎቹን ጥሎ ማዳመጥ ያዘ። ሰዎቹ አሁንም ከሰውዬው ጋር በስልክ ያወራሉ። በወሬያቸው መሀል የአባቱ ስም ሲጠራ የሰማ መሰለው። አዎ! አልተሳሳተም። የገንዘብ መጠኑ ጭምር እየተብራራ ነው። ይህኔ የልጅነት አይምሮው ፈጥኖ መንቃት ያዘ። አሁን ነገሩ ሁሉ ገባው። እሱ በሶስቱ አጋቾች እጅ የወደቀበት ምክንያት የገንዘብ ጉዳይ ነው።

ሰዎቹ ልጅን አግተው አባትን ገንዘብ እየጠየቁ ነው። ለዚህ ድርጊታቸው የሚተባበራቸው አንድ ሰው ከጎናቸው አለ። ታጋቹ ህጻን ንግግራቸውን በጥንቃቄ ማዳመጡን ቀጥሏል። ደጋግመው የሚጠሩት ግለሰብ የአባቱ የቅርብ ጓደኛና የሰፈራቸው ትልቅ ሰው ነው። የልጅነት ልቡ በሰውየው ላይ ተስፋ አደረገ። ካለበት፣ ችግር ከታገተበት ዓለም ፈጥኖ እንዲያወጣው ተመኘ።

ታጋቹ ልጅ ጥቂት ቆይቶ ለጆሮው የደረሰው መልዕክት ክፉኛ አስደነገጠው። ሰውየው እንዳሰበው አይነት አልሆነም። ሰዎቹ ለሚያቀርቡለት ጥያቄ አስደንጋጭ መልስ እየሰጠ ነው። እሱ እንደተረዳው ቃል የተገባላቸው ገንዘብ በተባለው ጊዜ ከእጃቸው አልደረሰም።

‹‹ፈላው›› የተባለውና ጓደኞቹ ሰውዬውን ምን ማድረግ እንዳለባቸው እየጠየቁት ነው። ሰውዬው ብሩን አባትዬው ካላመጣ ልጁ መገደል፣ አልያም ለሌሎች መሸጥ እንዳለበት ትዕዛዝ አስተላልፏል። ታጋቹ ህጻን የስልክ ምልልሱን አንድ በአንድ አዳመጠ። ተደብቆ ካለበት የጭድ ክምር የሚያወጡትን እጆች እየናፈቀም በሀሳብ ነጎደ።

**ከቀናት በፊት...**

ምዕራብ ጎጃም ዞን ዱርቤቴ ከተማ። በማለዳው ፈንጥቃ የወጣችው ጸሀይ የዕለቱን ውሎ በድምቀት ያስጀመረች ይመስላል። ሁሌም በዚህ ሰአት ጉዳይ ያላቸው ሁሉ ወዳሰቡት ይተማሉ። ገበያተኞች፣ መንገደኞች፣ ተማሪዎች፣ በየተራ ከተማዋን ይሸፍኗት ይዘዋል። ህጻን ሀብታሙ ታዬን በጠዋት የቀሰቀሰው የትምህርቱ ጉዳይ ነበር። እሱም እንደ እኩዮቹ ቁርሱን በልቶ፣ ደብተሩን ይዞ ወደትምህርትቤት መሄድ አለበት።

ሀብታሙ ሁሌም ማለዳ በዚህ ሰአት ወደትምህርትቤት ለመሄድ ከጓደኞቹ ይገናኛል። የዕለት ትምህርቱን አጠናቆ ከቤቱ ሲደርስ ወላጆቹ በስስት እያዩ ይቀበሉታል። ስለነገው ታላቅ ተስፋን የያዙበት ትንሹ ልጃቸው የቤታቸው በረከት ነው። ለትምህርቱ ይጨነቃሉ፣ ለነገው ማንነቱ ያስባሉ።

ሀብታሙና ባልንጀሮቹ ሰፈራቸውን አቋርጠው ትምህርትቤት የሚሄዱት በአንድነት ነው። እኩያሞቹ አንገት ለአንገት ተያይዘው ትምህርትቤት ሄዶ መመለስ የዘወትር ልምዳቸው ነው። የዛን ቀንም ሀብታሙ ከእነሱ ጋር በአንድ ተራምዶ ትምህርትቤቱ ግቢ ደርሷል።

ጓደኛሞቹ ወደየክፍላቸው ከመሄዳቸው በፊት አንዲት ባጃጅ አጠገባቸው ደርሳ መቆሚን አስተዋሉ። ሁሉም ዓይናቸውን ተክለው በየተራ ከውስጥ የሚወጡትን ሰዎች ተመለከቱ። ሰዎቹ ጓደኛሞቹን አልፈው ወደ ሀብታሙ ቀረቡና ይዘውት መሄድ እንዳለባቸው አሳወቁት። ከአባቱ እንደተላኩ የተነገረው ሀብታሙ ጓደኞቹን ተሰናብቶ ወደ ባጃጁ ወንበር አመራ። አፍታ ሳይቆይ ባጃጁ ፍጥነቱን ጨምሮ ወደፊት ተፈተለከ። ጓደኛሞቹ የባልንጀራቸውን መራቅ እያስተዋሉ እርስ በርስ ተያዩ።

የትምህርቱ ሰአት ተጠናቆ ልጆቹ ወደ የቤታቸው ለመሄድ ተፈላለጉ። ሁሉም ጠዋት ከእነሱ የተለየውን ጓደኛቸውን አልረሱም። ከበርካታ ተማሪዎች መሀል በዓይናቸው ቃኙት። እንደቀድሞው ሀብታሙን በቶሎ አላዩትም። ወደ ክፍሉ ተመልሰው በወጉ ፈለጉት። አላገኙትም።

ልጆቹ ክፉኛ ተጨነቁ። ጠዋት ያዩዋቸው ሰዎች መልሰው እንዳላመጡት ቢገባቸው ወደሰፈር ለመሄድ መንገድ ጀመሩ። ሰፈር የደረሱት ባልንጀሮች የሀብታሙን ጉዳይ ለማወቅ ወላጅ አባቱ ዘንድ መሄድ ነበረባቸው። አባትየውን እንዳዩት ሀብታሙ ወደ ቤት መጥቶ እንደሆን ጠየቁ። አባት ልጆቹ የሚናገሩት አልገባ ቢለው ከልብ ደነገጠ። ልጁ ዛሬ ማለዳ ከእነሱ ጋር ወደ ትምህርትቤት መሄዱን ያውቃል። ጉዳዩን እንዲያብራሩለት ጠየቀ። ሀብታሙን የማይታወቁ ሠዎቹ በባጃጅ ይዘውት መሄዳቸውን ገለጹለት።

አባት ይህን ሲሰማ በእጅጉ ደነገጠ። ልጁን ማንም በባጃጅ ይዞት እንደማይሄድ ያውቃል። ውስጡ ጥርጣሬና ድንጋጤ ገባው። እየተጣደፈ ወደ ልጁ ትምህርትቤት ገሰገሰ። መምህራን በተማሪያቸው መጥፋት እንደተደናገጡ አገኛቸው። ጊዜ አልፈጀም። ጉዳዩን ለህግ ለማሳወቅ ወደ ፖሊስ ጣቢያ አመራ።

አባት ጉዳዩን ለህግ እንዳሳወቀ መላው ቤተሰብ በጭንቀት ተዋጠ። የአካባቢው ነዋሪ የህጻኑ መጥፋት በእጅጉ አሳሰበው፣ ወዳጅ ዘመድ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ፍለጋውን ያዘ። አባት የአካባቢውን ጫካ፣ ጉድባና ጉድጓዱን በፍለጋ አሰሰ። መራዊና፣ ቢኮሎ ከተባሉ ስፍራዎች ደርሶም ‹‹ልጄን ያያችሁ›› ሲል ተማጸነ። ታዳጊውን ተማሪ ‹‹አየነው ›› የሚል አላገኘም። እየተጨነቀ ከአንድ ገዳም ገባ፤ ልጁን በሰላም ያገኘው ዘንድም እያነባ ተሳለ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የአባትዬው የእጅ ስልክ አንቃጨለ። እየተጣደፈ አፈጠጠበት። ከዚህ በፊት የሚያውቀው ቁጥር አይደለም። እጁ እየተንቀጠቀጠ ፈጥኖ አነሳው። ከወዲያኛው ጫፍ አንድ ሰው ጎርነን ባለ ድምጽ « ሀሎ » ሲል ተሰማው።

ሰውየው ጊዜ ያለው አይመስልም። ጥርት ብለው በሚሰሙ ቁጥብ ቃላቶች መልዕክቱን በሚገባ አደረሰ። አባት የሚሰማውን እውነት ማመን አልቻለም። ደዋዩ ስምንት መቶ ሺህ ብር ከከፈለ ህጻን ልጁን መረከብ እንደሚችል እየነገረው ነው። አባት ጉዳዩን እስኪያስብ ጊዜ አልተሰጠውም። ስልኩ በፍጥነት ከጆሮው ተዘጋ።

የደቡብ አቸፈር ወረዳ ፖሊስ ከልጁ አባት የደረሰውን የስልክ መልዕክት እንደመረጃ ይዞ ፍለጋውን ቀጠለ። ፖሊስ ከ‹‹አፋልጉኝ›› ማስታወቂያው ጋር ተያይዞ ያልተገባ ጥቅም የማግኘት ፍላጎት እንደሚኖር ገምቷል። ‹‹አገኘነው›› ብለው የሚደውሉ ሁሉ ትክክል ናቸው ብሎ አያምንም። አባት ይህን በማወቁ ልቡ ለሁለት ተከፍሏል።

በማግስቱ የልጁ አባት ስልክ አቃጨለ። ፈጥኖ አነሳው። የትናንቱ ደዋይ ነበር። ሰውየው ቀድሞ ያነሳለትን ጉዳይ ሳያዛባ ደገመለት። አባት ቃሉን ሰምቶ በትህትና ለማናገር ሞከረ። እነሱ የጠየቁትን ያህል ገንዘብ እንደሌለውና በእጁ ያለውን ሁሉ እንደሚሰጥ ቃል ገባ።

ደዋዩ ይህን ሲሰማ ያባብለው ያግባባው፣ ያዘ። እሱና ጓደኞቹ በግል እንደማያውቁት፣ ልጁን አሳልፎ የሰጣቸው የቅርብ ጎረቤቱና ወዳጁ መሆኑን በእርግጠኝነት ነገረው። አባት ግራ ተጋባ። በተለይ ሰውዬውን ይቅርታ እንዲጠይቅ መጠየቁ ይበልጥ አደናገረው። ተረጋግቶ ይህን ያደረገውን ሰው ማንነት ጠየቀ። ደዋዩ ጥቂት ምልክቶችን ጠቅሶ ስልኩን ጠረቀመው።

**አውጫጭኝ...**

እሁንም የዱርቤቴ ከተማ ነዋሪ በህጻኑ መጥፋት እንደተጨነቀ ነው። ልጁ ባልታወቁ ሰዎች ተወስዷል መባሉ ሁሉንም አሳስቧል። በየጊዜው በስብሰባ እየመከረ። መላምቱን ያስቀምጣል። የሚጠረጥራቸውን እየጠቆመ፣ የአቅሙን ይተባበራል። አንድ ቀን ከተሰብሳቢዎቹ መሀል አቶ ቸኮል የተባለ ወደ ልጁ አባት ቀርቦ ነዋሪውን በስብሰባ ማድከሙ ተገቢ ያለመሆኑን እያነሳ ገሰጸው።

አባት የእንዲህ ባዩ ሰው ንግግር ቢያስገርመው ለምን ሲል ጠየቀ። ቸኮል ከዚህ ቀድሞ የተደወለለትን ስልክ እያስታወሰ የአስጠላፊውን ማንነት በስም ጠርቶ አረጋገጠለት።

ፖሊስ ጠንካራ የምርመራ ቡድን አዋቅሮ ህጻኑን የማፈላለግ ስራውን ቀጥሏል። ስማቸው ሳይታወቅ በምልክት ብቻ የተነገሩትን ተጠርጣሪዎች አድኖ መያዝ ቀላል አልሆነም። የዳንግላ ከተማን ጨምሮ በተለያዩ ገጠሮች የሚገኙ ተጠርጣሪዎችን በማስረጃ አረጋግጦ ለመያዝ ፈታኝ ትግል ይጠይቃል።

በተደጋጋሚ በእጅ ስልኩ እየተደወለ ዛቻና ማስፈራራት የሚደርሰው አባት ጉዳዩን ለፖሊስና ለሌሎች ቢናገር ልጁን በህይወት እንደማያገኝ ተነግሮታል። አባት ሚስጥሩን ደብቆ ለማቆየት ከራሱ መክሮ በሚሉት ሁሉ ተስማምቷል። በተለይ የልጁን አንገት እንቆርጠዋለን ካሉት ወዲህ ውስጡ በፍርሀት እየራደ ነው። አሁን ዝምታን መምረጡ ለልጁ ህይወት እንደሚበጅ አውቋል። ለማንም ትንፍሽ እንደማይል ቃል ገብቶም ለሚሰጡት ትዕዛዝ ተገዢ ሊሆን እየተዘጋጀ ነው።

**መልዕክተኛው...**

በሁለቱ ወገኖች መሀል መልዕክት የሚያመላልሰው አቶ ቸኮል በሽምግልና ገብቶ እያደራደረ ነው። ገንዘቡን ከሰባ ሺህ፣ ወደ ስልሳ ሺህ አድርሶም ለሚገባቸው ሰዎች ለማድረስ ቀን ቆርጧል። ገንዘቡን ከአባትዬው ተቀብሎም አራት ሺህ ብር እንዲቀነስለት አድርጓል።

**የፖሊስ እርምጃ ...**

አባት ገንዘቡን ከፍሎ ልጁን ከተረከበ በኋላ እውነቱን ያወቁት ፖሊሶች ጉዳዩን በዋዛ አልተውትም። በእገታው ተሳትፈው ገንዘብ የወሰዱትን ተጠርጣሪዎች ለመያዝ አሰሳቸውን ቀጠሉ። ለፖሊስ በቂ መረጃ በመስጠት ታላቁን ድርሻ የተወጣው ህጻን ሀብታሙ በእገታ ቆይታው ያስተዋለውንና የደረሰበትን በአግባቡ በማስረዳት ለነገሮች ስኬት መንገዱን ጠረገ።

በአስተዋዩ ታዳጊ ምሪት መንገድ የጀመረው ፖሊስ ተጠርጣሪዎችን በእጁ ለማስገባት ሰፊ ዕድል አገኘ። ተፈላጊዎቹን ከያሉበት አድኖ በቁጥጥር ስር እንዳዋለም ድርጊቱን እንዲያስረዱት ጠየቀ። ሶስቱ ወጣቶች ስለፈጸሙት ወንጀልና ስለተቀበሉት ጥቅም አልካዱም። ሁሉም በድርጊቱ ስለመሳተፋቸው በቃላቸው አረጋገጡ። ፖሊስ እነሱ በሰጡት ቃል ብቻ አላበቃም። የድርጊቱን መነሻ በማስታወስ ለውጥኑ ማን እንዳደራጃቸው እንዲነግሩት ጠየቀ።

ሶስቱ ወጣቶች በየተራ በሰጡት ቃል ህጻኑን ለማገት ትዕዛዝ የተቀበሉት ከአባትዬው ጎረቤትና የቅርብ ወዳጅ አቶ ሽታ አወቀ መሆኑን አረጋገጡ። ሰውዬውና የልጁ አባት የአመታት ጎረቤትና የልብ ወዳጆች ናቸው። አብረው በልተው፣ ጠጥተው ክፉ ደጉን ስለማለፋቸው በርካቶች ይመሰክራሉ። ህጻኑ በሚፈለግበት ወቅት ሽታ ከተሰብሳቢዎች መሀል ሆኖ የሚባለውን ሲያዳምጥና ሲታዘብም ነበር።

ፖሊስ አራቱን ተጠርጣሪዎች በእጁ ካስገባ በኋላ በአጋቾቹና በአባትየው መሀል እንደሽማግሌ ሆኖ የማደራደሩንና ገንዘብ የማቀበሉን ስራ የከወነውን አቶ ቸኮል ዋሴን በቁጥጥር ስር አዋለ። ግለሰቡ ጉዳዩን ለፖሊስ ሳያሳውቅ የድርጊቱ ተባባሪ መሆኑ በህግ አስጠይቆታል።ፖሊስ የአምስቱን ተጠርጣሪዎች ቃል በአግባቡ መዝግቦ በእማኞች ፊት አስፈረመ።

## ውሳኔ...

አሁን የደቡብ አቸፈር ፖሊስ የምርመራ መዝገቡን በአግባቡ አጠናቆ ተጠርጣሪዎች በህግ የሚጠየቁበትን አግባብ አመቻችቷል። በበቂ ማስረጃና መረጃ የተጠናከረው የተከሳሶች መዝገብ ወደ ዓቃቤህግ ተላልፎም በችሎት መዳኘት ይዘዋል። የባህርዳርና አካባቢው ከፍተኛ ፍርድቤት ተከሳሾችን በአካል አቅርቦ የክስ መዝገባቸውን እየፈተሸ የድርጊቱን መፈጸም ከግለሰቦቹ ቃል ሲያረጋግጥ ቆይቷል።

ተከሳሾቹ በቀረበባቸው ህጻንን የማገትና ገንዘብ የመቀበል ወንጀል ጥፋተኞች ተብለዋል። ይህን ማረጋገጫ ተከትሎም ፍርድቤቱ መከላከል እንዲችሉ ዕድል ሰጥቷል። ተከሳሾቹ ወንጀሉን ማስተባበል አልቻሉም። ሁሉም በድርጊቱ ተሳታፊና ተጠቃሚዎች እንደነበሩ በህግ ፊት አረጋግጠዋል።

የባህርዳርና አካባቢው ከፍተኛ ፍርድቤት ታህሳስ 25 ቀን 2010 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሲመረምር የቆየውን የተከሳሾቹን መዝገብ አጠናቆ ተከታዩን ውሳኔ አሳልፏል።

1ኛ ተከሳሽ ሽታ አወቀ በአስራ ስምንት አመት ጽኑ እስራትና በሶስት አመታት የህዝባዊ መብት እግድ፡-

2ኛ 3ኛና 4ተኛ ተከሳሾች በመሆን የቀረቡትና የእገታ ወንጀሉን የፈጸሙት ሶስት ወጣቶች እያንዳንዳቸው በአስራ ሰድስት አመት ከአስር ወር እስራት፡-

3ኛ ተከሳሽ አቶ ቸኮል ዋሴ ከህጻኑ አባት ገንዘብ በመቀበል የእገታ ወንጀሉን በማስፈጸሙ የአስራ ሶስት አመት ጽኑ እስራት እንዲወሰንበት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በማሳለፍ የክስ መዝገቡን አጠናቋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ጣጣውን የጨረሰ ነው?

**ዘካርያስ ዶቢ**

ለክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ! ዛሬ ዋዜማው ላይ ነን። የዓመት በዓል ስሜት እዚህም እዚያም ይስተዋላል። ያም ያም ስለዓመት በዓል ያወራል። በዓሉ ሲቃረብ ስለዋጋ የሚያወሩ ብዙ ናቸው። አጀንዳው ሁሉ ገበያ ነው፤ ዋጋ ነው።

ነጋዴው የሚያስወራቸው ይሁኑ ወይም ደላሎች አይታወቅም ብቻ ብዙ ይወራል። የገዢዎችን አቅም ለመፈተሽ ይመስላል፤ የዚያንም የዚያንም ዋጋ የጠየቁትን ስታነጋግሩ በተለይም የከብት፣ የበግ የፍየል የዶሮ ዋጋ አይቀመስም ነው ምላሻቸው። ነጋዴዎች ይታወቃሉ፤ የተለያዩ ምክንያቶችን በመደርደር ከፍተኛ ዋጋ ይጠራሉ። የሚጠሩት ዋጋ ይዘገንናል። ለነገሩ ቅቤ ነጋዴ ስለድርቅ ያወራል ይባል አይደል፤ በተለይ አለአግባብ ለመክበር የሚጥር ነጋዴ ሌላ ምን ሊል ይችላል።

ሰሞኑን ቄራ ከብት ተራ ብቅ ያለን አንድ ሰው አግኝቼ ነበር። ከብት ያውቃል፤ ቅርጫ ላይም አዋቂ ነው ። ገበያውን አይቼ ልምጣ ብሎ የሄደ ነው፤ እንዴት ነው አልኩት፤ ተወኝ አለኝ። የገናውን የዘመን መለወጫውን እያስታወሰ አሁን የሚጠራው ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን ገለጸልኝ። ከብት ገብቷል፤ የዋጋ ነገር ግን አይቀመስም፤ እሳት ነው አለኝ።

ይለይለት፤ ዓርብ ቅዳሜ አናየዋልን ተባብለን ጉዳዩን አሳደርነው፤ ለነገሩ ነጋዴ የሚጠራው ዋጋ ለጊዜው ነው የሚፈራው፤ እሱ የጠራውን ንደው የሚጠሩለት አሉ። ወገቡን ብለው። የምሩ ግብይት ሲጀመር ገበያው በነጋዴው ጥሪ ቆሞ አይቀርም፤ ደግነቱ ከብት ገበያ ሱፐር ማርኬት አይደለም፤ መከራከር ይቻላል።

ሰውም የሚገዛበት ወቅት ይለያያል። አንዳንዶች የከብት ግዢ የሚፈጽሙት አስቀድመው ነው። ከከተማ ውጭ በጥሩ ዋጋ ካገኙ አስቀድመው ይገዛሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ በዓሉ እየደረሰ ሲሄድ ያለውን ግፊያ እየጠሉ ይመስለኛል በጊዜ ይጠናቀቃሉ፤ አንዳንዶች ዋጋ ሲያጠያይቁ ሰንብተው /አጥንተው/ የሚገዙት በዋዜማው ነው። እነዚህ ጥሩ መረጃ ስለሚኖራቸው ጥሩ ይገበያሉ። አንዳንድ በግና ፍየል ገዥዎች ደግሞ የበዓሉ እለት ጠዋት መግዛትን ይመርጣሉ፤ እነዚህ ደግሞ በጥሩ ዋጋ ጥሩ ከብት ይገኛል የሚሉ ናቸው። ከብት ሳይመረጥ ብለው አስቀድመው የሚገዙም አሉ። በበዓል ወቅት ሁሉም በየፈናው ይሮጣል።

ጨዋታችን ሌሎች ጎረቤቶቻችንም ተቀላቀሉት። የገበያ ወሬው ቀጠለ። አንድ ጎረቤታችን ከስራ ሲመጣ ስጋ ቤቶች ቀለም ተቀብተው ሙብራታቸውን ፏ አርገው መመልከቱን ነገረን። የገረመው ግን በጾሙ ወቅት ስጋ ሲሸጡ የነበሩትም ታድሰው እኩል ተሰልፈው ማየቱ ነው። ለነገሩ አብዛኞቹ ስጋ ቤቶች ሁለት ወር ለሚጠጋ ጊዜ ጦም ላይ ነበሩ። ዝግጅታቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ ለአንዴት አይነት አገልግሎት ሊሰጡን ይሆን ይህን ያህል የተዘጋጁት ? ብሎ መጠየቅ ግን ይገባል።

የስጋ ቤቶቹ አጀንዳ ሲነሳ ምን ስጋ ቤት ትለኛለህ ሲል ሌላው ጎረቤታችን ጥያቄ አነሳ። ወርቅ ቤት በል እንጂ አለ ሲል እሱው መለሰው። እውነቱን ነው የዘንድሮ ስጋ ቤት ወርቅ ቤት ማለት ነው። አንዳንድ ስጋ ቤቶች የሚጠይቁት የአንድ ኪሎ ስጋ ዋጋ ሲታሰብ ወርቅ ቤት ያሰኛቸዋል። አንድ ግራም ወርቅ ነበር ይህን ያህል የሚያወጣው። ለዚያውም ካራቱ ጥሩ የሚባለው።

የከብት ዋጋ ጨምሯል እየተባለ ባለበት በዚህ ወቅት የስጋ ቤቶች የስጋ መሸጫ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፤ አብረን ኖረን አይደል። በእዚህ በዓል ደግሞ ሌላ ጉድ ያሳዩናል። ፊትም ደግ የሚያወሩ አይደሉም፤ በኪሎም በሚዛንም ይገሽልጡናል።

አንድ ቦታ ደግሞ ስለቅቤ ዋጋ ሲያወሩ ሰማሁ። ይሄ ጆሮ አልሰማም አይልም። ከዘጠኝ መቶ ብር በላይ ደርሷል ሲባል ሰንብቷል። ሰባት መቶ ቤትም እንዳለ ተወራ፤ የዶሮ ጣጣ በዘይት ሊዘጋ ነው ስል አሰብኩ። የዘይት ዋጋስ አስቀድሞ ታውቋል፤ ለምደነዋል።

ታክሲ ላይ የሰማሁት ግን በጣም ተመችቶኛል። አንድ ወጣት ነው። በስልክ እያወራ ነው። ይስቃል፤ ይጠይቃል ፤ አሁንም ይስቃል፤ ይጠይቃል። በመጨረሻም እሺ ግን ሁሉም ነገር ያለው ነው? ሲል ይመልስላቸዋል፤ ምን እንዳሉት አላውቅም ብቻ ታዲያ ይህን ያህል እንዴት ሊያወጣ ይችላል ሲል መለሰላቸውና አጠገቡ ካለው ጓደኛው ጋር ማውራት ጀመረ።

ጉዳዩ የዶሮ ዋጋ ይመስለኛል። ዶሮ ሶስት አሃዝ ደርሷል ሲባል የሰማሁ መሰለኝ። ጣጣውን የቻለ ነው ወይ ማለቱ ነው። ቅቤም፣ ዘይትም፣ ሽንኩርትም፣ ቅመምና የመሳሰሉትም አብረውት ካሉ ችግር የለውም እንደ ማለት ነው። የዶሮን ጣጣ ታውቁታላችሁ። እንደ ስጋ በዋዛ ተጠብሳ አትበላ።

የሚያሳስበው ይሄ ዋጋ በየበዓሉ እየጨመረ መሄዱ ነው። በግ እና ዶሮ ወይም ፍየልና ዶሮ ተገዝተው ከሆነ በእዚህ ላይ ደግሞ ቅርጫ ተጨምሮ ከሆነ እነ ሽንኩርት፣ ዘይትና ቅቤ እንዲሁም ቅመማ ቅመሞች የግድ ናቸው። ፓኬጅ የሚባሉ ናቸው። አብረው የሚሄዱ ናቸው። የወጪውን ነገር አስሉት። እኛ እያወራን ያለነው ስለዶሮ ፣ በግ ፍየልና በሬ ነው። ጉዳዩ እዚያ ላይ አያቆመም። ተከትሎ ብዙ ጣጣ ይመጣል።

ዘይቱ፣ ቅቤው፣ ሽንኩርቱና ቅመማ ቅመሞቹም በየራሳቸው ዋጋ ከጨመሩ ቆይተዋል፤ የበግና የፍየል ዋጋ በስፋት የሚታወቀው ያው በዓሉ ሲደርስ ነው። የዘይት ዋጋ የሕዝብና መንግስት አጀንዳ ሆኖ ነው የቆየው። አሁን ተረኛው የቅቤ፣ የከብትና የዶሮ ዋጋ ነው።

ባለፈው ዓመት በዓል ቅርጫ ለገቡ ሰዎች ከብት ሊገዙ ገበያ የወጡ ብዙ ተቸግረው እንደነበር ይነገራል። እንዳንዶቹ ገበያው የሚቀመስ አልሆን ሲላቸው የቅርጫው አባላት ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፍሉ አድርገዋል፤ ያን ማስፈጸሙ ግን አስቸጋሪ ነበር። አንዳንዶች ደግሞ የበግና ፍየል ገበያ ሳያልፍ ብለው ገንዘቡን በጊዜ መልሰዋል። ቅርጫው ተበትኗል፤ ይሄ እየተለመደ መጥቷል። አንዳንዶች ደግሞ በቅርጫው የሚሳተፉ ሰዎችን ቁጥር ጨምረው፣ አንድ በሬ ለስድስት ሊያርዱ ያሰቡትን ለስምንት በማድረግ፣ ሌሎች ደግሞ አንዱን መደብ ለሁለት በመካፈል ያን ጊዜ አልፈውታል።

ሁሉም የሄዱበት መንገድ ጥሩ የሚባል ነው። እንደ እኔ እንደ እኔ ቅርጫ ገቢዎች የግድ ቅርጫ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ አሁንም ተጨማሪ ሰዎችን እያስገቡ መቀጠል ቢችሉ መልካም ይመስለኛል። ይህን አይነቱን ሀሳብ ብዙዎች አይወዱትም፤ ሰው ሲበዛ ስጋው ይበጣጠሳል ይላሉ።

ዋናው ችግር ሰዎች እንደ ቀድሞው ለመኖር መፈለጋቸው ነው። በእዚህ ዘመን እንደ ቀድሞው መኖር ከታቻለ እሰየው ነው። በአገራችን በተከታታይ እየታየ ያለው የኑሮ ውድነት ግን እንደ ቀድሞው መኖርን የሚፈቅድ አይደለም፤ ይህ የኑሮ ዘይቤ እንዲቀየር የሚያስገድድ ነው።

ስጋ በኪሎ ገዝቶ በዓል ማሳለፍ አይቻልም ወይ?፤ በኪሎ ገዝቶ መጠቀም እየለመደ ያለ ህብረተሰብ ባለው ሁኔታ ለምን እንደሚቸገር ይገርመኛል፤ ለነገሩ ስጋ ቤቶች ዘንድ ደግሞ ችግር አለ፤ ዋጋው እና ቅሸባው።

በቅርጫው የሚሳተፉ አባላት ቁጥር በመጨመር የለመዱትን መፈጸም አይቻልም ወይ? ሁሉም ይቻላሉ። ሁሌም በቀደመው መጓዝን ለምን ያስፈልጋል? መጓዝ የፈለገ ደግሞ መጮህ የለበትም ፤ ህመሙን ቻል ነው ማድረግ ያለበት።

የበግ ወይም የፍየል ስጋ በኪሎ ገዝቶ በዓሉን ማሳለፍ አይቻልም ወይ፤ ይህስ ይቅር እሺ፤ በግ ወይም ፍየል ለሁለት ለምን ማረድ አይቻልም፤ ግማሽ ግማሽ መካፈል። ሙከት አርዶ ቅርጫ ቢደረግ ምን አለበት? ሰው ምን ይላል የሚሉ ሰምቻለሁ፤ ይሉኝታ ነው አንዱ ችግር።

በግ ወይም ፍየል አርደው ለሁለት የሚካፈሉ አንዳሉ አውቃለሁ። አስቀድሞ የገባቸው ናቸው። ይሄ ብልጠት ነው። ብልሃቱ ግን ወደሌሎች ሰፍቶ አይታይም። እንዲህ አንዲህ እያደረጉ በዓልን በብልሃት ማሳለፍ ሲቻል በትንሹም በትልቁም መጮህ ምን ይጠቅማል? ምንም አይጠቅምም። በዓልን እንደዚህ ዘመን አድርጎ ማክበር እንጂ ከጥንቱ ተጠብቆ ማላዘን አያስፈልግም። መልካም በዓል።

# ዓለም አቀፍ



## የሆንዱራስ የቀድሞው ፕሬዝደንት በእጽ ዝውውር ወንጀል ለአሜሪካ ተሳልፈው ተሰጡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአደገኛ እጽ ዝውውር እና በሕገ-ወጥ የተገኘን ገንዘብ ሕጋዊ አድርጎ ማቅረብ በሚሉ ወንጀሎች ክስ የቀረበባቸው የቀድሞ የሆንዱራስ ፕሬዝደንት ለአሜሪካ ተላልፈው ተሰጡ።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሆንዱራስን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ሁአን ኦርላንዶ ህርናንዴዝ በአሜሪካ አውሮፕላን ወደ ኒው ዮርክ ተወስደዋል።

የቀድሞ ፕሬዝደንት ሁለተኛ የስልጣን ዘመናቸው ከጀመሩ ከሳምንታት በኋላ ነበር ከሁለት ወራት በፊት ከመኖሪያ ቤታቸው በቁጥጥር ሥር የዋሉት።

ህርናንዴዝ ከቀረቡባቸው ክሶች መካከል አደንዛዥ እጽ ወደ አሜሪካ እንዲገባ ማሴር፣ ጦር መሳሪያ መጠቀም እና መያዝ እንዲሁም ጦር መሳሪያ ለመጠቀም እና ለመያዝ ማሴር የሚሉት ይገኙባቸዋል።

በቀድሞ ፕሬዝደንት ባለቤት የትዊተር ገጽ ላይ በተለጠፈ ተንቀሳቃሽ ምስል፤ ህርናንዴዝ የቀረቡባቸውን ክሶች አጣጥለዋል።

የአሜሪካ የፍትህ ቢሮ ህርናንዴዝ ዛሬ ሚያዚያ 14/2014 ኒውዮርክ በሚገኝ ፍርድ ቤት ይቀርባሉ ብሏል።

ዐቃቤ ሕግ ዳሚአን ዊሊያምስ የቀድሞ ፕሬዝደንት ከፍተኛ መጠን ያለው ኮኪዬን ለማዘዋወር ከእጽ አዘዋዋሪዎች ጋር ተጣምረዋል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም የህርናንዴዝ ታናሽ ወንድም ከእጽ ዝውውር ጋር በተያያዙ ወንጀሎች ጥፋተኛ ተብለው በአሜሪካ የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶባቸዋል።

የህርናንዴዝ ታናሽ ወንድም ቶኒ ህርናንዴዝ ለታላቅ ወንድሙ ፕሬዝደንታዊ የምርጫ ቅስቀሳ እንዲውል ከታዋቂው የእጽ አዘዋዋሪ ዮአኪን ‘ኤል ቻፖ’ ጉዝማን 1 ሚሊዮን ዶላር ተቀብሏል ይላሉ የአሜሪካ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ።

ጆአን ኦርናልዶ ህርናንዴዝ ላለፉት 8 ዓመታት የሆንዱራስ ፕሬዝደንት በሆኑበት ወቅት አደገኛ እጽ አዘዋዋሪዎች ምርመራ እንዳይከፈትባቸው፣ በቁጥጥር ሥር እንዳይውሉ እና ለአሜሪካ ተላልፈው እንዳይሰጡ በመከላከል በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር በጉቦ መልክ ይቀበሉ ነበር ተብሏል።

የቀድሞ ፕሬዝደንት ግን በተቻለኝ አቅም ሁሉ የእጽ ዝውውርን ስከላከል ቆይቻለሁ ይላሉ።

እአአ 2014 ላይ ፕሬዝደንት ሆነው የተመረጡት ህርናንዴዝ፤ በርካታ እጽ አዘዋዋሪዎችን ለአሜሪካ አሳልፌ በመስጠቴ የተበሳጩ እጽ አዘዋዋሪዎች በቂም በቀል ተነሳስተው መሠረተ ቢስ የሆኑ ማስረጃዎችን እያቀረቡብኝ ነው ይላሉ።

ህርናንዴዝ ባለፉት ሁለት ወራት በሆንዱራስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ቆይተዋል።

## በዩኬ ኮቪድ-19 በህሙማን ላይ የቆየበት ረጅሙ ጊዜ ከ16 ወር በላይ መሆኑን ምርመራዎች አመለከቱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሐኪሞቹ በኮቪድ-19 ተይዘው ሕክምና ያደረጉላቸው ህመምተኛ ከቫይረሱ ነጻ ሳይሆኑ በአጠቃላይ ለ16 ወራት ወይም ለ505 ቀናት እንደቆዩ ምርመራዎች እንዳመለከቱ ገልጸዋል።

ስማቸው ያልተጠቀሰው እኚህ ግለሰብ ሌላ ተጓዳኝ በሽታዎች የነበሩባቸው ሲሆን እአአ በ2021 ሆስፒታል ውስጥ ሕክምናቸውን እየተከታተሉ ይህችን ዓለም ተሰናብተዋል።

እኚህ ግለሰብ ለ16 ወራት ያህል በተመረመሩ ቁጥር ቫይረሱ ይገኝባቸው ነበር።

የለንደን የሕክምና ባለሙያዎች ለረጅም ጊዜ በቫይረሱ ተይዞ መቆየት እምብዛም የተለመደ አይደለም ይላሉ።

አብዛኛው ሰው በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅም ከቫይረሱ ነጻ ይሆናሉ። ነገር ግን ቀደም ሲል የተጠቀሱት ግለሰብ የነበራቸው በተፈጥሮ በሽታን የመከላከል አቅም እጅግ የተዳከመ ነበር።

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደዚህ ያሉ ስር የሰደዱ የሰውነት መቆጣቶችን ስለኮቪድ ያለን ግንዛቤ እና ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ለማሻሻል ጥናት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ ብለዋል።

ህመምተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ በኮቪድ-19 የተያዙት በ2020 መጀመሪያ ላይ ነበር። የበሽታው ምልክትም የነበራቸው ሲሆን በፒሲአር ምርመራ በቫይረሱ መያዛቸው ተረጋግጧል።

ከ72 ሳምንታት ለሚበልጥ በርካታ ጊዜ ለመደበኛ ምርመራ እና ለእንክብካቤ ሆስፒታል ሲገቡ እና ሲወጡ ነበር።

በአጠቃላይ ለ50 ጊዜ ያህል ምርመራ አድርገው ከቫይረሱ ነጻ አለመሆናቸው በምርመራ ተረጋግጧል።

የኪንግስ ኮሌጅ ለንደን እና ጋይስ ኤንድ ሴንት ቶማስ ኤንኤችኤስ ፋውንዴሽን ትረስት ሐኪሞች እንዳሉት ግለሰቡ በተደጋጋሚ በቫይረሱ የተያዙ ሳይሆን አንድ ጊዜ ተይዘው ለረዥም ጊዜ ከቫይረሱ ሳያገግሙ መቆየታቸውን ዝርዝር የሆነ ላብራቶሪ ምርምራ ትንታኔ አሳይቷል።

ህመምተኛው የፀረ ቫይረስ መድሃኒቶች ከወሰዱ በኋላ እንኳን ከበሽታው ማገገም አልቻሉም ነበር።



ይህ አንድ ግለሰብ ከቫይረሱ ነጻ መሆኑ ተረጋግጦ ምልክቶቹ ከማይጠፉበትና በቫይረሱ ለረዥም ጊዜ ተይዞ መቆየት ጋር የተለየ ነው።

በሕክምና ጉባዔ ላይ ስለግኝቶቹ ከሚያቀርቡት ሐኪሞቹ አንዱ በአውሮፓ ኮንግረንስ ክሊኒካል ማይክሮ ባዮሎጂ እና ተላላፊ በሽታዎች ሐኪም የሆኑት ዶክተር ሉኬ ብላግዶን ስኔል ናቸው።

ዶክተር ሉኬ “ከጉሮሮ የሚወሰድ ናሙና ምርመራ ይደረግ ነበር። ግለሰቡ ሁልጊዜ በተመረመሩ ቁጥር ከቫይረሱ ነጻ አለመሆናቸውን ያሳይ ነበር።

ህመምተኛው ከቫይረሱ ነጻ መሆናቸውን የሚያሳይ የምርመራ ውጤት ኖሯቸው አያውቅም። እናም ይህ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ በሽታ እንደሆነ መናገር እንችላለን። ምክንያቱም የቫይረሱ ዘረ መል ላይ ያደረግነው ተከታታይ ምርመራ ቫይረሱ በህመምተኛው ላይ የተለየ እና ወጥ የሆነ እንደሆነ አመላክቷል” ሲሉ ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ዶክተር ሉኬ “ሰዎች ለረጅም ጊዜ በቫይረሱ ተይዘው ሲቆዩ ቫይረሱ ከሰውነታቸው ጋር ይላመዳል። ይህም አዳዲስ ዝርያዎችን ለመከላከል አቅም እንዲያዳብሩ ሊያግዝ ይችላል” ብለዋል።

ምርመራ ካደረጉላቸው ዘጠኝ ታካሚዎች መካከልም አንዳቸውም በሌላ የቫይረስ ዝርያ አለመያዛቸውን ዶክተር ሉኬ ተናግረዋል።

ስር በሰደደ ኢንፌክሽን የተያዘ ሰው ቫይረሱን ለሌሎች ላያስተላልፍ እንደሚችልም ዶክተር ሉኬ አክለዋል።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ስቅለት በየቀኑ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

ሰሞኑን የስቅለት በዓል ላይ መሆናችንን ታሳቢ አድርገን፤ ስቅለት የወንጀለኛ መቅጫ ሆኖ የሚቀርብበት ዘመንን አስበን በሌብነት ላይ ስቅለትን በኢትዮጵያ ብንተገበር በየቀኑ ስንት ስቅለት ይኖር ይሆን? ከሚል ጥያቄ ይህን እንባባል።

አስቀድመን የሌብነትን ትርጉም እናንሳ። ሌብነት ምን ትርጉም ያስፈልገዋል ያው ሌብነት ነው ብሎ ከሚሰጠው ቀላል ትርጉም ወደ ተጨባጭ ከእለት ወደ እለት ትርጉም እንውሰደው። ከህጻን እስከአዋቂ በቀላሉ የሚረዱትን ነገር እንዴት ጥያቄ አድርጎ ማቅረብ አስፈለገም ያስብልም ይሆናል።

ፋብሪካው ውስጥ ክርክሩ ጦፏል። እንደሚታሰበው ሁሉም የሌብነትን ትርጉም የተረዳ በሚመስልበት ሁኔታ ውስጥ አንድ ሰው የለም ትርጉማችን ይለያያል ሲል በዙሪያው ካሉት ጋር ሙግት ገጠመ። አብረው ምሳ የሚበሉ በሻይ ሰዓትም ሰብሰብ ብለው አውጥተው የሚያወርዱ የአንድ ፋብሪካ ሰራተኞች ናቸው። አመታትን በፋብሪካው ውስጥ ቆይተው በህይወታቸው ብዙ ነገሮችን አሳልፈዋል። አንዳቸው ስለሌላቸው ታሪክ ቁጭ ብለው እንዲመለከቱ አስቀድመው የተወሰኑ እንደሆኑ እስኪቆጥሩ ድረስ ረጅምን የህይወት ጉዞ አብረው ዘልቀዋል። መኖሪያቤታቸው ፋብሪካውን ታሳቢ አድርጎ በተሰራው ካምፕ ውስጥ ነው። ከፋብሪካው ወደ ቤት፤ ከቤት ወደ ፋብሪካው ሲሄዱ የታክሲ ወጪ የሌለባቸው አብረው ውለው አብረው በተመሳሳይ እርቀት ላይ የሚያድሩ የሥራ ባልደረቦችና የአንድ መንደር ነዋሪዎች ናቸው።

ክርክራቸው የሌብነት ትርጉምን በመፈለግ አቅጣጫ ላይ ነው። የሌብነት ትርጉማችን አንድ አይደለም የሚለው ባልደረባቸው የታዘበውን ከውስጡ አድርጎ ስለሌብነት ብዙ ያስባል፤ ብዙም ይናገራል። "ልጅ እያለን እርስበእርስ ቀላል የሆኑ ነገሮችን እንሰራረቅ ነበር፤ ካደግን በኋላ ደግሞ እድሚያችንን የሚመጥን መሰራረቅን እንሰርቃለን" ይላል። "አንዳንዱ ስርቆትን ሲያስብ የሚያስበው ሙሰኛውን ብቻ ነው። አዎ፤ ሙሰኛው ሌባ ነው። ነገርግን ከትልቁ ሌባ መለስ በብርም ከብር ውጪም በሆነ መንገድ የሌብነት ትርጉም ውስጥ የምንገኝ ብዙ ነን ብሎ ያስባል። ማንስ ነው ከሌብነት ራሱን የጸዳ እንደሆነ አድርጎ የሚያስብ?" ብሎም ይሞግታል። "የቢሮ ሰዓት ፌስቡክ ለማየት እኮ ስርቆት ነው፤" ይላል።

"ድርጅቱ የወር ደሞዝ ወርን ጠብቆ ሲከፍል የደሞዝ መክፈያ መለኪያ ያደረገው ጊዜን ነው። ጊዜ መለኪያ ካልተደረገ የወሩ ድምር የስራ ሰዓታት ለድርጅቱ የተሸጡ ናቸው ማለት ነው። ይህን የተሸጠ ሰዓት ለግል ጉዳይ መጠቀም ሌብነት ነው፤ ትርጉም ያልተሰጠው ሌብነት። በሌብነት መዝገበቃል ውስጥ በግልጽ የማይታይ ነገርግን በድምር ውጤቱን አገርንም ሆነ ተቋምን ብዙ የሚያከስር ሌብነት። በአንድ የተሸጠ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ የማይመለከተው አካል ገብቶ ማስታወቂያውን ቢያስነገር ስርቆት ነው፤ ምክንያቱም የከፈለበት ሳይሆን ያልከፈለበት ማስታወቂያ የተስተናገደ ስለሆነ። የድርጅት ሰዓትም ለድርጅቱ ዓላማ ብቻ አለማዋል በቅጡ ለሚያስብ ሰው ስርቆት ስለመሆኑ አስረጂ አያስፈልገውም።" ይላል የክርክር ድምቀት የሆነው የማህበረሰብ ንቃት መጨመር ለለውጥ ትልቅ እምነት እንዳለው የሚያምነው የፋብሪካው ሰራተኛ።

ከድርጅት ሰዓት ባሻገር ሌብነትን ሊያሳዩ የሚችሉ አያሌ ተግባራት በየቀኑ እንደሚፈጸሙ አንባቢው ልብ ሊለው ይችላል። ለሌብነት ክፍያው ስቅላት ቢሆን በየቀኑ ስንት ሰው ይሰቀል ይሆን ለሚለው ጥያቄ ግላዊ ምላሻችንን ዳግም እየመረመርን ሌባው መጀመሪያ የሚሰርቀው ራሱን መሆኑን እናንሳ።

### ሌባው ራሱን ሲሰርቅ

"ሌባው ማንን ይሰርቃል?" ቢባል ትክክለኛው መልስ "እራሱን ነው" ይላል የምናብ ታሪካችን የፋብሪካው ሰራተኛ።

የሌብነት ድምር ውጤት ከራስ ላይ መስረቅ ቢሆንም በሌባው አዕምሮ የተሳለው ተቃራኒው ስለሆነ ሌብነቱን ባሳካ ጊዜ ውጤት ያስቆጠረ እንደሆነ ያስባል። ስለትንሹም ሆነ ስለትልቁ ሌባ አንስተን ብናወራ በጊዜ ሂደት ውስጥ ያለው ውጤቱ ከራስ ሰርቆ መገኘትን እንደሆነ እንረዳለን።

ጥቂት ማሳያዎችን አንስተን ጥያቄውን ለአንባቢው እናቅርብ። በትዳሩ ላይ የማገጠ ሰው የፈጸመው የመማገጥ ተግባር ዛሬ ነገ ታወቀብኝ እያለ በስጋት ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል። ነገርዬው የታወቀ ቀን ደግሞ በቤቱ ውስጥ የፈራው ነገር ሆኖ ይመለከታል። የፈራው በሆነ ጊዜ ሁሉም በቀረብኝ ሲል የሚቆጥራቸው የረዘሙ ቀናት ይወለዱበታል፤ የጸጸት ቀናት። በትዳሩ የማገጠው ሰው በስተመጨረሻ የሰረቀው ከማን ነው?። የራሱን የልብ መተማመን ማጣት ስርቆቱ ከማን መሆኑን ያሳያል? የራሱን በሰላም ትዳሩን መምራት አለመቻል ዋናው ተሰራቂ ማን እንደሆነ ይነግረናል? የራሱን በቤተሰቡ ውስጥ በነጻነት መኖርን ሲነፈግ በተጨባጭ ተጎጂ ሆኖ የሚገኘው ማን እንደሆነ ያሳያል? አንባቢው ራሱን በዚህ ሰው ቦታ ላይ አድርጎ ይመልከትና ሌባው ከማን እንደሰረቀ ብያኔን ይስጥ። ጸሃፊው ግን ሌባው ራሱን እንደሰረቀ ያምናል።

በሥራ ቦታው በግዢ ስራ ላይ የተሰማራ ግለሰብ በግዢ ሂደቱ ላይ በሌብነት ነገሮችን የሚያከናወን ቢሆን፤ በሌብነት እጁ ስለሚገባው እቃ ብሎ ያልሆነ ነገር እንዲገዛ የሚያደርግ ቢሆን፤ እውን ይህ ሰው ስለስራው በልበሙሉነት በባልደረቦቹ ፊት መመላለስ ይችላል? እውን በቅርቡ ያሉ ሰዎች የሚያደርገውን የማያውቁ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል አለ? የሚያውቁ ቢሆን ምናልባትም የሚተባበሩት እንዲሁ እኒህ ሰዎች ስለሞራል፣ ስለ ህግ የበላይነት፣ ስለ ስፖርት፣ ስለ እምነት፣ ስለ ትዳር ወዘተ አብረው መነጋገርና መወያየት ይችላሉ? እናሳ እኒህ ሰዎች የተሰረቀባቸው በነጻነት ሃሳብን የመከፋፈል፤ በሰው ፊት ሰው ሆኖ የመታየት ነገርስ በምን ይመለሳል?

ለአንድ ሥራ ብቁ ያልሆነ ሰው በዘመድ በኩል ወይንም በሌላ እጅ መንሻ አንድ መስሪያቤት ውስጥ ቢቀጠር፤ ዛሬ ነገ ሚስጥሬ ታወቀ ከሚለው ስጋት ጀምሮ በብቃት ባልተገኘበት ስራ ውስጥ በሚፈጥረው ጉድለትና የስራ ጥራት ማነስ ምክንያት ወዘተ የሚኖረው በልበሙኑት ስራውን አለመስራት ስርቆት የተከናወነው በማን ላይ ነው?

እጅግ የበዙ የስርቆት ማሳያዋችን መደርደር እንችላለን። የስርቆትን ትርጉም በሚገልጸው ደረጃ አድርገን ስንመለከት መዳረሻው ተሰራቂው ጋር ስንደርስ ሌባው ባሰበበት ተቃራኒ ተሰራቂውን እናገኘዋለን። አዎ፤ ሌባው በዚህ ሂደት ውስጥ የሚያገኘው ነገር ይኖራል፤ ነገርግን በመሰረታዊነት ሌባው ራሱ ተሰራቂ ነው። ሌባው ሰላሙን፣ ጤንነቱን፣ ከሰዎች ጋር ያለውን መስተጋብር፣ በልበሙሉነት አንድን ነገር ቀርጾ የመንቀሳቀስ አቅምን፣ እድገትን፣ የሞራል ልእልናን፣ ወዘተ የሚሰርቅ ነው። ሰዎች እኒዚህን ነገሮችን ከተሰረቁ ራሳቸውን በመጠጥና በአጉል ነገሮች ውስጥ የመደበቅ መንገድን የሚከተሉ ስለሆነ በቀኝ እጁ የተቀበለውን ገንዘብ በግራ እጁ ያወጣዋል። በጊዜ ሂደት የእኒህ ነገሮች የጤናና የቤተሰብ መዋቅርን የማዳከምና የማፍረስ እንዲሁም የህይወትን አቅጣጫም የሚቀይሩ ሆነው ይገኛሉ። አዎን ሌባ ሌላውን ይሰርቃል፤ በዋናነት ግን ራሱን ይሰርቃል! አንባቢው ደጋግሞ ለራሱ ይበለው፤ አዎን ሌባ ሌላውን ይሰርቃል፤ በዋናነት ግን ራሱን ይሰርቃል!!

### የወረቀት ላይ ሌብነት

ባለንበት ዘመን ሙያዊነት እያደገ የመጣበትን ሁኔታን በጉልህ እናስተውላለን። ስራዎችን በሚመለከተው ባለሙያ ለማሰራት ለባለሙያ የመክፈል ባህል እየመጣ ነው። በጠቅላላ እውቀት ስራዎችን ከመስራት ሙያን ማእከል አድርጎ በትኩረት መስራት የተሻለ አሰራር መሆኑም በሰፊው ተቀባይነት ያገኘም ይመስላል።

ከሙያዊ እድገት ጋር አብሮ እያደገ የመጣው ሙያዊ የወረቀት ላይ ሌብነት ነው። ባልተገባ መንገድ የተዘረፈን ገንዘብ፤ ኦዲተር እንዳያገኘው በሚያስችል ሁኔታ ሙያን ተጠቅሞ ወረቀት ሲሰራለት እርሱ ወረቀት አገዝ ሌብነት ልንለው እንገደዳለን። አንድ ድርጅት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓትን ተግብሮ ነገርግን የቁጥጥር ስርዓቱ ሌብነትን መያዝ እንዳይችል የሚያደርግ የወረቀት ላይ ሌብነት የበረከተበት ዘመን ውስጥ እንገኛለን። በአለምአቀፍ ትልልቅ ተቋማት ላይ የሚሰሙ የምርመራ ሪፖርቶች ሙያን ተገን ያደረጉ የበረከቱ ቅሌቶች/scandals የሚያጋጥሙ መሆኑን ነው። ወደ አገራችን የተለመደው የቁጥጥር ስርዓትን አልፎ የሚሰራውን ስርቆት ከሚያሳዩት መካከል የፕሮፎርማ ስርዓት ተጠቃሽ ነው። ሦስት ፕሮፎርማ ሰብስቦ የተሻለ ዋጋ ሊሰጥ የሚችልን ለማግኘት የተዘረጋ ስርዓት ከአንድ ነጋዴ ሶስት ፕሮፎርማ በማግኘት የቁጥጥር ስርዓቱ እንዳይሰራ ማድረግ እንደ ማሳያ ሊቀርብ የሚችል ነው። በየህክምና ባለሙያ ገቢውን ለመጨመር ሲል በሙያዊ መረዳቱ የማያምንበትን ምርመራ እንደሚያዝ የሚቀርበው ወቀሳ አድማሱ የሰፋ ነው። ይህም ሌላው የወረቀት አገዝ ሌብነት ማሳያ ነው። በምህንድስና፣ በመንገድ ስራው፣ በባንኮች የብድር አሰጣጥ ስርዓት ውስጥ ወዘተ የሚከናወነውን ስንመለከት የምናየው የወረቀት ላይ ሌብነት መዋቅራዊ እየሆነ መምጣቱን ነው።

የመንግሥት፣ የህዝብ እንዲሁም የግል ተቋማት እንዴት አድርገው የወረቀት ላይ ሌብነትን ለማስቀረት አስበው የማይሰሩ ከሆነ በወረቀት ጋጋታ ውስጥ ሌብነት ስር እየሰደደ፤ ለሌብነት የሚመች ከባቢ እየተፈጠረ ይሄዳል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ መንገድ ላይ ሞባይል መንትፎ ከሚሮጠው ቀማኛ በከፋ ሁኔታ ከረባት አድርጎ፤ በንግግሩ መካከል የእንግሊዘኛ ቃል ጣል ጣል የሚያደርግ ወረቀት አገዝ ሌብነትን የሚያደርግ አንቱታ የተሰጠው ሰው ከፍተኛ ነው። ለአንድ ስራ ውል እስከመግባት ጀምሮ እስከ ውሉ አፈጻጸም ድረስ የወረቀት አገዝ ሌብነት በስፋት ይተገበራል። መፍትሔውን ማሰብ እንደ አገር በሌብነት ምክንያት የከፋው ላይ ከመድረስ በፊት ያግዛል።

የሌብነት መስፋት እንደ መንስኤ ከሚቀርቡት ነጥቦች መካከል የግብረገብ ትምህርት አለመኖር፣ የእምነት ተቋማት በተከታታዮቻቸው ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ማሳደር አለመቻል፣ አገራዊው የስልጣን አያያዝ ሂደት ከመነሻው በሌብነት ላይ የተመሰረተ መሆን፣ የኢኮኖሚ እድገት ውስንነትና የሰው ልጅ የሚካፈለው ሃብት እያነሰ መምጣት ወዘተ ተብሎ ይቀርባሉ። ከመነሻው ሥልጣን ሲሰራ የሚለውን ነጥብ እናንሳና ሌሎቹን በሌሎች ጊዜዎች ልናነሳቸው እንደምንችል በማሰብ ወደ ማጠቃለያው እንቃረብ።

### ከመነሻው ሥልጣን ሲሰራ

በአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ ሁሉም ስርዓቶች ተገጣጥመው በአንድ ሳንባ መተንፈስ ወደሚችሉበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ህዝብ የሚተዳደርባቸው ስልጣኖች በግልጽነትና ከሌብነት በጸዳ መንገድ መያዝ እንዳለበት ይታመናል፤ በአገራችንም ህገመንግሥት ውስጥ ይህን ለማሳካት የሚያስችል ድንጋጌዎች ይገኛሉ።

የአንድ አገር ህዝብን ማገልገያ ስልጣን የሚሰራበት መንገድ በማህበረሰቡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊእንቅስቃሴላይጉልህየሆነተጽእኖያለውመኖሩ ማህበረሰቡ የሚከተለው እሴትን በሰፊው ለመግራት እድልን ይሰጣል። በህዝብ ይሁንታ የተሰራ ስልጣን በህዝብ ይሁንታ እንደሚወርድ ሲታሰብ የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴውም ከሌብነት የጸዳ የመሆን እድሉ ሰፊ እንደሆነ በርካታ የምርምር ስራዎች ያሳያሉ።

በየደረጃው ውሳኔ ሰጪነት የሚመነጭበት ስልጣን ምንጩ ብቃት ሲሆን፤ መውጫና መውረጃው ነጥቡ ውጤት ሲሆን በጤናማ መንገድ ስልጣንን ለመስራት የሚረዳ ሆኖ ይታያል። በጤናማነት ስልጣን ባልተሰራበት ሁኔታ የሚፈጠረው የሌብነት ደረጃ መዋቅራዊ እንዲሁም የቢሮክራሲው አንድ አካል ተደርጎ ሊጠቀስም ይችላል።

ግልጽነት በሰፈነበት አሰራር ውስጥ ሌብነት እድል ስለማያገኝ ሌብነት እየቀጨጨ የመሄድ እድል አለው።



ከዓለማችን የትላንት እንዲሁም የአሁን ዘመን ታሪክ የምንረዳው ስልጣን በቤተሰብ ደረጃ በተያዘበት ሁኔታ ስልጣን በእጁ ያለቤተሰብ ስልጣንን እንዳሻው የመጠቀም እድሉ ሰፊ ስለሆነ ስርቆት በተቀናጀ ሁኔታ በቤተሰቡ ኔትዎርክ ሊመራ እንደሚችል ነው። ግልጽነት በቤተሰቡ ቁጥጥር ውስጥ ስለሚገባ ማለት ነው። አምባገነን መንግሥታት ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ ከቤተሰብ በከፋ ሁኔታ ገዢው ቡድን ስርዓት ውስጥ ያሉ ሰዎች ስልጣንን በመጠቀም በሌብነት ውስጥ በሙሉ አካላቸው ለመገኘት በሚያደርጉት ሂደት ሌብነት እውቅና የተሰጠው የተወሰኑ አካላት ሙብት ሆኖም ይገኛል። ህዝብ በገዛ ፈቃዱ መሪውን የሚመርጥበትና የሚያወርድበት ስርዓት እስካልተረጋገጠ ድረስ ሥልጣን የሚሰራበት መንገድ ለሌብነት የራሱን አስተዋጾ ማድረጉን ይቀጥላል።

ዛሬ እንደ አገር የገባንበት ቢሮክራሲውን የተቆጣጠረው ሌብነት ላይ መፍትሔ እንዲመጣ ስልጣንን በንጽህናና በግልጽ መንገድ የመያዝ ባህልን ለማዳበር መስራት ይኖርብናል። ወጣቶቻችንን ነገ አገራቸውን ወደ መልካም ለመምራት ህልም የሚያደርጉት ዛሬ ያለውን በመመልከት መሆኑን በመረዳት። የመፍትሔው መንገድ ትውልድ ተኮር ሊሆን የተገባው ነውና።

### ትውልድ ተኮር መፍትሔውን ሳይውል ሳያድር

ትላንት ሌብነትን በስቅላት ፍርድ ለመከላከል የሞከሩ አሉ። በአገራችንም ሌብነትን መጸየፍ እንዲቻል ሌባው የሰረቀውን እየተናገረ በህዝብ መካከል እንዲንቀሳቀስ ይደረግ እንደነበር ታሪካችን ይነግረናል። ያለፈው ትውልድ ሌብነት በተለያዩ መንገዶች ለመከላከል ያደረገው ጥረት ያመጣለትን ውጤት በመመርመር ለአሁኑ ሊወሰድ የሚገባውን ትምህርት ማግኘት ያስፈልጋል።

ትውልድ ተኮር መፍትሔን ለአገራችን ለመፈለግ ስናስብ ዛሬ ላይ በዙሪያችን ያሉትን እንዲሁም በእናታቸው ሆድ ውስጥ ያሉትን በተጨባጭ እያሰብን መሆን አለብን። ትውልድ ተኮር መፍትሔን በምናስብበት ጊዜ ማህበረሰባዊ ለውጥ በጥቂት ሰዎች ብቻ የሚመጣ ባለመሆኑ በሰፊው መስራት እንዳለብንም የሚያሳይ ነው።

ማህበረሰብ እንደ ማህበረሰብ ለውጥ ያስፈልገዋል ሲባል በእውቀት የሆነ ለውጥ መሆኑ እሙን ነው። ሌብነትን አሰቃቂ ከሆነ ፍርድ በላይ በእውቀትና በመረዳት ለመቀየር መሞከር አዋጭ ይመስላል። ይህ ማለት በሌብነት ውስጥ እንዳሻቸው እየኖሩ ያሉትን የማእረግ ስም እየሰጠን ባሉበት እንዲቀጥሉ እንፍቀድ ማለት ግን አይደለም። እነርሱን ወደ መስቀል እንሂድ ብንል ደግሞ ስቅለት በየቀኑ ስለሚሆን። በየቀኑ ብቻም ሳይሆን በየደቂቃውም፤ በየሰከንዱም ሊሆን ስለሚችል፡!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ከመቀጠር ብዙዎችን ወደመቅጠር

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ትውልድና እድገቷ የሸመና ባለሙያዎች ጥበባቸውን ከሚያፈሱበት ሰፈር፤ እጹብ ድንቅ የሆነው የእጅ ሥራዎቻቸው ሞልቶ ከተትረፈረፈበት ከጥበበኞቹ ደጃፍ ሽሮ ሜዳ ነው። የአገር ባህል አልባሳቱ በአይነት በአይነቱ በሚመረትበት አካባቢ ተወልዳ አድጋለች። ባህር በሆነው የሸመና መንደር ተወልዳ እንደማደጓ የአገር ባህል አልባሳትን ማምረት ባትችልም ተቀራራቢ በሆነው የጋርመንት ሥራ ተሰማርታ ውጤታማ መሆን ችላለች።

በወቅቱ ውጤት ሳይመጣላቸው እንደቀሩት እንደ አብዛኛው ተማሪ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም መግባት አልቻለችም። በውጤቷ ምክንያት በትምህርቷ ባትገፋም ለዛሬ ማንነቷ መሰረት የጣለላትን የጋርመንት ሥራ ለመሥራት ግን አላገታትም። እንዲያውም ከመቀጠር አልፋ ሌሎችን መቅጠር እንድትችል ሁነኛ ምክንያት ሆኗታል። ቤት ከመቀመጥ ውላ መግባትን ምርጫ በማድረጓ ሥራ ሳትንቅ በአንድ የጋርመንት ድርጅት ውስጥ ከስፌት ሥራ በጣም ቀላሉና ብዙም ልምድ በማይጠይቀው ረዳት ቀንጫቢ በመሆን በግለሰብ ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ ሰርታለች። በዚሁ ድርጅት ውስጥ ተቀጥራ መሥራት ለመቻሏም ወላጅ እናቷ ምክንያት ነበሩ። ወላጅ እናቷ የድርጅቱን ባለቤት ያውቁት ኖሯልና ልጃቸውን ቀጥሮ እንዲያሰራት ተማጽነውታል።

ተቀጥራ የመሥራት አጋጣሚውን በማግኘቷ በድርጅት ውስጥ የሚሰሩ የተለያዩ ሥራዎችን በመልመድ ሙያዋን ከጊዜ ወደ ጊዜ አሻሽላለች። እራሷን የመለወጥ ትልቅ ፍላጎት የነበራት በመሆኑም በድርጅቱ የሚመረቱ ምርቶችን ልቅም አድርጋ በማወቅ የራሷን ድርጅት ለመክፈት የሚያስችላትን ሞያና ገንዘብ ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች። ጥረቷም ፍሬ አፍርቶ በአንድ የስፌት መኪና የጀመረችው የልብስ ስፌት ሥራ በአሁን ወቅት ወደ ድርጅት አድጎ ከራሷ አልፋ ለብዙዎች የሥራ ዕድል መፍጠር አስችሏታል።

በአንድ የስፌት መኪና በቤቷ ውስጥ ሥራ የጀመረችውና ዛሬ ላይ ከ160 በላይ የስፌት መኪናዎችን እንዲሁም ለጋርመንት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ማሽኖችን ማትረፍ የቻለችው የዕለቱ የስኬት እንግዳችን ወይዘሮ ሀረጓ ወንድማገኝ የሀረጓ ጋርመንት ዋና ሥራ አስኪያጅ ናት። ሀረጓ ወደ ሥራው ስትገባ በቀዳሚነት ተቀጥራ ትሰራበት ከነበረበት ድርጅት ጤናማ በሆነ መንገድ በመሰናበቷ ድርጅቱ ያመረታቸውን የተለያዩ ምርቶች በማሻሻጥና አለፍ ሲልም ተመሳሳዩን የማምረት ጥሩ ዕድል ገጥሟታል።

በድርጅቱ በስፋት ይመረት የነበረው የቦቲ ጫማ ገበር መሆኑን ያስታወሰችው ሀረጓ፤ ተመሳሳዩን በማምረት ለገበያ ማቅረብ ቀዳሚ ሥራዋ ነበር። በወቅቱ ሁለት ሰራተኞችን ቀጥራ በመኖሪያ ቤቷ ታሰራ የነበረው የቦቲ ጫማ ገበር ሥራ እንዲሁም ሌሎች የልብስ ስፌት ሥራዎች እየተስፋፉ በመምጣታቸው የመሥሪያ ቦታ እጥረት አጋጥሟታል። በመኖሪያ ቤቷ ግቢ ውስጥ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የሰራችው የመስሪያ ቦታ ከጥበቱ በላይ ሙቀቱ ለሥራ ምቹ አልነበረምና ለምትኖርበት ወረዳ ችግሯን አስረድታለች።

የአቃቂ ቃሊቲ ወረዳ ሰባት ጽህፈት ቤትም አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት መቻሏን ካረጋገጠ በኋላ 160 ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ አስረክቧታል። በዚህ ጊዜ ታድያ ሀረጓ በስሯ የነበሩ ሁለት ሠራተኞች ላይ 28 ሠራተኞችን ጨምራ በድምሩ 30 ሠራተኞች ነበሯት። 30 ሠራተኞችን ይዛ በ160 ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ ውስጥ ምርቶቿን ማምረት ቀጠለች። የተለያዩ የህጻናትና የአዋቂ አልባሳትን በጥራት እያመረተች ለገበያ ስታቀርብ ዕለት ዕለት ሥራው ውጤታማ መሆን ቻለ። በዚህ ጊዜ ታድያ 160 ካሬ ሜትር ሼድ አልበቃትምና ማስፋፊያ እየጠየቀች በአሁን ወቅት 408 ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ ውስጥ 160 ሠራተኞችን ይዛ እየሠራች ትገኛለች።

600 ብር በተገዛች አንዲት ሲንጀር የስፌት መኪና የተጀመረው የሀረጓ ጋርመንት ከአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ከአምስት ሺ ብር ጀምሮ እስከ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺ ብር ድረስ በመበደር ሥራውን ማስፋፋት ችላለች። በአሁን ወቅትም ብድሯን በመመለስ ከማምረቻ ማሽኖች በተጨማሪ ከሶስት ሚሊዮን ካፒታል በላይ ሃብት ማፍራት የቻለችው ሀረጓ፤ እዚህ ደረጃ ለመድረሷ ከፍተኛው ድርሻ የግል ጥረቷ ቢሆንም፤



ሴት ነጋዴዎችን በመደገፍ የተሰማሩበትን የንግድ ሥራ ማስፋፋት እንዲችሉ የገንዘብ ብድር እንዲሁም የተለያዩ ስለልጠናዎችን በመስጠት የሚታወቀው የሴቶች ልማት ፕሮጀክት ከፍተኛ ድርሻ የነበረው መሆኑን አጫውታናለች።

በሀረጓ ጋርመንት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሰራተኞች ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ሲሆኑ በተለይም ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና በዘርፉ የሰለጠኑ ይገኙበታል። በድርጅቱ ከ120 በላይ የስፌት መኪናዎች ያሉ ሲሆን በስፌት መኪናው ከሚሰሩት ባለሙያዎች በተጨማሪ በቆራጭነት፣ በመዘምዘም፣ በረዳትነትና በሌሎች ሥራዎችም የተሰማሩ አሉ። በድርጅቱ ከስፌት መኪናዎች በተጨማሪ በቦታ ጥበት ምክንያት ከሥራ ውጭ ሆነው የተቀመጡ 37 ዘመናዊ ማሽኖች መኖራቸውን የጠቀሰችው ሀረጓ፤ ድርጅቱ አሁን ካረፈበት 408 ካሬ ሜትር ቦታ ተጨማሪ ማግኘት ከቻለ ማሽኖቹን ወደ ሥራ በማስገባት ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚቻል ትናግራለች።

ከሥራ ውጭ ሆነው የተቀመጡት 37 ዘመናዊ ማሽኖች አቨር ሎክንና ኢንተር ሎክን ጨምሮ ለጋርመንት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች መሥራት የሚችሉ ናቸው። ይሁን እንጂ ከዚህ ውጭ ባሉት ከ120 በላይ የስፌት መኪናዎች ግን ማንኛውንም አልባሳት በጥራት በማምረት ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። ጅንስን ጨምሮ ገበያው የጠየቀውን ሁሉ ማምረት እንደሚችሉ የገለጸችው ሀረጓ፤ በዋናነት የተለያዩ የሥፖርት ማሊያዎችን፣ ፖሎ ቲሸርቶችን፣ ሱሪ፣ ሸሚዝና ሌሎችን ይመረታሉ። በአብዛኛው ደንበኞች የሚፈልጉትን አልባሳት በሚሰጡት ትዕዛዝ መሰረት የሚያመርቱ ቢሆንም የሀረጓ ጋርመንት መለያ የሆኑ የተለያዩ ቁምጣዎችን አምርቶ ገበያ የሚጠብቅበት ሂደትም አለ።

በሀረጓ ጋርመንት በአብዛኛው ከሚቀጠሩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተማሪዎች በተጨማሪ ምንም የማያውቁ ሠራተኞች በቅንጫባና በረዳትነት ገብተው ስፌት ደራጃ ላይ የደረሱ ሠራተኞች ስለመኖራቸው ሀረጓ አጫውታናለች። በተለይም እራሷ ቆማ ያሰለጠነቻቸው ሠራተኞች ዛሬ ላይ እራሳቸውን ችለው የሚሰፉና የሚቆርጡ ስለመሆናቸው ትናገራለች። ለዚህም ዋነኛ ምክንያቷ የሠራተኞቹ ባህሪና ለሥራው ያላቸው ፍላጎትና የማወቅ ጉጉት ሲሆን ደሞዛቸው እየተከፈላቸው የሥራ ላይ ስልጠና ወስደው የሥራና የደምወዝ ዕድገት በማግኘት እየሠሩ ያሉ በርካቶች ናቸው።

‹‹የምናመርታቸውን ምርቶች በጥራት አምርቶ ተወዳዳሪ ለመሆን እየተጋን ነው›› የምትለው ሀረጓ፤ በተለይም ወደ ውጭ የሚላኩ አልባሳትን ማምረት የሚያስችል ደረጃቸውን የጠበቁ የተለያዩ ስልጠናዎችን ያገኘች እንደመሆኗ በአሁን ወቅት ጥራት ያላቸውን ልብሶች በስፋት በማምረት ከአገር ውስጥ አልፎ ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ ዕቅድ አላት። ለዚህም ሲባል ለሠራተኞቿ የተለያዩ ስልጠናዎችን ማለትም በጥራት፣ በጊዜ ማድረስንና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ልምዶችን ለማካፈል ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር እየሰራች ትገኛለች።

በአገር ውስጥ የሚመረቱ አልባሳት ከውጭ አገር ከሚገባው ጋር ሲነጻጸር ብዙም ልዩነት የሌለውና አንዳንድ ጊዜ የአገር ውስጥ ምርት የሚበልጥበትንና የአገር ውስጥ ምርት በውጭው ዓለም ገበያ ላይ እንደሚገኝ አጋጣሚዋን ስታጫውተን፤ ከዱባይ አገር ተገዝተው ወደ አገር ቤት ከመጡ አልባሳት መካከል በኢትዮጵያ የተመረተ የሚል መለያ ያለው ልብስ ያጋጠማት ጓደኛዋ መኖሯን አስታውሳ ማህበረሰቡ በአገር ውስጥ ምርት እንዲኮራ ጥሪ አቅርባለች። በአገር ውስጥ መጠቀም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው ያለችው ሀረጓ፤ የሚመረቱት ምርቶችም ጥራት ያላቸውና ከውጭው የሚተናነሱ አለመሆናቸውንና ማህበረሰቡም ግንዛቤ የሌለው እንደሆነ አንስታለች።

ደንበኛው እንዲሰራለት የሚያዘው የልብስ አይነት በብዛት የውጭ አገር አልባሳት ሲሆን ለአብነትም በውጭ አገር የተመረተ አንድ ቲሸርት በማምጣት አስመስለው እንዲሰሩ ይጠየቃሉ። በተጠየቁት መሰረትም ምንም አይነት ልዩነት ሳይኖረው አምርተው እንደሚያስረክቡ የገለጸችው ሀረጓ፤ እንዲያውም የጎደለውን በመሙላት በተሻለ ጥራት የሚመረት መሆኑን ትናገራለች። በተለይም ከቻይና ታሽገው የሚመጡ የህጻናት አልባሳትን በምሳሌነት በማንሳት በጥራት የማይመረት እንደሆነና እጁ አልያም አንገቱ የሚጠብበትና እጅግ በጣም የሚሰፋበት አጋጣሚ እንዳለም ጠቁማለች።

ታድያ እንዲህ ያሉ ምርቶችን ስንመለከት በአገር ውስጥ የሚመረቱ አልባሳት ጥራት ያላቸው ለመሆናቸው ምስክሮች ነን የምትለው ሀረጓ፤ ደንበኞች ለማሳያነት የሚያመጡትን ልብስ ሳይቀር ጥራት ጨምረው የሚያመርቱ መሆናቸውን ትናገራለች። ምርቶቹን ለማምረት አስፈላጊ የሆነው ግብአትም በዋናነት ክር ሲሆን ክሩ የሚገኘው ከነጋዴ እንደመሆኑ ዋጋው በየጊዜው ይቀያየራል። ይሁን እንጂ አሉ የተባሉ ችግሮችን በመቋቋም ሀረጓ ጋርመንት ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል እንዲችል ምርቶቹን በብዛትና በጥራት እያመረተ ይገኛል።

በጥራትና በብዛት የሚመረቱት የሀረጓ ጋርመንት ምርቶች የገበያ መዳረሻቸው በዋናት መርካቶና ኮልፌ ገበያ ላይ የሚገኙ ነጋዴዎች ናቸው። ጅምላ ነጋዴዎቹ የፈለጉትን የአልባሳት አይነት በሚፈልጉት መጠን ያዛሉ። ምርቱን ተረክበውም በችርቻሮ ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን ከጅምላ ነጋዴዎች ተረክበውም በየአካባቢው የሚሸጡ ነጋዴዎች አሉ።

ቤት ከመዋል ወጣ ገባ ማለት መልካም ነው ብላ የጀመረችው የቅንጨባ ሥራ ሙያ እንድትማር ዕድል ከፍቶላታል። የቀሰመችውን ሙያም በተግባር ለመዋልና ተጠቅማ ሌሎችን ለመጥቀም ጊዜ አላጠፋችምና የጋርመንት ሥራዋን በቤቷ ውስጥ ከጀመረች ከአስር ዓመታት በላይ አስቆጥራለች። ከጊዜ ወደ ጊዜም ሥራዋን እያሻሻለችና እያስፋፋች ከሁለት ሶስት፤ ከአስር ሃያ ሰላሳ እያለች ለ160 ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለችው ሀረጓ፤ ለሥራው ጥልቅ ፍቅር ያላት መሆኑን በመግለጽ በዘርፉ በርካታ ችግሮችን ተጋፍጣ ማለፍ መቻሏንም ትናገራች።

ወደ ድርጅቷ የምታቀናው ገና በማለዳ ሠራተኞች ሳይገቡ ሲሆን ሠራተኞች ከገቡ በኋላ አርፍዳ ስትገባ እንኳን ምቾት የማይሰማት ሀረጓ፤ ለሥራዋ የተለየ ፍላጎትና አክብሮት ያላት መሆኑን በመግለጽ፤ ውጤታማ መሆን የቻለችውም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ታምናለች። ማንኛውም ሰው ሥራውን ወዶትና ፈልጎት መሥራት አለበትም ትላለች።

ማህበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር በወረዳዋ የተለያዩ ድጋፎችን በተለይም ችግረኛ ለሆኑ ህጻናትና ሴቶች የአቅሟን ታደርጋለች። አገራዊ በሆኑ ማንኛውም ጥሪዎችም እንዲሁ ምላሽ በመስጠት ኃላፊነቷን ትወጣለች። በቀጣይም ባላት አቅም ሁሉ ማህበረሰቧን የማገልገልና አገራዊ ለሆኑ ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ወደኋላ የማትል መሆኗን አረጋግጣልናለች።

በመጨረሻም ሰዎች በማንኛውም የሥራ ዘርፍ ውጤታማ መሆን ከፈለጉ ከትንሹ ሊጀምሩ ይገባል። የምትለው ሀረጓ፤ ከትንሽ መነሳት ትልቁ ያደርሳል በማለት በተለይም ወጣቱ፤ ፍላጎቱንና ውስጡ ያለውን ክህሎት በመረዳት ራዕይ ሰንቆ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባና ሥራን ሳይንቅ እንዲሠራና እንዲለወጥ ትመክራለች። ታድያ በየትኛውም መንገድ ሲጓዙ ብዙ ተስፋ አስቆራጭ የሆኑ ነገሮች ቢገጥሙም ጥርስን ነክሶ ማለፍ የግድ መሆኑን አስረግጣ በመናገር ከሁሉ አስቀድሞ ግን ወጣቱ ራዕዩን ሊያስቀምጥ ይገባል ትላለች። ራዕይ ያለው ሰው ራዕዩን ተከትሎ በሚወደው ሙያ በመሰማራት ውጤታማ መሆን ይቻለዋል። በማለት ለወጣቱ ባስተላለፈችው መልዕክት አበቃን።


ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

# የዲላ ከተማ ሕዝብና ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቱ

ፍሬሕይወት አወቀ

**በዲላ ከተማ የሚስተዋለውን የንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ በ2013 ዓ.ም ታኅሳስ ወር ላይ የተጀመረው ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት 18 ወራት የሚፈጅ የኮንትራት ጊዜ ተወስኖለታል። ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ቢሆንም ወደ መጠናቀቅ ሳይደርስ ከሁለት ወራት ያነሰ ጊዜ ብቻ ቀርቶታል**



የዲላ ከተማ ዋና ከንቲባ አቶ ተስፋጺዮን ዳካ

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ የክልል ከተሞችና የገጠር ቀበሌዎች ጭምር የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች በስፋት ይነሳል። በሁሉም አካባቢዎች ዋነኛ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች ከሆኑትና በመንግሥት አቅም ከሚሰሩት የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መካከል የመንገድ፣ የመኖሪያ ቤት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል መስመር ዝርጋታና የንጹህ የመጠጥ ውሃ በዋናነት ይጠቀሳል።

ሕይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መሰረት ልማቶች መካከል ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው ንጹህ የመጠጥ ውሃ አንዱ ነው። ‹‹ውሃ ሕይወት ነው›› የተባለውም ያለ ምክንያት አይደለም። የሰው ልጆችን ጨምሮ እንስሳትና እጽዋቱ ሁሉ ከውሃ ውጭ ሕይወት የላቸውምና ነው። ይሁንና በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ እጥረት ሲገጥማቸው መመልከት የተለመደ ቢሆንም በአንጻሩ ደግሞ መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት ሲያደርግም ይስተዋላል። በዛሬው ዕትማችንም ልናስነብባችሁ የወደድነው በንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ችግር ላይ ባለው የዲላ ከተማ ሕዝብ የውሃ ጥሙን ማርካት እንዲችል ታስቦ እየተሰራ ባለው ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ዙሪያ ነው።

የዝግጅት ክፍላችን በዲላ ከተማ በተገኘበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩን ከንቲባ አግኝቶ ፕሮጀክቱ መች እንደተጀመረ፣ ምን ያህል ወጪ እንደሚጠይቅና መች እንደሚጠናቀቅ ጭምር አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃዎችን እንደሚከተለው አጠናቅሯል።

በአገሪቱ ከሚገኙ የክልል ከተሞች መካከል በልምላሜዋና ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴዋ የምትታወቀውና በደቡብ ክልል ጌዲዮ ዞን የምትገኘው ዲላ ከተማ ከፍተኛ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ችግር የሚታይባት ለመሆኗ በየሰው ደጃፍ የተኮለኮሉት ቢጫ ጀሪኪናች ምስክሮች ናቸው። በከተማዋ የሚታየውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ እጥረት ለመፍታት ከተማ አስተዳደሩ ምን እየሰራ ነው ስንል ላነሳነው ጥያቄ የዲላ ከተማ ዋና ከንቲባ አቶ ተስፋጺዮን ዳካ የሚከተለውን ብለዋል።

እንደሳቸው ገለጻ፤ በአሁን ወቅት ከተማዋ ከሚያስፈልጋት ንጹህ የመጠጥ ውሃ መጠን በታች እያገኘች እንደሆነ በመጥቀስ ዜጎች በንጹህ የመጠጥ ውሃ ችግር ውስጥ ከፍተኛ ችግር እያሳለፉ ነው ያለ ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ነው።

በዲላ ከተማ ከፍተኛ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እጥረት አለ። አጠቃላይ የከተማው ሕዝብ ለአንድ ቀን ብቻ 25 ሺ ሜትር ኪዩብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚያስፈልገው ቢሆንም በአሁን ወቅት የከተማ አስተዳደሩ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት በከተማ ደረጃ 2993 ሜትር ኪዩብ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ብቻ እያቀረበ ይገኛል። ይህም ከፍላጎቱ ጋር ሲነጻጸር እጅግ ሰፊ ልዩነት እንዳለውና ዘርፉ ክፍተት ያለበት ለመሆኑ ማሳያ ነው።

ይሁንና ችግሩን መቅረፍ የሚያስችል ግዙፍ የሆነ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት በከተማዋ ተጀምሯል። ፕሮጀክቱ ከ298 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ሲሆን ፕሮጀክቱ ዕውን እንዲሆን ማህበረሰቡን ጨምሮ ከተማ አስተዳደሩ በከፍተኛ ትኩረት እየተከታተለው እንደሆነ አቶ ተስፋጺዮን ተናግረዋል። በተለይም ማህበረሰቡ ፕሮጀክቱ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ በጣም በቅርበት እየተከታተለና እየጠየቀ መሆኑን በማንሳት በአሁን ወቅትም አጠቃላይ የፕሮጀክቱ የሥራ እንቅስቃሴ 33 በመቶ ደርሷል። ከዚህ በኋላም ቀሪ ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉና ወደ ፍጻሜው ለመድረስ የሚሠራ ይሆናል።

ለመስመር ዝርጋታው በርካታ የፕላስቲክ ቱቦዎች ወደ ከተማው የገቡ እንደመሆናቸው በቀጣይ የመስመር ዝርጋታው ይከናወናል ያሉት አቶ ተስፋጺዮን፤ ወደ መስመር ዝርጋታው ሲገባ ትልቅ ችግር የሚገጥማቸው ይሆናል። በተለይም ከግለሰቦች ይዞታ ጋር በተያያዘ አጥሮችን፣ ግቢዎችንና ሰብሎችን የመንካት ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም በሥራው የሚጠበቅ ችግር ነው።

በመጀመሪያው ዲዛይን 24 የሚደርሱ ዓለም አቀፍ የአስፓልት መንገዶችን ይቆርጥ እንደነበር አስታውሰው ይህም በአንድ በኩል የውሃ ልማት ሲረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የመንገድ መሰረተ ልማትን ማፍረስ ተገቢ እንዳልሆነ በማመን ዲዛይኑን መቀየር ተችሏል። በአዲስ መልኩ በተጠናው ዲዛይንም የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ከ24 የአስፓልት ቆረጣ ወደ 12 ዝቅ ማድረግ ተችሏል። ይህም ወጪን ከመቆጠብ ጀምሮ በመንገድ መሰረተ ልማት ላይ ይደረስ የነበረውን ጉዳትም መቀነስ አስችሏል።

የሕዝብ የሆነው ይህ ፕሮጀክት ውጤታማ መሆን እንዲችልና በተቀመጠለት የጊዜ ገደብና በጀት ተጠናቅቆ አገልግሎት እንዲሰጥ የሁሉም አካላት ርብርብ ያስፈልጋል። ከተማ አስተዳደሩም በተቻለው አቅም ሁሉ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል እያደረገ ይገኛል። ዞኑ፣ ከተማ አስተዳደሩና የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅትም እንዲሁ ተገቢውን በጀት እየከፈሉ መሆኑን አቶ ተስፋጺዮን ይጠቅሳሉ። ክልሉም አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ነው። በተለይም ከተማ አስተዳደሩ አምስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በመክፈል ሶስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር የሚቀርበት መሆኑን አስረድተዋል።

የዲላ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት አምስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ብር መክፈል የነበረበት ቢሆንም ከሚያቀርበው ውሃ አንጻር የሚያገኘው ገቢ አነስተኛ እንደሆነ ተናግረው ፕሮጀክቱ ተግባራዊ መሆን ሲችል ተጠቃሚው አጠቃላይ የከተማው ሕዝብ እንደመሆኑ ተቋሙን በመደገፍ ፕሮጀክቱ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ርብርብ ማድረግ ከሁሉም የሚጠበቅ በመሆኑን ይናገራሉ።

ሕዝቡ ከንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቱ ተጠቃሚ መሆን እንዲችል በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ሲሆን የተወሰኑ ግብዓቶች ማለትም ፓምፕ፣ ጀነሬተሮችና ሌሎች ግብአቶች ጅቡቲ ወደብ ላይ መድረስ እንደቻሉ የጠቆሙት አቶ ተስፋጺዮን፤ ከጅቡቲ ወደ ዲላ ከተማ እስኪዘዋወር የሚወስደው ጊዜ እንዳለ ሆኖ በቀሪዎቹ ወቅቶች በተጠናከረ መንገድ ሙሉ አቅማቸውን አሟጠው መሥራት ከቻሉ በቀጣይ ስድስት ወራት ፕሮጀክቱን በማጠናቀቅ መሰረታዊ የሆነውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ጥያቄ ለመመለስ ጥረት የሚደረግ መሆኑን ነው ያስታወቁት ።

ለተግባራዊነቱም ከተማ አስተዳደሩ ህብረተሰቡን በማንቀሳቀስ የሚጠበቅበትን ሥራ መሥራት ይኖርበታል ያሉት አቶ ተስፋጺዮን፤ በተለይም ከወሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ የውሃ መስመር በሚያልፍባቸው አካባቢዎች ከይገባኛል ነጻ የማድረግ ሥራ አንዱ ነው። ይህ ሥራ በሚሠራበት ወቅትም ህብረተሰቡ ሊደግፍ እንደሚገባ አመላክተዋል። ህብረተሰቡ የረጅም ጊዜ ጥያቄው የነበረውንና ሕይወት የሆነውን ውሃ ለማግኘት የሚጠበቅበትን ግዴታ ለመወጣት በተለይም አጥርና ሰብሎችን ማንሳት የውሃ መስመሩ እንዲያልፍ የማድረግ ሥራ በመሥራት ከከተማ አስተዳደሩ ጎን ቢሆኑ መልካም ነው በማለት ጥሪ አድርገዋል ።

ከፕሮጀክት ጥራት አንጻር ከፍተኛ ክትትል በማድረግ ጥራቱን የጠበቀ ሥራ እንዲሠራም ከፍተኛ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ያነሱት አቶ ተስፋጺዮን፤ የፕሮጀክቱ አማካሪ መሃንዲሶች ጋር ክፍተት የነበረ መሆኑን አስታውሰው፤ በአሁን ወቅት ክፍተቱን ለመድፈን መሃንዲስ መቀየር እንደተቻለና አዲስ የተቀየረው መሃንዲስም ጥሩ ክትትል እያደረገ ያለበት ሁኔታ መኖሩን አመላክተዋል። ከዚህ በተጨማሪም በዘርፉ ዕውቀት ያላቸውን አመራሮች ጭምር በማማከር አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ችግሮችን በፍጥነት እየታረሙ ነው።

ከከተማ አስተዳደሩ በተጨማሪ ክትትሉ በዋናነት በፕሮጀክቱ መሃንዲስ፣ በከተማው የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣ በዞኑ ውሃ መምሪያ ኃላፊ እንዲሁም በአማካሪ መሃንዲሶች ጭምር ከፍተኛ የሆነ ክትትል እየተደረገ ያለበት ሁኔታ መኖሩን አስረድተው፤ የህብረተሰቡ ሚና ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ ያነሱት አቶ ተስፋጺዮን፤ ህብረተሰቡ ፕሮጀክቱ የራሱ መሆኑን አምኖ በተለይም መስመሩ በሚያልፍባቸው አካባቢዎች ሁሉ የተቀመጡ የውሃ ማስተላለፊያ ቱቦዎችን መጠበቅ እና ንብረቱ የራሴ ነው በማለት ልዩ ጥበቃ ሊያደርግላቸው እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተው አሳስበዋል።

ፕሮጀክቱ ተጠናቅቆ ከሚሰጠው አገልግሎት ባሻገር በግንባታው ሂደት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ መሆኑ ያነሱት አቶ ተስፋጺዮን፤ ከጉልበት ሥራ ጀምሮ ለተለያዩ አካላት ግብዓት ከማቅረብ አንስቶ በርካታ አገልግሎት ላላቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችሏል። በግንባታው ዘርፍም ተሳታፊ የሆኑትም የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ሲሆን ፕሮጀክቱ ያልተጠናቀቀ እንደመሆኑ በቀጣይ በመስመር ዝርጋታም እንዲሁ ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚችል በመሆኑ በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች ሥራን ሳያማርጡ የተገኘውን የሥራ ዕድል ተጠቅሞ ገቢ ማግኘት እንዲችል በማለት ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

በዲላ ከተማ የሚስተዋለውን የንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍ በ2013 ዓ.ም ታኅሳስ ወር ላይ የተጀመረው ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት 18 ወራት የሚፈጅ የኮንትራት ጊዜ ተወስኖለታል። ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን በርካታ ሥራዎች የተሰሩ ቢሆንም ወደ መጠናቀቅ ሳይደርስ ከሁለት ወራት ያነሰ ጊዜ ብቻ ቀርቶታል።

ፕሮጀክቱ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መጓዝ እንዳይችል የተለያዩ መሰናክሎች ማጋጠማቸውን አንስተዋል። በተለይም አገር አቀፍ በሆነው የሲሚንቶ ግብዓት እጥረት የግንባታ ሂደቱ ተቋርጦ ቆይቷል። በዚህ ምክንያትም ከስድስት እስከ ሰባት ወራት በግንባታው ሂደቱ ላይ መስተጓጎል ተፈጥሯል። ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ በሚገቡ ግብዓቶች አማካኝነት በጨረታ ሂደት ወደ ኋላ የቀረ ሲሆን በአሁን ወቅት ግን የጨረታ ሂደቱን በማለፍ አስፈላጊው ግብዓት ወደ አገር ውስጥ ብሎም ወደ ከተማው እየገባ ይገኛል።

የዲላ ከተማ ሕዝብ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ የዘመናት ጥያቄው የሆነውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ ማግኘት እንዲችል በከፍተኛ ትጋት እየተሠራ ስለመሆኑ የዝግጅት ክፍላችን በቦታው ተገኝቶ በጎበኘበት ወቅት መረዳት ችሏል። ንጹህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቱ በሁለት ክፍሎች ተከፋፍሎ እየተሠራ ያለ ሲሆን የመጀመሪያው የሥራ ክፍል ጥልቅ ጉድጓዶችን መቆፈር እንደመሆኑ በአራት የተለያዩ ሳይቶች ላይ አራት ጥልቅ ጉድጓዶች ተቆፍረዋል። በሁለተኛው የሥራ ክፍልም እንዲሁ 219 ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ የሲቪል እና የኤሌክትሮ መካኒካል ግንባታ ሥራው እየተከናወነ ይገኛል። በአጠቃላይ ከማማከርና ከሌሎችም ሥራዎች ጋር ተያይዞ ፕሮጀክቱ ከ298 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት የሚጠይቅ ነው።

ወጪው የሚሸፈነውም ከዓለም ባንክ በተገኘ ብድር፣ በክልሉ፣ በከተማ አስተዳደሩ፣ በዞኑና በዲላ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ዘርፍ የሚሸፈን ስለመሆኑም መረዳት ተችሏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓሉን በመተሳሰብና በአብሮነት እናሳልፍ

በበዛው ብዝሃነቷ የምትታወቀው ኢትዮጵያ፤ የሕዝቦቿ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊና ሌላም መገለጫ የሆኑ አያሌ ሁነቶች፣ አያሌ እሴቶች በዘመን ሳይበረዙ፤ በጊዜ ሳይደበዝዙ ሕያው ሆነው የሚገኙባትም ናት። እነዚህ ባህላዊ፣ ታሪካዊም ሆኑ ሃይማኖታዊ እሴቶቿ ደግሞ፤ በሕዝቦች ተጠብቀው፣ የማንነት መገለጫና ማሳወቂያ ሆነው የኖሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ናቸው። ከዚህም ባለፈ እንደ አገር ከፍ ያለ ገጽታን ለመገንባት፣ የቱሪዝም መስህብነትን በማሳደግ ከፍ ያለ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፤ ሕዝቦችን ከማቀራረብ፣ አብሮነትን ከማጠናከር፣ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴትን ከፍ ከማድረግ አኳያ ያላቸው ሚና ተኪ የሌለው ነው።

በዚህ ረገድ ሃይማኖታዊ በዓላት ቀዳሚውን ድርሻ ይይዛሉ። ኢትዮጵያ ደግሞ የክርስትናው፣ የእስልምናውና የዋቄ ፈታ ሃይማኖት ተከታዮች ከበዛ ሃይማኖታዊ እሴቶቻቸው ጋር ከፍ ብለው የሚገለጹባት እንደመሆኗ፤ ኢትዮጵያውያን ከእምነታቸውም፣ ከባህሎቻቸውም ያገኙትን የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት፣ አብሮ የመብላትና የመጠጣት፤ አንዱ ለአንዱ የመድረስና በደስታ አብሮ በዓላትን የማሳለፍ አስተምህሮ በአደባባይም፣ በጉርብትናም የሚገልጹባቸው ናቸው። በሁሉም ሃይማኖታዊ በዓላት ላይም ዘር፣ ቀለም፣ ፆታ፣ እድሜ፣ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ ሌላው ቀርቶ እምነት ሳይገድባቸው አብሮ ማሳለፍ፣ አንዱ ለአንዱ መድረስ፣ ያለው ለሌላው በማካፈል ለሌሎች ደስታ መፍጠር የኖረ ማንነታችን ነው።

ይህ ማንነታችን ደግሞ እንደ እስከዛሬው ሁሉ በቀጣይም ሊገለጥ፤ ባለን ነገር ከምንፈጥረው ደስታ ባሻገር ለሌሎች በማድረግ እና ከሌሎች ጋር በማሳለፍ በሰዎች በምንፈጥረው ደስታ ውስጥ እኛም ከፍ ያለ ደስታን ለማግኘት በሚያስችለን ልክ ልናስቀጥለው ይገባል። በዚህ ረገድ ከፊታችን የሚጠብቁን የትንሳኤም ሆነ የኢድ አልፈጥር በዓላት ይሄንኑ የሚጠይቁ ናቸው። ለአብነት፣ ከኢድ አልፈጥር ቀደም ብለን የምናከብረው የትንሳኤ በዓል ከራስ ይልቅ ለሰዎች ማድረግን የሚያስተምር፤ በሰዎች ደስታና መሻገር ውስጥ የራስን ደስታ መፍጠርን፤ ካለን ብቻ ሳይሆን ከሌለን ላይ ማካፈልን፤ ለብቻ ሳይሆን በሕብረት አብሮ ማሳለፍን፣ ወዘተ. አጥብቆ የሚሻ ነው።

የትንሳኤን በዓል ስናከብር ቀዳሚው ጉዳይ እየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ሃጥያት ሲል ራሱን ቤዛ አድርጎ በመስቀል ላይ የዋለበትን፤ በከርሰ መቃብር ውሎ ያደረበትን፤ እንደ ፈጣሪነቱም የመቃብሩን ጉድጓድ ፈንቅሎ የወጣበትንና ለሰው ልጆች የዘለዓለም ሕይወትን የሰጠበትን የምናስብበት ነው። ይህ በጌታ እየሱስ ለእኛ ለሰው ልጆች የተከፈለ የበጎነት ሁሉ ቁንጮ፣ የፍቅር ሁሉ ታላቅ ፍቅር፣ የመስጠት ተምሳሌት ራስን አሳልፎ የመስጠትን ሃያልነት የምንማርበት ነው።



ይህ እውነት ዛሬ ላለንበት ክፉ ጊዜ፤ ወገኖቻችን በችግር፣ በስደት፣ በድርቅ፣ በርሃብና ሌላም ችግር ውስጥ ሆነው፤ በበዛ መከራና ጭንቀት ውለው በሚያድሩበት ዛሬ ላይ በእጅጉ የሚያስፈልገን ነው። ትናንት በሞቀ ቤታቸው በዓልን ሲያሳልፉ የነበሩ ሚሊዮኖች ዛሬ ከሞቀ ቀያቸው በግፈኞች ተፈናቅለው በየመጠለያ ጣቢያውና በየጉራንጉሩ ወድቀው የእኛን እጅ የሚመለከቱበት፤ በዓልን በወግ ማክበር ቀርቶ የጨቅላ ልጆቻቸውን የሰቆቃ ድምጽ ማስታገስ ሳይችሉ በብርቱ ሃዘን ውስጥ ያሉበት፤ መኖር እንደ አለት ከብዶ የሚሰማቸው፣ በአንጻሩ ሞት እንደ ሰማይ የራቃቸው በምድር ሲዖል የሚማቅቁ ወገኖች የበዙበት ወቅት ነው።

ወገኖቻችን፣ ወንድም እህቶቻችን፣ ሕጻናት ልጆቻችን፣ ወዘተ. በዚህ መልኩ በምድር መከራ ውስጥ ሆነው፤ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ እያሉ፤ በአንጻሩ እኛ በሞቀ ቤት፣ በተትረፈረፈ ማዕድ፣ በተቀናጣ ሕይወት ውስጥ ብንገኝ፣ በዓሉንም በተቃርኖ ዓለም ውስጥ ሆነን ብናከብር ምን ሊረባን?።

ይልቁንም ጌታ እየሱስ ስለ እኛ የከፈለውን ዋጋ አስበን ስለእነዚህ ወገኖቻችን ልንጨነቅ፤ ስለ እኛ የተደረገልንን እያስታወስን ስለምንዱባን ወገኖቻችን ተጨንቀን ልናደርግ፤ በሞቱ ጥላ ስር በሰላምና በፍቅር እንድንሰባሰብ ሕይወት ተከፍሎ የተሰጠንን ሕይወት ሳንዘነጋ፤ በዓልን ከእነዚህ ወገኖቻችን ጋር በቤትም በደጅም በጋራ ተሰባስበን ልናሳልፍ የተገባ ነው። የትንሳኤው ትርጉም፣ የዓውዳመቱ ድምቀትና ደስታ፣ የኢትዮጵያዊነት ወግና ባህሉም ይሄው ነው። እናም ታላቁን ትንሳዔን በዓልን በመተሳሰብና በአብሮነት እናሳልፍ!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# በወቅታዊ ሀገራዊ የደህንነትና ፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በመምክር ከብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ

በወቅታዊ ሀገራዊ የደህንነትና ፀጥታ ጉዳዮች ዙሪያ በመምከር የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት የሰጠው መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ የደረሰችው በየዘመናቱ የገጠሟትን ፈተናዎች በድል እየተሻገረች ነው። እንድትጠፋ የሚፈልጉ ኃይሎች ሊያጠፏት ሲነሡ ምንጊዜም ሦስት ኃይሎችን እንደሚጠቀሙ እሙን ነው።

የመጀመሪያዎቹ ምንጊዜም የማይተኙት ታሪካዊ ጠላቶቻችን ናቸው። እነዚህ ጠላቶቻችን ጠላትነታቸውን የሚያቆሙት ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ከምድር ገጽ ስትጠፋ ብቻ ነው። ይኼ ምኞታቸው እንዲሳካ ብቻቸውን አይሠሩም። ተላላኪ አላቸው። እነዚህም ሁለተኛዎቹ ናቸው። ለገንዘብና ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ወገናቸውን እንደ ይሁዳ የሚሸጡ፣ ሀገር የጣለባቸውን እምነት በሸርፍራፊ ሳንቲም የሚለውጡ ሀገር አልባ ባይተዋሮች ሞልተዋል። የተናገሩትን ሆነው የማይገኙ፣ ቀን ቀን በአደባባይ ስለ ሕዝብ ፍቅር እና ስለ ሀገር አንድነት የሚደሰኩሩ፤ ማታ ማታ ከጠላት ጋር እያሴሩ ወገንን የሚከዱና ሀገር ለማፍረስ ጉድጓድ የሚቆፍሩ ናቸው።

ሦስተኛዎቹ የኢትዮጵያ ጠላቶች ደግሞ ባለማወቅ የእነዚህ የሁለቱ አካላት ተባባሪ የሚሆኑት ናቸው። ግዴለሽ ስለሆኑ፣የሚያደርጉት ነገር የሚያስከትለውን ውጤት ሳይገምቱ እንዲሁ በነሲብ የጠላትን ተልዕኮ የሚፈጽሙ ውል አልባ ኢትዮጵያውያን ናቸው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን አንድን ነገር ተቀብለው ማውራታቸውን፤ ወይም አድርጉ የተባሉትን ነገር ማድረጋቸውን፤ ወይም ሳይመረምሩ የሰጧቸውን መረጃ ሁሉ ማስተላለፋቸውን እንጂ በሀገራቸውና በሕዝባቸው ላይ የሚያስከትለውን ጣጣ አይመረምሩትም። ከመረመሩም ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ ብቻ የሚፀፀቱ ናቸው።

ኢትዮጵያ ይበልጥ እየተፈተነች ያለችው በእነዚህ በሁለቱ ነው። ታሪካዊ ጠላቶቻችን በአንድ ስሙ ቁርጣቸው የታወቀ ጠላቶቻችን ናቸው። ባይተዋሮችና ውል አልባ ኢትዮጵያውያን ግን በወቅቱ ልብ ሳንላቸው ደጋግመው ዋጋ ያስከፍሉናል። በዚህ መልኩ እስከመቼ? ለዚህ ጥያቄ ሁላችንም ቆም ብለን ምላሽ ልንሰጥ ይገባል።

ለውጡ ከመጣ ጀምሮ እንኳን እንደ ሀገር በብዙ ተፈትነናል፤ የሰነቅነውን ተስፋ እንዳናይ የሚከልሉ ስንት ጋሬጣዎች ገጠሙን? ስንቱን ተሻገርን? በስንቱ ወደቅን? አንድ በአንድ ብንዘረዝረው ቁጥሩ ቀላል አይደለም። እነዚህ ፈተናዎች የመጡት ከላይ ከተጠቀሱት የኢትዮጵያ ጠላቶች ነው። ለውጡ እንዳይሳካና ኢትዮጵያ ጠንካራ የአፍሪካ ኃይል ሆና እንዳትወጣ ለማድረግ አቅማቸው የፈቀደውን አድርገዋል። ኢትዮጵያውያን በዘር ተከፋፍለው እርስ በርስ እንዲጋጩ፣ ሀገር በኢኮኖሚ እንድትዳከም፣ ሀገር ተሸክመው የኖሩ ተቋሞቻችን እንዲፈራርሱ በብርቱ ሲሠሩ ነበር።

ሚዲያና የጦር መሳሪያ የታጠቁ ሰዎችን በመጠቀም ማህበራዊ እሴቶቻችንን ለመበጣጠስ፣ የእምነትና ማኀበራዊ ተቋማትን ለማቃጠል፣ በሕዝብ መካከል ሽብር ለመንዛትና ዜጎቻችንን ዕረፍት ለመንሣት ክፋት የተባሉትን ተግባራት ሁሉ ፈጽመዋል። የፈጸሙት እኩይ ሥራ እጅግ አሰቃቂና ዜጎቻችንን የጎዳ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያውያን ኅብረ ብሔራዊ አንድነትና ለሀገራቸው ባላቸው የጸና ፍቅር ምክንያት ጠላቶቻችን የሚፈልጉትን ግብ ሊያሳኩ አልቻሉም።

ከለውጡ በፊት ተቋማዊ ስብራት ከገጠማቸው መካከል የሕግና ጸጥታ ተቋማት ይገኙበታል። እነዚህ ተቋማት እንዲሰበሩ የተደረጉት ሆን ተብሎ የታሪካዊ ጠላቶቻችንን ዓላማ ለማሳካት እንዲቻል ነው። በሀገር ውስጥ ሥልጣንና ሀብት ይዘው የነበሩት የታሪካዊ ጠላቶቻችን ተላላኪዎች፣ የሕግና የጸጥታ ተቋማትን በሞትና በሕይወት መካከል እንዲኖሩ አድርገዋቸው ነበር። ከለውጡ በኋላ በእነዚህ ተቋማት ላይ በተሠራው ሥራ የኢትዮጵያን ህልውና ለመታደግ ወደሚችሉበት ደረጃ ለማድረስ ተችሏል። እስከዛሬ ድረስ እነዚህን ተቋማት ለማጠናከርና ለዛሬ ችግሮች ምላሽ፣ ለነገ ፈተናዎች ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ ሲባል፣ እያመመንም ቢሆን አያሌ ችግሮችን ተሸክመን ለማለፍ ተገደናል።

ዳሩ ግን ትዕግሥትም ልክና መጠን አለው። አሁን የጸጥታና ደኅንነት ተቋማት በተሻለ ቁመና ላይ ስለሚገኙ አስፈላጊ በሆነ ሰዓት ሁሉ ተመጣጣኝ ምላሽ ከመስጠት ወደኋላ አንልም። ከደህንነትና ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ችግሮቻችን በዘላቂነት እንዲቀረፉ የብዙ አካላት ርብርብና ተናብቦ መሥራትን እንደሚጠይቅ ምንም ጥርጥር የለውም። እኛኑ ለሚያሸብሩና እኛኑ ለሚያሰቃዩ ጠላቶች ሕዝብ ምሽግ ከሆነ የጸጥታ አካላት ጥረት ብቻውን መፍትሔ አያመጣም። ስለዚህ እያንዳንዱ ዜጋ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ሚዲያና ሌሎች የሕዝብ ዐይን፣ ጆሮና ክንድ ሆናችሁ የምትሰሩ አካላት ከጸጥታ ተቋማት ጋር በቅንጅትና በመግባባት ለመሥራት በሙሉ ልብ ቁርጠኞች መሆን አለባችሁ።

በለውጥ ጎዳና ላይ በመጓዝ ዴሞክራሲን የሚገነቡ ሀገራት በሁለት ጫፍ መካከል የሚቆም ፈተና ይገጥማቸዋል። በአንድ በኩል ዴሞክራሲያዊ ባህልን መገንባት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሀገርንና የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት በጥብቅ ርምጃዎች ማስከበር ነው። ዴሞክራሲያዊ ባህልን ለመገንባት ስንነሣ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት የሚያስከብሩ ጥብቅ ርምጃዎቻችን በነጻነትና መብት ስም እንዳይላሉ፤ የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት ለማስከበር የምንወስዳቸው ጥብቅ ርምጃዎችም ዴሞክራሲያዊ ባህልን እንዳያቀጭጩ በሚዛን መንቀሳቀስ ይገባናል። ሁለቱን በሚዛን ለማከናወን ደግሞ የእያንዳንዱ ዜጋ፣ ተቋም፣ ፓርቲ፣ ቡድን፣ ወገን፣ የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት። የሕግና የጸጥታ ተቋማትም ሕገ መንግሥታዊና ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን መወጣት አለባቸው።

በመሆኑም ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ ቡድኖችንና ግለሰቦችን፣ ሐሰተኛ መረጃዎችን በማሠራጨት ሕዝብና ሀገርን ሰላም የሚነሡ አካላትን፣ በሕገ ወጥ መንገድ ታጥቀው የሕዝብን ሰላም የሚነሡና ለታሪካዊ ጠላቶቻችን በተላላኪነት የሚያገለግሉ ቡድኖችን፣ በመሬት ወረራና በተለያዩ የሥርቆትና የማታለል ተግባራት የተሠማሩትን፣ የትራንስፖርትና ሕዝብ እንቅስቃሴዎችን የሚያውኩትን፣ የልማትና የኢንቨስትመንት ተግባራትን የሚያደናቅፉትን፣ በጥናትና በመረጃ በመለየት አስፈላጊው ሁሉ ሕግ የማስከበር ርምጃ እንዲወሰድ የደኅንነት ምክር ቤቱ ወስኗል። በተመሳሳይ የምግብና ልዩ ልዩ ሸቀጦች ዋጋ እንዲንር በሕገ ወጥመንገድ ምርት የሚያከማቹ፣ በኮንትሮባንድ መልክ ነዳጅና ሌሎች ምርቶችን ወደ ጎረቤት ሀገራት የሚያሾልኩ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች ላይ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል።

ወላጆች ልጆቻችሁን፣ ሽማግሌዎች ወጣቶቻችሁን፣ የሃይማኖት አባቶች ምእመኖቻችሁን፣ የፓርቲ መሪዎች አባሎቻችሁን፣ የጎሳ መሪዎች ወገኖቻችሁን በመምከር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከግጭትና ከሽብር ራሱን አርቆ፣ ለሰላምና ለሀገር ደኅንነት የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ እንድታደርጉ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪያችንን እያቀረብን፣ ከዚህ በተቃራኒው ተሰልፎ የሚገኝ ማንኛውም ሰው፣ አካልና ቡድን ላይ ሕጉ የሚፈቅደውን ተገቢውን ሕግና ጸጥታ የማስከበር ሥራ የምንሠራ መሆኑን እናሳውቃለን።

መጪው ቀናት ለሕዝበ ክርስቲያኑም ሆነ ለሕዝበ ሙስሊሙ የበዓላት ሰሞን እንደመሆኑ መጠን አማኞች በትብብርና በመግባባት የጠላቶቻችንን ፍላጎት በማክሸፍና የጋራ ደህንነታችንን በማረጋገጥ እንደ ሀገር የተሳካ ጊዜያት እንድናሳልፍ የደህንነት ምክር ቤቱ አበክሮ ይጠይቃል።

**የብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት**
**ሚያዚያ 14/ 2014 ዓ.ም**

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ለተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፣ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ለራስ ምንም ለአገር ደጀን

አስናቀ ፀጋዬ

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በከፈተው ወረራ ገፈት ቀማሽ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ነው። በዚህ ወረራ ቤት ንብረቱን አጥቷል። የንግድ ቤቱን ተዘርፏል። ግፍና መከራም ተፈራርቆበታል። የዛሬውን አያድረገውና ከዛሬ ሀያ ሶስት አመታት በፊት በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት እርሱም የመከላከያ ሰራዊት አባል ነበርና ውትድርናን ጠንቅቆ ያውቃል።

በውስጡ ያለው የአገር ፍቅር ስሜትና አልሸነፍ ባይነት ታዲያ ወራሪው ሃይል ወደ አፋር ጭፍራ ዘልቆ በገባበት ወቅትም ተንፀባርቋል። ምንም እንኳን ነፍጥ ይዞ ወራሪውን ሃይል ፊት ለፊት ገጥሞ ባይፋለምም ለኢትጵያ መከላከያ ሰራዊት ስንቅ በማቀበል፣ ቁስለኞችን በመንከባከብና ህይወታቸው ያለፈውን በክብር በመቅበር እውነተኛ የኢትዮጵያ ባለውለታ መሆኑን አስመስክሯል።

ወራሪው ሃይል ጭፍራን እስኪቆጣጠር ድረስ የሚችለውን ሁሉ አድርጎ በኋላ ላይ የባለቤቱንና ሶስት ልጆቹን ነፍስ ለማዳን ሲል ወደ አማራ ክልል፣ ጃንጀሮ ተብሎ ወደ'ሚጠራ አካባቢ ከሄደም በኋላ ቤተሰቡን ደብቆ ከሕወሓት ሃይል ጋር በሚችለው አቅም ሁሉ ለመፋለም ጥረት አድርጓል። ወራሪው ቡድን በመከላከያ ሰራዊት በደረሰበት ጠንካራ ምት ሙሉ በሙሉ ከአማራና ከአፋር ክልል ተጠራርጎ እስኪወጣም ድረስ እዛው ነበር።

ለፍቶ ያገኘባት፣ ተድሮ ልጅ የወለደባት፣ ነግዶ ያተረፈባት፣ ክፉ ደጉን ወዳ'የባት ጭፍራ ሲመለስ ግን ቤቱ ፈርሶ፣ ንብረቱ ተዘርፎ ጠበቀው። ተስፋ ቆርጦ ሙሉ ቤተሰቡን ይዞ ወደ ተወለደባት አዲስ አበባ በመምጣት በወንድሙ ቤት በጥገኝነት ተጠለለ።

አሁን ጥገኝነቱ አንገሽግሾታል። ባለቤቱም ልጆቹም ተመልሰን ወደ አገራችን እንሂድ እያሉ ሲወተውቱት አይኑ እምባ ያቀራል። እርሱም ቢሆን ብዙ አመት ወደ ኖረበትና ክፋውንም ደጉንም ወዳ'ሳለፈበት አፋር ጭፍራ መሄድ ይፈልጋል። ልጆቹም ያቋረጡትንና የሚወዱትን ትምህርት ለመጀመር ጓጉተዋል።

ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ የደረሰበት ቢሆንም ህይወትን እንደ አዲስ ማጣጣም ይፈልጋል። ቤተሰቦቹም እንደዛው። ወደ አፋር ጭፍራ ዳግም ሄዶ ለመኖር ግን እርሱና መሰል ከሌላ አካባቢዎች የመጡና ኑሯቸውን በአፋር ጭፍራ ያደረጉ ሰዎች የመኖር ደህንነት ዋስትና ይፈልጋሉ።

የዛሬ የ"እንዲህም ይኖራል" እንግዳችን አቶ አቡበከር መርዕድ ይባላል። እድገትና ውልደቱ እዚሁ አዲስ አበባ፣ ሰሜን ማዘጋጃ አካባቢ ነው። ትምህርቱን እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ በወይዘሮ ቀለመወርቅ ደበበ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታትሏል። በ1990 ዓ.ም የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ሲጀመር የሰራዊቱ አባል ሆኖ ዘመተ። ባድመ ላይ በተደረገው ጦርነትም ተመቶ ለህክምና መጀመሪያ ጎንደር በመቀጠል ደግሞ ወደ አዲስ አበባ ጦር ሃይሎች ሆስፒታል ተላከ።

ህክምናውን ካጠናቀቀ በኋላ ፍቃድ ቢጠይቅም በድጋሚ ወደ ሽሬ ግንባር እንዲሄድ ታዘዘ። ይሁንና የተሰጠው የአስራ አምስት ቀን ፍቃድ ከደረሰበት ጉዳት ሙሉ በሙሉ ለማገገም ስላልበቃው በአዲስ አበባ ለመቆየት ወሰነ። በኋላ ግን ከጦርነቱ የተረፉና የሞቱትን ለመለየት በየቀበሌው ፖሊሶች ፍለጋ ሲያካሂዱ እርሱም ተገኝቶ ከሌሎች ጋር ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተወሰደ። ከዚያም ወደ ታጠቅ የወታደር ማሰልጠኛ አመራ።

ማጣሪያ ካደረጉ በኋላ እርሱን ጨምሮ ሰላሳ ወታደሮችን በዛው እለት ምሽት ላይ ለቀቋቸው። እንደገና በማግስቱ ከሰላሳዎቹ ውስጥ ከእርሱ ጋር አስራ አምስቱን ስንፈልጋችሁ ትመጣላችሁ በሚል መርጠው



ፎቶ፡- በአስናቀ ፀጋዬ

አቶ አቡበክር መርድ፤

አሰናበቷቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ቤቱ ገብቶ ቀረ። ስራም በቀላሉ ሊያገኝ አልቻለም።

መቼም ሁሌም ቤት መቀመጥ ለአእምሮም ለአካልም ጤና አይሰጥምና አቶ አቡበከር ኑሮን ለማሸነፍ ሲል እዚህ አዲስ አበባ አብሮት በተማረ አንድ ጓደኛው ገፋፊነት ወደ ወልድያ አቀና። ወልድያ ሄዶ ግን በቀላሉ ስራ ማግኘት አልቻለም። ወልድያ እያለ ግን የሰፈሩን ልጅ አገኘ። ስራ እንዳላገኘና ወደ አዲስ አበባ የሚመለስበትን መንገድ እንዲያመቻችለት ጠየቀው። የሰፈሩ ልጅም ችግር የለውም አለው።

በጊዜው ይህ የሰፈር ልጅ ተብዬው የመስኖ ፕሮጀክት ኃላፊ ነበርና ስራ ሊያሰራው ወደ አፋር ወሰደው። በዚህ የመስኖ ፕሮጀክት ውስጥም ከግንበኝነት እስከ አናፂነት ከአናፂነት እስከ ኤሌክትሪክ ሰራተኛነት አገለገለ። ውሃ አጣጩንም ከዛው አግኝቶ አገባ። ቤት በአፋር፣ ጭፍራ ተከራየ። ልጆችም ወለደ። በመስኖ ፕሮጀክት ውስጥ እያለ የቀሰመውን የግንባታ ስራ ሙያ በመጠቀም ያገኘውን የተለያዩ የግንባታ ስራዎችን ይሰራም ጀመር። ቀስ እያለም አነስተኛ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ ደጃፉ ላይ ከፈተ። በዚህ መልኩ ቤተሰቡን እየደጎመ ኑሮን ሲገፋ ቆየ።

የሕወሓት ሃይል የመጀመሪያውን ወረራ አፋር ላይ ሲያደርግ በርካቶች ቀያቸውን ለቀው ሲወጡ አቶ አቡበከርም አብሮ ወጥቶ ነበር። ሆኖም የመከላከያ ሰራዊቱ ወራሪውን ሃይል ከአካባቢው ጠራርጎ ሲያወጣ የአካባቢው ነዋሪ ሕወሓት ዳግም አይመለስም በሚል ሙሉ እምነት በፊት ከነበረው በተሻለ ንግዱንም አካባቢውንም ይበልጥ አሙቆት ነበር። እርሱም በጫካ ሸሽጓቸው የነበሩትን ልጆቹን አውጥቶ ዳግም ወደ ነበረው የህይወት እንቅስቃሴው ተመለሰ።

የሕወሓት ቡድን ጭፍራን ጨምሮ ሌሎች የአፋር አካባቢዎችን ዳግም ሲወር ነገሮች ሁሉ ተገለባበጡ። እንደዛ ሞቅ ብላ የነበረችው ጭፍራ በወራሪ ቡድኑ በደረሰባት ከፍተኛ ዝርፊያ እርቃኗን ቀረች። ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና ሲል የነበረው የአቶ አቡበከር ቤት ንብረትም በአንድ ጀምበር ኦና ሆነ። ሱቁንም ተዘረፈ።

ይህ ሁሉ ሆኖ ታዲያ አቶ አቡበከር ቤተሰቡን ወደ ወረባቦ ጀንጀሮ ወደሚባል አካባቢ ካሸሸ በኋላ ከሰራዊቱ መለየት አልፈለገም። እንዲያውም የእርሱን ብቻ ሳይሆን እርሱ የሚኖርበትን አካባቢ ያወደመውን ይህን አረመኔ ቡድን ከሰራዊቱ ጎን በመሆን የመበቀያው ጊዜ ይህ መሆኑን በመረዳት ለሰራዊቱ ደጀን ለመሆን ወሰነ።

ከአካባቢው ሰው ሽሮ፣ በርበሬና እንጀራ እያሰባሰበ ለሰራዊቱ መስጠት ጀመረ። ቁስለኞች ሲያጋጥሙ ሌሎችን በማስተባበር ወደ ሌላ አካባቢ ሄደው እንዲታከሙ አደረገ። የሞቱት ደግሞ ተገቢውን ክብር አግኝተው እንዲቀበሩ ህዝቡን አስተባብሯል። ውሃ በጀሪካን ቀድቶና በጀርባው ተሸክሞ ለሰራዊቱ አቀብሏል።

ወራሪው ቡድን ገፍቶ ወደ ወረባቦ ከመጣም በኋላ አቶ አቡበከር ለሰራዊቱ ያለውን ደጀንነት በብዙ መልኩ አሳይቷል። እንደውም የመከላከያ ሰራዊት አባል የነበረ በመሆኑ መሳሪያ የማግኘት እድል ስለነበረና ቦታውም ለውጊያ አመቺ በመሆኑ በወረባቦ አካባቢ ያለውን ወጣት በማስተባበር እርሱ ከፊት ሆኖ ለመፋለም ዝግጁ የነበረ ቢሆንም የሚከተለው ሰው ግን ሊያገኝ አልቻለም።

ቆስለው በጤና ጣቢያዎች ውስጥ ላሉ የሰራዊቱ አባላትም ምግብ በማምጣት፣ ከባንክ ገንዘብ አውጥቶ በማቀበልና ከራሱም ጭምር ገንዘብ አውጥቶ በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ አድርጓል። ነገሮች ተጠናቀው ወራሪው ቡድን በመከላከያ ሰራዊቱ ተመቶ አካቢውን ከለቀቀ በኋላ መንገዶች ሲከፈቱ አቶ አቡበከርም ሙሉ ቤተሰቡን ይዞ ወደ አዲስ አበባ መጣ።

አዲስ አበባ ከመጣ በኋላም ወረባቦ እያለ ቁስለኞቹ ወደ እርሱ አካውንት ያስገቡትን ገንዘብ ለቤተሰቦቻቸውና ለሚቀርቧቸው በማስረከብ ትክክለኛ ኢትዮጵያዊ ጨዋነቱን አሳይቷል።

ረጅም አመታትን በአፋር ጭፍራ ያሳለፈውና በርሃ የለመደው አቶ አቡበከር ቀን ጥሎት ዛሬ በወንድሙ ቤት አዲስ አበባ ተጠልሏል። ወንድሙን እያስቸገረ ከእርሱ ጋር ተጠግቶ መኖሩ አሳቆታል። እጁ ላይ ምንም ነገር የለም። በዚሁ ጦርነት ጦስ ምክንያት በተለይ ሁለቱ ልጆቹ ያለትምህርት መቀመጣቸው በጣም ያሳስበዋል። ወደ ሁለት ወር እየተጠጋት ያለችው የመጨረሻ ጨቅላ ልጁን ለማሳደግም ዳግም ታች ላይ ማለት እንዳለበትም ያውቃል።

አፋር ጭፍራ ያለው ሁኔታ ከተስተካከለና ለመኖር አመቺ ሁኔታ ካለ አቶ አቡበከር አሁንም ቢሆን ተመልሶ ለመሄድ ዝግጁ ነው። እንኳን እሱ ይቅርና ባለቤቱና ልጆቹም ወደ አገራችን እንመለስ እያሉ ይወተውቱታል። በአፋር ጭፍራ አቶ አቡበከርን መሰል በርካታ ከሌሎች አካባቢ መጥተው የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት የሚፍጨረጨሩ ብዙ ናቸው። እነዚህ ሰዎች በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቅለዋል። ሆኖም በአሁኑ ወቅት እነዚህ ሰዎች ወደ ቄያቸው ተመልሰዋል።

ልክ እንደነዚህ ሰዎች ሁሉ አቶ አቡበከርም ወደ ጭፍራ ተመልሶ የቀድሞ ህይወቱን ዳግም መጀመር ይፈልጋል። ነገር ግን ይህን ለማድረግ መንግስት ለነዚህ ሰዎች በበቂ ሁኔታ እርዳታ ሊያደርስ ይገባል ባይ ነው። ኑሯቸውን ሳይሳቀቁ እንዲገፉና ሰርተው እንዲበሉ መንግስት የመኖር ዋስትናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅበታልም ነው የሚለው።

‹‹ይህን ሁሉ ድጋፍ ለመከላከያ ሰራዊቱ ያደረኩት የኢትዮጵያዊ ዜግነት ግዴታ ስላለብኝና ለአላህ ብዬ›› ነው የሚለው አቶ አቡበከር የወታደርን ህይወት እኔም ወታደር ሆኜ አውቀዋለው፤ ስለዚህ መከላከያውን ረዳሁ ሲል ይገልፃል። ይህን ሁሉ ነገር ሳደርግ ግን ለቤተሰቤና ለኑሮዬ ቅድሚያ መስጠት አቅቶኝ አይደለም፤ የአገር ፍቅር ህሊናዬ ይዞኝ እንጂ" ሲል እምባ እየተናነቀው ይናገራል።

እንደ አቶ አቡበከር ሁሉ በርካታ ያልተነገረላቸውና በዚህ ጦርነት ለአገራቸው ቅድሚያ ሰጥተው ሰራዊቱን ያገዙ፣ አብረው የተዋጉና ያዋጉ ህይወታቸውንም የገበሩ በርካቶች ናቸው። ግን ማን ያውራላቸው? ማን ይናገርላቸው? በእኛ ባህል ሁሌም ጀብዱ የሚነገርለት ከፊት ያለው ብቻ ነው።

‹‹የኋላው ከሌለ የለም የፊቱ›› ነውና ተረቱ አቶ አቡበከርን የመሰሉና በጦርነት የኋላ ደጀን ሆነው ለአገራቸው ውለታ የዋሉ ሰዎች ሊመሰገኑና ሊሸለሙ ይገባል። አሁን ያሉበት የህይወት ሁኔታ ታይቶም በመንግስትም ሆነ በህብረተሰቡ በተለያየ መልኩ ድጋፍና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፤ የእለቱ መልእክታችን ነው። ሰላም!!

# ስፖርት



## በሃምቡርግ ማራቶን ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች የአሸናፊነት ግምት አግኝተዋል

ብርሃን ፈይሳ

በጀርመን የጸደይ ወራት ከሚካሄዱ የአትሌቲክስ ውድድሮች ትልቁ የሃምቡርግ ማራቶን ነው። የተጀመረው እአአ ከ1986 የሆነው ይህ የማራቶን ውድድር፤ በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው የጎዳና ላይ ውድድሮች መካከል አንዱ ነው።

በዘንድሮው ነገ በሚካሄደው በዚህ ሩጫ ላይም 25ሺ ሰዎችን በማካፋል እንደሚካሄድም የውድድሩ አዘጋጆች አስታውቀዋል። በውድድሩ ላይ ከመላው ዓለም የተወጣጡ በርካታ አትሌቶች ተካፋይ ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ደግሞ አሸናፊ ይሆናሉ የሚል ቅድመ ግምት አግኝተዋል።

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በብዛት ከሚካፈሉባቸው የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ኢትዮጵያውያኑ በውጤታማነትም ውድድራቸውን የሚያጠናቅቁበት ነው። ለዚህም ማሳያ ከሚሆኑት መካከል በሴቶች የቦታውን ክብረወሰን በኢትዮጵያዊቷ ጠንካራ አትሌት መሰለች መልካሙ እስካሁን መያዙ ነው። አትሌቷ ክብረወሰኑን ያስመዘገበችው እአአ በ2016 ሲሆን፤ በወቅቱ የገባችበት 2:21:54 የሆነ ሰዓት እስካሁን ሊሻሻል አልቻለም።

በዚህ ውድድር ላይም ተሳታፊ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን የተሻለ ሰዓት በማስመዝገብ ያጠናቅቃሉ በሚል ከሚጠበቁት መካከል አንዷ በግማሽ ማራቶን የምትታወቀው አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ናት። በጎዳና ላይ ሩጫዎች ፈጣን ሰዓቶችን በማስመዝገብ የምትታወቀው አትሌቷ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በሃምቡርግ የማራቶን ውድድሯን ታደርጋለች፤ ይሁንና የተሻለ የአሸናፊነት ግምት ካገኙት አትሌቶች መካከል ቀዳሚዋ ሆናለች።

በግማሽ ማራቶን ውድድሮች ስኬታማ የሆነችው አትሌቷ፤ ርቀቱን 1:03:51 የሆነ ሰዓት በመሮጥ የዓለም ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት የግሏ ነው። ከሁለት ወራት በፊት በ10 ኪሎ ሜትር ሩጫ 24 ደቂቃ ከ29 ሰከንድ ከ14 ማይክሮ ሰከንዶች በመሮጥ የዓለም ክብረወሰኑን በእጇ ማስገባቷ ይታወሳል። በታላቁ የኢትዮጵያ ሩጫ ላይም ውድድሩን በቀዳሚነት ማጠናቀቋ አይዘነጋም።

በአሰልጣኝ ተሰማ አብሽሮ የምትሰለጥነው አትሌቷ ግማሽ ማራቶንን ከ10 ጊዜያት በላይ በመሮጥና አሸናፊም በመሆን ከፍተኛ ልምድ አላት። ይህም አትሌቷን ለተሻለ ተፎካካሪነት እንድትጠበቅ አድርጓታል። የውድድሩ አዘጋጆችም የመጀመሪያ ውድድሯን በስኬት የማጠናቀቅ አቅም ያላት አትሌት ናት ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

አትሌቷ ውድድሩን አስመልክቶ በሰጠችው አስተያየትም ‹‹የማራቶን ሩጫዬን በሃምቡርግ በመጀመሬ እጅግ ደስታ ይሰማኛል። በዚህ ውድድር ለመሳተፍ ብቻም ሳይሆን ክብረ ወሰን የሆነ ሰዓት ለማስመዝገብ እፈልጋለሁ›› ብላለች።

በወንዶች በኩል ደግሞ እአአ በ2017 የሀምቡርግ ማራቶን አሸናፊ የነበረው አትሌት ጸጋዬ መኮንን ተካፋይ እንደሚሆን የውድድሩ አዘጋጆች አረጋግጠዋል። አትሌቱ አሸናፊ በሆነበት ውድድር ያስመዘገበው 2:07:26 የሆነ ሰዓት ይሁን እንጂ፣ እአአ በ2014 የዱባይ ማራቶን የገባበት 2:04:32 የሆነ ሰዓት ምርጡ ነው። የ26 ዓመቱ ወጣት አትሌት በቦታው ያለውን ልምድ ተጠቅሞ የውድድሩ አሸናፊ ሊያም ተፎካካሪ ያደርገዋል የሚል ግምት አግኝቷል።

የበርሊን ማራቶን ቻምፒዮኑ ጉዬ አዶላም የዚህ ውድድር ተካፋይ ሲሆን፤ ሁለቱ አትሌቶች አሸናፊዎች እንደሚሆኑ በስፖርት ቤተሰቡ ይጠበቃሉ። ምክንያቱ ደግሞ ሁለቱም አትሌቶች ከ2 ሰዓት ከ05 ደቂቃ በታች የሆነ ሰዓት ስላላቸው ነው። ያለፈው ዓመት የበርሊን ማራቶን አሸናፊ አትሌት ጉዬ አዶላ 2:03:46 የሆነ ፈጣን ሰዓት አለው። አትሌቱ ከጉዳት፣ የኮቪድ ወረርሽኝ እና ሌሎች ምክንያቶች ጋር በተያያዘ ለሁለት ዓመታት ከውድድር ርቆ ቆይቶ በተካፈለበት ውድድር ነበር ውጤታማ የሆነው። በምርጥ አቋም ላይ የሚገኘው አትሌቱ በሃምቡርግ ሲሮጥ ይህ የመጀመሪያው ቢሆንም ለተፎካካሪዎቹ ፈተና እንደሚሆን ተገምቷል።

እአአ 2019 ላይ ቫሌንሺያ ማራቶንን 2:03:51 በሆነ ሰዓት የሮጠው ክንዴ አጣናውም በውድድሩ ሌላኛው ተጠባቂ ነው። የፓሪስ ማራቶንን 2:04:48 በሆነ ሰዓት የሮጠው ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አበበ ደገፋም በውድድሩ አንደሚሳተፍ ታውቋል። የጎረቤት ሃገራት ኬንያ፣ ኤርትራ እና የኡጋንዳ አትሌቶችም የኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ተፎካካሪ እንደሚሆኑ ይጠበቃል።


አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው በመጀመሪያው የማራቶን ውድድሯ እንደምታሸንፍ ይጠበቃል፤


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | የአመልካች ስም ፡- ነፃነት ዋሴ አላምረው<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ. 01 የቤት ቁጥር. 064/4, ኮ/ቀራኒዮ, አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ | | |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/11623/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 25/04/2014 E.C. | | |
| 3. | ምልክት፡ Beky Furniture | 4. | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5. | የቀለም ዓይነት፡- ሀምራዊ እና ቢጫ |
| | | 6. | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡-<br>የሶፋ ምስል (Furniture and image of sofa) |
| | | 7. | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 20 |
| 8. | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረት (ምድብ 20) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-225 15/8/2014 (23/4/2022)**



### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | የአመልካች ስም ፡- ቅናሽ ቴክኖሎጂስ ኃላ/የተ/የግ/ማ<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 10 የቤት ቁጥር 589/12 , ጉለሌ, አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ | | |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/11708/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 19/05/2014 E.C. | | |
| 3. | ምልክት፡ QINASH | 4. | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5. | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁርና ነጭ |
| | | 6. | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ፡- |
| | | 7. | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 42 |
| 8. | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ሶፍትዌር መፈብረክ (ዲዛይን ማድረግ ማበልፀግና ትግበራን ያካትታል ) (ምድብ 42) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-225 15/8/2014 (23/4/2022)**



### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | የአመልካች ስም: The Arabian Petroleum Supply Co<br>የአመልካች አድራሻ:-P.O.Box1408, Jeddah-21431,Saudi Arabia | | |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር:- FTM/ 13200<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን: 28/2/2022 | | |
| 3. | ምልክት፡ أبسكو | 4. | የምልክቱ መግለጫ:- የምስል |
| | | 5. | የቀለም ዓይነት፡- ቀይ፣ ሰማያዊ እና ነጭ |
| | | 6. | የብቸኝነት መብት አለመጠየቅ ፡- |
| | | 7. | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 4 |
| 8. | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች:-<br>በአመጋገብ እና በተለዋዋጭ ዘይቶች ውስጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉት ዘይቶችና ቅባቶች በስተቀር በኢንዱስትሪው ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘይቶችና ቅባቶች፤ ለሞተር ሥራ የታቀዱ ሰው ሠራሽ ዘይቶችን ጨምሮ አፈርን ለማዳቀል እና ነዳጅ ለመምጠጥ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እና ዝግጅቶች፤ የብርሃን ቁሶች፤ የሁሉም ዓይነቶች ሻማዎችን ማብራት እና ዊኪዎችን ማብራት (ምድብ 4) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከትነውን የንግድ ምልክት ለማስገንዘብ ማመልከቻ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታውቂያ በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት ካልቀረበ፣ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን።ስለሆነም ማንኛውም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፍቃድ ውጪ በዚህ ምልክት በሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል፡፡

**የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-225 15/8/2014 (23/4/2022)**



### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | የአመልካች ስም ፡- ጭዋኔ አስመጪና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>የአመልካች አድራሻ፡- ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 865 , አራዳ , አዲስ አበባ , ኢትዮጵያ | | |
| 2. | የማመልከቻ ቁጥር ፡- LTM/11929/2014<br>ማመልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን፡- 02/07/2014 E.C. | | |
| 3. | ምልክት፡ ጭዋኔ አስመጪና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማ Chweani Import & Export PLC | 4. | የምልክቱ መግለጫ፡-የቃልና ምስል |
| | | 5. | የቀለም ዓይነት፡- ጥቁር እና ነጭ |
| | | 6. | የብቸኛነት መብት አለመጠየቅ መግለጫ:<br>አስመጪና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር (Import & Export PLC) |
| | | 7. | ዓለም አቀፍ ምድብ፡- 35 |
| 8. | ማመልከቻው የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች | | |
| | ጥራጥሬ እህሎች ላኪነት፣ ቅባት እህሎች ላኪነት፣ የመንገድ እና ደረቅ ጭነት አገልግሎት፣ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች እና የኬሚካል ውጤቶች አስመጪ፣ ለህክምና፣ መድሀኒት እና ምግብ ማምረት አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎች አስመጪ፣ የሰው መድሀኒት እና የህክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች አስመጪ(ምድብ 35) | | |

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ 60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት በመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን መ/ቤት ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ሰው ካለባለቤቱ ፍቃድ በዚህ ምልክት ከተጠቀመ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል፡፡

**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXI No-225 15/8/2014 (23/4/2022)**